# 5. የሰብአዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ በኢትዮጵያ ታሪክ

## የጦርነትና የሰብአዊ መብት ቅራኔ

የታሪክ እውቀትና እውነት በስልታዊ ሙያና ትምህርት ተመር ምሮ የሚታወቀው በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ በተወሰኑ ሰዎች በተፈጸመ የሥራ መረጃና ሚዛን ነው። በሌላ ቃል የታሪክ ትምህርት መነሻና መሠረት በተወሰነ ሥፍራ፣ ጊዜና ተግባር የተፈጸመ የሰዎች ሥራ ነው። በዚህ አጭር ትርጉም መሠረት ታሪክ ረቂቅ የተፈጥሮ ክስተት ወይም ምስጢራዊ የአማልክት ተአምር ሳይሆን በሥፍራና በጊዜ የሚገለጽ ሰብአዊ ተግባርና ማኅበራዊ ትምህርት ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ በተለይ ላለፉት 700 (1270-1974) ዓመታት ከአገር ውጭ የግብፅና የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖትና የቋንቋ አስተማሪዎች በአገር ውስጥ ከሰለሞ ናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎች ጋር በእምነትና ትምህርት ተስማም ተው የኢትዮጵያን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖ ቶችና ባህሎች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ከይሁዳውያኑ የፍጥረትና የሃይማኖት ትምህርት ጋር በሥፍራና በጊዜ በማያያዝ የአገሪቱን ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ በዓመተ ዓለም በአንደኛው ሚሊኒየም መጀመሪያ አጋማሽ (1000-500) የፈጠሩት ባለቤቶችና ጌቶች ከኢየሩ ሳሌምና ከምድረ አረቢያ የገቡ «ምርጥ» ሴማዊ የአይ ሁድና የአረብ ነገዶች ናቸው ብለው አስተምረዋል።

በዚህ የግብፅና የአውሮፓ አስተማሪዎች ትምህርት መሠረት፣ የኢትዮጵያ የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎች መላ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር አዋማዊ፣ እስላማዊና አረታዊ ሕዝቦችን፣ ቋንቋዎችን፣ ሃይማኖቶችንና ባህሎችን በሙሉ ለመቆጣጠርና ኢትዮጵያ በሚል ስም የራሳቸውን አህዳዊ ማኅበረሰብ፣ ሃይማኖት፣ መንግሥትና ታሪክ ለመፍጠር ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ባካሄዱት የጦርነትና የጭቆና ፖሊሲ የሰሜን/ፈላሻ፣ የሸዋ፣ የህዲያ፣ የዳሞት፣ የይፋት፣ የደዋሮ፣ የአርባቢኒ፣ የሻርካ፣ የባሌ፣ የአዳል፣ የዜይላ፣ የፈጠጋር፣ የአውሳ፣ የእናርያ፣ የከምባታ፣ የአይመላል፣ የጉራጌ፣ የጋፋት፣ የቦሻ፣ የጃንጀሮ/የም፣ የወላይታ፣ የጋሞ፣ የቀቤና፣ የጊቤ፣ የሐረሪ፣ የከፋ መንግሥታትን ጨምሮ ብዙ አገሮችንና ሕዝቦችን በባሪያ፣ በገባር፣ በነፍጠኛ፣ በጢሰኛና በባላባት ሥርዓቶች እንደገዙና ቋንቋዎችን፣ ሃይማኖቶችንና ባህሎችን "ጨፍልቀው" ለማጥፋት ሁለአቀፍ የፖለቲካና የሕግ እርምጃዎችን እንደወሰዱ ራሳቸው በዜና መዋዕሎችና በቅዱሳን ኃይሎች ቀርበው ለትውልድና ለታሪክ በደፋ አሰውቀዋል።





በዚህ የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና ታሪክ የጦርነትና የጥፋት ሥርዓ ታዊ ምንጭና መነሻ አህዳዊ የመንግሥት ሥርዓት ነው። በዚህ ጥናት ተደጋግሞ እንደተገለጸው፣ የቅርጽና የእድገት ደረጃ ልዩነት ሳይደረግ በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ መንግሥት አንድ የተወሰነ የመሬት ክልል፣ የመሬቱ ባለቤት ሕዝብና የፖለቲካ ሥልጣን ሕጋዊ መስተ ጋብር ነው። የዚህ የመንግሥት ዋናው መሠረትና መግለጫ የፖለቲካ ሥልጣን ነው። በምንም ሥፍራና ሥርዓት የፖለቲካ ዓይነት የግድ የመንግሥትና የኅብረተሰብ ዓይነትና የዕድገት ደረጃ ይወስናል። ባጭሩ የመንግሥት ሥልጣን በአንድ በተወሰነ መሬትና ሕዝብ ላይ በሕይወትና በንብረት ጉዳዮች ይግባኝ የማይኖረውን የመጨረሻ ውሳኔ ለማሳለፍ የሚችል የበላይ ኃይል ነው። ይህ ወሳኙ የመንግሥት ሥልጣን በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ ከሶስቱ በአንዱ መንገድ ማለትም ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ ትውፊታዊ የሥልጣን ውርስ ወይም በመሣሪያ ኃይል ወይም በዲሞክራሲያዊ የሕዝብ ውሳኔ ሊገኝ እንደሚችል ታሪክ ጨምሮ ያስተምራል።

የመንግሥት ሥልጣን የሚገኝበት መንገድና መሣሪያ ደግሞ ዘውዳዊ ይሁን ወታደራዊ ወይም ሕዝባዊ የአንድ መንግሥትን ዓይ ነት፣ ድርጅትና ተግባር ይወስናል። በዚህ ረገድና ተግባር የመን ግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነና የሚሆን ኃይል ራሱ በራሱ የመንግሥት ሥልጣን ሉአላዊ ምንጭም ባለቤትም ነው። በመሆኑም በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለ ቤት ያልሆነና የማይሆን ሕዝብ ነፃና የራሱ ጌታ የሆነ ሕዝብ ነው ሊባል አይችልም። የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት ያልሆነና የማይሆን ሕዝብ ደግሞ ሰብአዊ ክብሩንና መብቱን፣ ሕይወቱንና ንብረቱን የሚጠብቅበት የሚከላከልበት መንገድና መሣሪያ የለውም። የመንግሥትን ዓይነት፣ ድርጅትና ተግባር በሚመለከት ደግሞ ከፖለቲካ ሥርዓትና ሥልጣን አኳያ መንግሥት ሥልጣኑና ተግባሩ በተለያዩና ሉአላዊ በሆኑ ማለትም በመብትና በግዴታ እኩል በሆኑ የፖለቲካ አካላትና ኃይሎች መካከል የማይከፈል አህዳዊ የተማከለ መንግሥት ወይም ሥልጣኑ በተለያዩ በመብትና በግዴታ እኩልና ሉአላዊ በሆኑ የፖለቲካ አካላትና ኃይሎች መካከል የሚከፈል ፌደራላዊ ኅብረመንግሥት ሊሆን ይችላል። መንግሥት አህዳዊም ሆነ ፌደራላዊ በራሱ ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የሚከሰትና የሚከስም ማኅበራዊ ሥርዓት ነው።

በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ እንደ ኢትዮጵያ ባለው በአንድ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረ ተሰብ ላይ የተማከለ አሀዳዊ መንግሥት በኅብረተሰቡ ላይ በኃይል የተመሠረተ የጭቆና ኃይልና ሥርዓት እንደሆነና እንደሚሆን ታሪክ ያስተምራል።

ምክንያቱም የበህውርታዊ ኅብረትና የአሃዳዊ መንግሥት መስተጋብር ሁልጊዜ ራሱ በራሱ የቅራኔ፣ የግጭትና የመከራ ሥርዓት ነው። በበህውርታዊ ኅብረተሰብና በአሀዳዊ መንግሥት ቅንጅት በውርስ ሆነ በኃይል ወይም በምርጫ የሚገኘውን የመንግሥት ሥልጣን በእጁ ይዞ የሚገዛው ኃይል ሊመጣ የሚችለው ከአንድ ከተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል፣ ወገን፣ መደብ ነው።

በመሆኑም በአንድ በህውርታዊ ኅብረተሰብ የገዥው መደብ ይግባኝ የሌላውን የመንግሥት ሥልጣን በእጁ ይዞ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሁሉን ወገኖች ሕጋዊና ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ጉዳዮችንና ፍላጎቶችን በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እና አሠራር በአንድነትና በእኩልነት ለማክበርና ለማስከበር አይች ልም። አቅምም አይኖረውም።

ስለሆነም በአንድ በህውርታዊ ኅብረተሰብ አሀዳዊ የተማከለ የመንግሥት ሥልጣን የሚይዘው ኃይል በፖሊሲና በተግባር ወገናዊና አካባቢያዊ ይሆናልI ብሎም በፖለቲካ፣ በሥርዓት፣ በመብት፣ በጥ ቅም፣ በክብር፣ በታሪክ፣ በሀብትና በባህል ጉዳዮች ምዕከልና ፖሊሲ ያካሂዳል። በሥርዓቱና በሁኔታው አስገዳጅነት ወገናዊና ጨቋኝ ኃይል ይሆናል። በደፋ የሚነገረውን በቲዮሪና በቃለመፊክር የሚሰብከውን አገራዊና ሕዝባዊ ጉዳይ በወገናዊ ተግባሩ ያፈርሳል። በኅብረተሰቡ ዘንድ በአንድ በኩል ብሔራዊ የአንድነት፣ የፀጥታና የክብር ዓላማና ጉዳይ ይሰብካል። በሌላ በኩል ግን በኅብረተሰቡ ዘንድ ዲሞክራሲያዊ እኩልነትና ማኅበራዊ ፍትህ ተግባራዊ እንዳይሆን ያደርጋል። በመሆኑም በኅብረተሰቡ ዘንድ ማኅበራዊ ሰላምና ሕዝባዊ አንድነት አይገኝም። ማኅበራዊ ዕድገት፣ ፍትህና እኩልነት አይገኝም። ከዚህም የተነሳ በአሀዳዊ ኃይሎች ላይ የሕዝቡ ጥላቻና አመጽ ይቀሰቅሳል። በዚህ ሁኔታ በበህውርታዊ ኅብረተሰብ የአሀዳዊ መንግሥት ሕይወትና ተግባር የሚወሰነው በኃይል ብቻ ይሆናል።

ባጭሩ እንደ ኢትዮጵያ ባለው በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት የፖለቲካ ምዕከልና ፖሊሲና ተግባር ማለት የኃይልና የጭቆና ሥርዓት ስለሚሆን በኅብረተሰቡ ውስጥ የአመጽ ሁኔታዎችን ኃይሎችንና እንቅስቃሴዎችን





ይፈጥራል። በዚህ ወቅትና ሂደት ለገዥው መደብ በአመጽ ሀሳቦች፣ ኃይሎችና እንቅስቃሴዎች ላይ በአገርና በሕዝብ ስም፣ በአንድነት በሰላምና በፀጥታ ስም የኃይል ፖሊሲና ፖለቲካ መከተልና መጠቀም የሥርዓትና የሕይወት ጉዳይና ግዴታ ይሆናል። ባጭሩ በኅብረተሰቡ ዘንድ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ እስኪደረግ ድረስ ማለትም ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች እስኪከበሩ ድረስ የሕዝቡ ተዛማጅ የመከራና የአመጽ ሕይወት ይቀጥላል።

## የሰብአዊ መብትና ነፃነት ትምህርት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

### *የሰብአዊ መብትና የነፃነት ሞዴሎች*

1.የተፈጥሮ ሕግ ሞዴል

ከሰው ልጅና ከሥልጣኔ ረጅም ታሪክ እንደሚታወቀው፣ በየ ትም ሥፍራና በምንም ጊዜ እንደሰብአዊ ነፃነትና እንደ ዲሞክራሲያዊ መብት ያለ የፍልስፍና መሠረተ-ሀሳብ፣ እምነትና ትምህርት ሁልጊዜ የአንድ በሥፍራና በጊዜ የተወሰነ ስልተምርትና ሥርዓተ ማኅበር መግለጫ ነው። መሠረተ-ሀሳቡም የሚፈጠረው በኅብረተሰቡ ዘንድ በአሮጌና በአዲስ ማኅበራዊ ሥርዓቶች መካከል ማለትም በሁለት ተከታታይና ተቃራኒ የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች መካከል በሚፈጠረው ሥርዓታዊ ቅራኔና ግጭት ምክንያት ነው።

በዚህ ረገድ የሰብአዊ መብትና ነፃነት መሠረተ ሀሳብ የፖለቲካ ፍልስፍና ሆኖ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው ከሶስት ምዕተ ዓመታት በፊት በአውሮፓ አገሮች በአሮጌው ዘውዳዊና ሃይማኖታዊ የፊውዳሊዝም ሥርዓትና በአዲሱ የቡርዧ ካፒታሊዝም ሥርዓት መካከል በተፈጠረው የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ቅራኔና ግጭት ሂደት እንደሆነ ታሪክ ያስተምራል።

በዚህ ታሪካዊ የሽግግር ዘመን በተለይ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ፈላስፋዎች፣ ሳይንቲስቶችና ምሁራን የፊውዳልዝምን ሃይማኖታዊ መሠረተ-ትምህርትና ርዕዮተ ዓለም ውድቅ በማድረግ የሕይወትና የሕልውና መነሻና መሠረት የተፈጥሮ አካባቢና ሁኔታ ነው የሚል አብዮታዊ መሠረተ ሀሳብና ትምህርት አስተማሩ። የሰው እውቀት መነሻ በሰው አዕምሮና በተፈጥሮ አካባቢ መካከል የሚካሄደው ተግባራዊ መስተጋብርና ዕድገት ነው በማለት ሰውን፣ ተፈጥሮን፣ እውቀትን፣ ማህበራዊ ሥርዓትንና ንብረትን በሚመለከት ፀረ-ፊውዳልዝም የሆነ አብዮታዊ የግንዛቤ ሀሳብና ትምህርት አስፋፉ። ተፈጥሮ፣ ሰውና ማህበራዊ ሥርዓት ሁሉም ከመሬት ጋር በአንድ ላይ ሕያው፣ አዳጊና

ተንቀሳቃሽ፥ ብሎም ቋሚ የሕይወትና የኃይል ምንጭ በሆነው ፀሐይ ዙሪያ ዘውትር የሚንቀሳቀሱ ነገሮችና አካላት እንደሆኑ አስተማሩ። የሰው ልጅ ሲወለድ አዕምሮው ባዶ ጥቁር ሰሌዳ ብቻ እንደሆነ ብሎም በባዶ የአዕምሮ ሰሌዳ ላይ የሰው አሳብና ቋንቋ እውቀትና ትምህርት በተግባራዊ ሥራና ልምድ በሥፍራና በጊዜ ቀመር እንደሚፈጠርና እንደሚያድግ ገለጹ።

በዚህ የአውሮፓ ፈላስፋዎች፥ ሳይንቲስቶችና ምሁራን ትምህርትና ግንዛቤ መሠረት፥ የሰው ልጆች የዘር፥ የጾታ፥ የቀለም፥ የሥፍራና የጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም በተፈጥሮ ነፃ፥ እኩልና ወንድማማች ናቸው። ሰው ራሱንና አካባቢውን በአዕምሮ መሣሪያዊው የሚያውቅና የሚለውጥ ሕያው አካል ነው። በዚህ ሕያውና አዳጊ የተፈጥሮ ሀሳብ፥ ሕግና ትምህርት መሠረት የሰው ልጅ የግል ሕይወትና ንብረት ያለባለቤቱ ፈቃድና ፍላጎት በማንም ሌላ ሰው በምንም መንገድና ሥርዓት የማይደፈር ውድና ክቡር ነገር ነው ተባለ። የሰው ልጅ የግል ሀብት የግለሰቡ ጥንካሬ፥ ትጋትና ብርታት ውጤት ነው። ኅብረተሰብ የግለሰቦች ስብስብ፥ ድርጅት ነው። በመሆኑም መንግሥት በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ ሊጋራ ደህንነትና አገልግሎት በነዋሪ ዜጎች ሉአላዊ ፍላጎትና ፈቃድ የሚመሠረት የፖለቲካ ሥርዓት ነው። የሕዝቡ የግልና የጋራ ሕይወት፥ ንብረትና ክብር ከሕግ አኳያ የሚከበረ ውና የሚዳብረው በዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና አሠራር እንደሆነ፥ ዲሞክ ራሲ ራሱ የሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣንና ሥርዓት እንደሆነ ተገለጸ።

ይህ በተፈጥሮ ሕግና ተግባር ሞዴል የተመሠረተው የቡርዧ ፈላስፋዎች፥ ሳይንቲስቶችና ምሁራን ትምህርት በምዕራቡ ዓለም በአንድ በኩል በአሮጌው የፊውዳሊዝም ሥርዓት ላይ ለአዲሱ የካፒታሊ ዝም ሥርዓት ድል የፖለቲካና የርዕዮተዓለም መሠረትና መሣሪያ ሆነ። በሌላ በኩል ደግሞ የካፒታሊዝም ሥርዓት ራሱ በራሱ የቡርዧና የወዛ ደር መደቦች መካከል ቅራኔና ግጭት ፈጠረ። ቀጥሎም የኢምፔ ሪያሊዝምን ዓለማቀፋዊ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓትና ዘመን አስከተለ።

## 2.የማኅበራዊ ሥርዓት ሞዴል

በወዛደር ምሁራን ማርክስ፥ ኤንግልስና ሌኒን አመለካከት ጸረ-ፊውዳሊስት የቡርዧ ፈላስፋዎች፥ ሳይንቲስቶችና ምሁራን እንደ ገመቱት የተፈጥሮ ሞዴልና ሚዛን የሰው ልጅ ማህበራዊ ሥርዓት፥ ሕይወት፥ ክብርና መብት የሚመዘንበት ታሪካዊ ሚዛን አይደለም። የሰው ልጅ ህልውና፥ ሕይወት፥ ክብርና መብት የሚመዘነው በተፈጥሮ ሞዴልና ሚዛን ሳይሆን በማህበራዊ ሥርዓት ተግባርና ፋይዳ ነው። የማህበራዊ ሥርዓት፥ መነሻና መሠረት ደግሞ የሰው ልጅ ሥራ ነው።





የሰው ልጅ ህልውና፥ ሕይወት፥ ክብር፥ መብትና ሀብት መሠረቱና ምንጩ ማኅበራዊ ሥራ ነው። በመሆኑም በተፈጥሮ ሞዴልና በግል ንብረት የተመሠረተው የቡርዧው ካፒታሊስት ሥርዓት፥ ማኅብረሰብና መንግሥት ኢሰብአዊ የሆነ የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት፥ ኅብረተሰብና መንግሥት ነው ተባለ።

ስለሆነም የካፒታሊዝም ሥርዓት ብሎም የቡርዧው ኅብረተ ሰብና መንግሥት በወዛደሩ አብዮታዊ አመጽ ተደምስሶ በምትኩ የዘር፥ የጾታ፥ የቀለም፥ የዕድሜና የሀብት ልዩነትና ምርጫ ሳይደረግ የሰው ልጅ መሠረታዊ አንድነትና እኩልነት፥ ክብርና መብት የሚከ በርበት አዲስ ወዛደራዊ ሶሻሊስት ሥርዓት፥ ኅብረተሰብ፥ መንግሥ ትና ርዕዮተዓለም በኃይል መገንባት አለበት አሉ እነማርክስ።

በዚሁ የወዛደር ምሁራን ትምህርት መሠረት በ1917 በሌኒን መሪነት ሶሻሊስት አብዮትና ሥርዓት በዛሩ ፊውዳል ሩሲያ ተካሄደ። በሚቀጥሉት 70 ዓመታት ዓለም በሁለት ተፃራሪ የካፒታልዝምና የሶሻልዝም ሠፈሮች ተከፈለ። በሶቭዬት ኅብረት የተመራው የሶሻል ዝም ሰፈር በወዛደራዊ ዓለማቀፋዊነት ትምህርት መሠረት ባካሄደው ርዕዮተ ዓለማዊ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ በምዝብር የዓለም ወዛደሮችና በምዕራቡ ካፒታሊስት መንግሥታት የኮሎኒያሊዝም-ኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ሥር በአፍሪካ፥ በእስያና በላቲን አሜሪካ አህጉራት በጦር ኃይልና በፖለቲካ ተጽዕኖ በሚገዙ ሕዝቦች ስም የሰው ልጅን መሠረታዊ ክብር፥ መብትና ነፃነት በመሚመለከት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ታሪክ ያስተምራል።

## 3. የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሞዴል

በተጠቀሰው የካፒታሊዝምና የሶሻሊዝም ኃይሎች ቅራኔና ግጭት ዘመን በተለይም ከ1920ዎቹ እስከ 1940ዎቹ ድረስ በተዛማጅ የጦርነትና የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ሥርዓታዊ ክስረትና ውድቀት የደረሰባቸው የቡርዧ ፋሽስቶች ማለትም የከሰሩ ከበርቴዎች የካፒታ ሊዝም ሥርዓትን ከወዛደራዊ አብዮትና ከኮሚኒዝም ሥርዓት እናድን ዋሰን በሚል መነሻ በተለይም በጀርመንና በኢጣሊያ መንግሥታዊ አምባገነኖች መሪነት ባካሄዱ ጸረ-ወዛደርና ጸረ-ሶሻሊዝም ጦርነት በመላው ዓለም ላይ ስድስት ሚሊዮን የአውሮፓ አይሁዶችን ጨምሮ የብዙ ሰላማዊ ሕዝቦችን ሕይወትና ንብረት በኢሰብአዊ መንገድና አሠራር አጠፉ። የሰውን ልጅ ሕይወትና ንብረት በአረመኔአዊ ጭካኔ አጠፉ።

ከታሪክ አኳያ ይህ ኢሰብአዊና ኢዲሞክራሲያዊ የሆነ የፋሽዝም ሥርዓትና ተግባር ክስተትና ውድቀት ሰወደፊቱ በዓለም

ላይ ዳግም እንዳይነሳ ያደርጋል ተብሎ የታመነበትን የዓለም መንግ ሥታት ድርጅትና የድርጅቱንም የ1948 ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ቻርተር አስከተለ።

### የ1948 የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ቻርተር ምሥረታ

በ1948 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች አዋጅ መሠረት፥ ሰዎች ሁሉ ሲወለዱ በተፈጥሮ አቸው ነፃና እኩል ናቸው። እኩል ሰብአዊ ነፃነት፥ መብትና ክብር አላቸው። ስለሆነም የዘር፥ የቀለም፥ የጾታ፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖት፥ የፖለቲካ አቋም፥ የብሔር፥ የመደብ፥ የንብረት፥ የልደት ወይም የማዕረግ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም የሰው ልጆች በአዋጁ የተዘረዘሩ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች እኩል ባለቤቶችና ተጠቃሚዎች ናቸው። በመሆኑም ማንም ሰው የሕይ ወት፥ የነፃ ነትና የደህንነት መብት አለው። ማንም ሰው በባርነትና በገባርነት አይገዛም። ማንም ሰው ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ መሰቃየት፥ መዋረድና መቀጣት የለበትም። ማንም ሰው በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ በሕግ ፊት ሉአላዊ ክብሩ የመታወቅ መብት አለው። ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። ሁሉም ሰዎች እኩል የሕግ ዋስትና አላቸው። ማንም ሰው በሕግ የታወቁ መሠረታዊ፥ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹና ነፃነቶቹ በማንም ሲጣሱና ሲደፈሩ ሥልጣንና መብት ባላቸው ፍርድ ቤቶች የፍትህ ብይን መብት አለው። ማንም ሰው በሕገወጥ መንገድ አይያዝም፥ አይታሰርም፥ አይከሰስም፥ አይደሰ ደድም። ማንም ሰው በነፃ ፍርድ ቤቶች የፍትሐዊ ዳኝነትና ብይን መብት አለው። ማንም በወንጀል ተግባር የተጠረጠረ ሰው ከፍርድ ቤት ውሳኔ በፊት ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት አለው። ማንም ሰው በቅድሚያ በሕግ ጥፋት መሆኑ ያልታወቀ ድርጊት በመፈጸሙ በሕግ ያለመቀጣት መብት አለው።

የማንም ሰው የግል፥ የቤት፥ የቤተሰብ፥ የመልእክት ምስጢር እና የስም ክብር በሕግ የተጠበቀ ነው። ማንም ሰው በመንግሥቱ ግዛት ውስጥ የመንቀሳቀስና የመኖር መብት አለው። ማንም ሰው በፈቃዱ ከአገሩ የመውጣትና ከውጭም ወደ አገሩ የመመለስ መብት አለው። ማንም ሰው ባገሩ ሆኖ ከሚደርስበት መከራ በሌላ አገሮች የጥገኝነት መብት አለው። የፖለቲካ ስደተኞች ላልሆኑትና የተመድን ዓላማዎችና መርሆዎች ለማያከብሩ ሰዎች ግን የጥገኝነት መብት አይፈቀድም። ማንም ሰው ዜግነት የማግኘት መብት አለው። ማንም ሰው በሕጋዊው መንገድና ሥራ የዜግነት መብት አያጣም።





ለትዳር የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በጋብቻ ጥያቄ የዘር፥ የዜግነት ወይም የሃይማኖት ገደብ ሳይደረግ የመጋባት መብት አላቸው። ጋብቻ በትዳር ጓደኞች ሙሉ ስምምነት ብቻ ይፈጸማል። ቤተሰብ የኅብረ ተሰብ መሠረት በመሆኑ የመንግሥት ጥበቃ ይደረግ ለታል። ማንም ሰው በግል ወይም በጋራ ሥራ ንብረት የማፍራትና የመያዝ መብት አለው። ማንም ሰው በሕገወጥ መንገድ ንብረቱን አያጣም። ማንም ሰው የሀሳብ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ማንም ሰው ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን በግል ወይም ከሌላ ሰዎች ጋር በይፋ የመከተልና በሰላማዊ መንገድ የማስተማር መብት አለው። ማንም ሰው የራሱን አስተያየት የመያዝና የመግለጽ መብት አለው። ማንም ሰው በሰላማዊ መንገድ ከሌላ ሰዎች ጋር የመሰብሰብና የመደራጀት መብት አለው። ማንም ሰው የማንም ድርጅት አባል እንዲሆን አይገደድም።

ማንም ሰው በቀጥታ ወይም በነፃ ምርጫ በተመረጡ ወኪሎች አማካይነት በአገሩ መንግሥት ጉዳይ የመሳተፍ መብት አለው። ማንም ሰው በአገሩ በሕዝባዊ አገልግሎት በእኩልነት የመሳተፍ መብት አለው። የመንግሥት ሥልጣን መሠረቱ የሕዝብ ፈቃድ ነው። ሉአላዊ የሕዝብ ፈቃድ ወቅታዊ፥ ሀቀኛ፥ ምስጢራዊ፥ አጠቃላይ፥ እኩልና ነፃ በሆነ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል። ማንም ሰው የኅብረ ተሰቡ አባል በመሆኑ የማህበራዊ ዋስትና መብት አለው። ማንም ሰው የመንግሥቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን ለክብሩ እና ለነፃ ሰብአዊ ዕድገቱ የሚያስፈልጉ የኢኮኖሚ፥ የማኅበራዊና የባህላዊ ጥቅሞችንና አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለው።

ማንም ሰው ሥራ የማግኘት የሥራ ዓይነትን በነፃ የመምረጥ ተስማሚ የሆነ የሥራ ሁኔታና የሥራ ዋስትና የማግኘት መብት አለው። ማንም ሰው አለምንም አድሎ ለእኩል ሥራ እኩል የሥራ ዋጋ የማግኘት መብት አለው። ማንም ሰው ለሚሰጠው አገልግሎት ፍትሐዊና ተስማሚ በሆነ መንገድ ለራሱና ለቤተሰቡ ፍላጎትና ክብር በቂ ዋጋ የማግኘት መብት አለው። ማንም ሰው ጥቅሙን ለማስከበር በሙያ ማኅበር የመደራጀትና አባል የመሆን መብት አለው። ማንም ሰው የማረፍ የመዝናናት የተወሰነ የሥራ ሰዓትና ወቅታዊ የበዓል ዕረ ፍት መብት አለው። ማንም ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ፥ ለምግብ፥ ለልብስ፥ ለመኖሪያ ቤትና ለሕክምና በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብት አለው። ለእናቶችና ለልጆች ልዩ ጥንቃቄና ዕርዳታ ይደረግላ ቸዋል። ከጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች እኩል እንክ ብካቤ ይደረግላቸዋል።

ማንም ሰው የመማር መብት አለው። የትምህርት አገልግሎት ለሰው ዕድገት በብሔር፣ በዘርና በሃይማኖት በተለያዩ ሕዝቦች መካከል የሰብአዊ መብቶችን ጉዳይና የተመድን የሰላም ፖሊሲ በሚያስፋፋ መንገድና አሠራር ይዘጋጃል። ወላጆች ለልጆች የትምህርት ዓይነት የመምረጥ ቀዳሚ መብት አላቸው። ማንም ሰው ከሳይንስ ዕድገትና ምርት ለመካፈል መብት አለው። ማንም ሰው የራሱ ሥራ በሆነ የሳይንስ፣ የሥነጽሑፍ፣ የሥነጥበብ ውጤት የሚገኙ ጥቅሞችን የማስጠበቅ መብት አለው።

ማንም ሰው በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መብቶችና ነፃነቶች ሁሉ ተግባራዊ ሊሆኑ በሚችሉበት ሥርዓት ውስጥ የመኖር መብት አለው። ማንም ሰው የራሱ ስብዕና በነፃና በተሟላ መንገድና ሁኔታ ለሚያድግበት ኅብረተሰብ ተገዥ የመሆን ግዴታ አለበት። የራሱን መብቶችና ነፃነቶች ተግባራዊ የሚያደርግ ማንም ሰው የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ማክበርና ለዲሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ የሚያስፈልጉ የሞራል የሕዝባዊ ሰላምና የደህንነት ጉዳዮችንና ግዴታዎችን ማሟላት አለበት። እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች የተመድን ዓላማዎችና መርሆዎች በሚቃረኑ መንገዶች ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም። ማንም መንግሥት፣ ቡድን ወይም ሰው እዚህ ከቀረቡ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች አንዱንም ለማጥፋት የሚያስችል መብት በዚህ አዋጅ እንደተሰጠው አድርጎ መተርጎም የለበትም።

*የተመድ የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ታሪክ*

የታኅሣሥ 1948 የተመድ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ቻርተር አዋጅ በድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከድርጅቱ 56 አባል አገሮች በ48ቱ ጸደቀ። ስድስት በሶቭዬት ሩሲያ የሚመሩ ሶሻሊስት አገሮች ከሳውዲ አረቢያና ከደቡብ አፍሪካ ጋር በድምሩ ስምንት አገሮች ቻርተሩን አላጸደቁም።

የ1948 የተመድ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ቻርተር አገልግሎት በሚመለከት በድርጅቱ መድረክ በፖለቲካ ሥርዓትና በርዕዮተዓለም ጉዳዮች ላይ በአሜሪካ በሚመሩ የምዕራብ ካፒታሊስትና በሶቪዬት ሩሲያ በሚመሩ የምስራቅ ሶሻሊስት መንግሥታት መካከል የተፈጠረው ልዩነትና ግጭት በ1980ዎቹ መጨረሻ የሶሻሊዝም ሥርዓት ከሶቭዬት ሩሲያ ኃይሎች ጋር እስኪወድቅ ድረስ በቻርተሩ ዓለማቀፋዊ ይዘትና ተግባራዊነት ላይ ከባድ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ታሪክ ያስተምራል።

በዚህ ረጅም የሽግግር ዘመን በአንድ በኩል በተፃራሪ የካፒታሊስትና የሶሻሊስት መንግሥታት መካከል በተፈጠረ የሥርዓት እና





የርዕ ዮተዓለም ግጭት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዘመኑ በኢምፔሪያሊዝም ተፅዕኖ ሥር በነበሩና ዛሬ «ሶስተኛ» ዓለም አገሮች ተብለው በሚታወቁ የአፍሪካ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች በተካሄዱ የነፃነት፣ የአብዮትና የእርስ በእርስ ጦርነቶች በሰላም፣ በነፃነት፣ በአብዮትና በዲሞክራሲ፣ በአገር አንድነትና ክብር፣ በሕዝቦች እኩልነት በወዘደራዊ ዓለማቀፋዊነት ስምና ስብከት፣ ለምሳሌ በካምቦዲያ ሽብርተኞች የተጨፈጨፉ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎችን እንዲሁም የረሃብ፣ የችግር፣ የበሽታ፣ የጦርነት፣ የፖለቲካ ሽብር፣ የእሥራትና የስደት ሰለባ የሆኑ ብዙ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ጨምሮ በዓለም ደረጃ ቁጥራቸውን በአሀዝ መገመት የማይቻል ብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች ሰብአዊ መብትና ነፃነት አጥተው እንዳለቁ አይረሳም።

# 6. የኢትዮጵያ ታሪክ ድልና ትንሣኤ

## የሕዝብ የመብት ትግልና ድል

በ20ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ (1950-2000) በአንድ
በኩል ብዙ የሰነድ፣ የአርኪኦሎጂ፣ የሊንጉዊስቲክስና የፓሌኦንቶሎጂ
መረጃዎች ግኝትና ትምህርት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ አብ
ዮት በአገሪቱ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች
ኅብረተሰብና ታሪክ መሠረታዊ የሥልተምርት፣ የሥርዓተ ማኅበር፣
የፖለቲካ፣ የሥልጣን፣ የሕግ፣ የዕውቀት፣ የአመለካከት፣ የማንነቱና
ትምህርት ለውጥና ዕድገት እንዳስከተሉ በዚህ *የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና
ሃይማኖቶች ታሪክ* በስፋትና በዝርዝር ተብራርቷል።

በጥናቱ ግኝትና ትምህርት መሠረት ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ
ምድር ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የሰው ልጅ ራሱ በአካልና
በአእምሮ መሣሪያዎቹ አድጎና ዳብሮ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ
የተከሰተበት ታሪካዊ ሥፍራ እንደሆነ በፓሌኦንቶሎጂ መረጃና ትምህ
ርት መሠረት ዓለማቀፋዊ እውቅና አግኝቷል። በዚህ ረገድ በቅድመ
ታሪክ የሰው ልጆችና ቋንቋዎች ከኢትዮጵያ የመነሻ ምድር ቀይ ባሕ
ርን በፍለሳና በሰፈራ እንቅስቃሴ ተሻግረው በእስያና በአውሮፓ አህ
ጉራት እንደሰፈሩ የሊንጉዊስቲክስ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።

በዚህ አኳያ ሴማዊ የአፍሮ እስያ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች
በቅርቡ ቅድመ-ታሪክ ማለትም ከዛሬ ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት
በፊት ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ቀይ ባሕርን ተሻግረው
በአረቢያና በመካከለኛው ምስራቅ እንደሰፈሩ አሁንም የሊንጉዊስቲክስ
ሳይንስ ጨምሮ ያስተምራል። በዚህ የሊንጉዊስቲክስ መረጃና ትምህ
ርት መሠረት የኢትዮጵያ አራቱ ኩሻዊ፣ ሴማዊ፣ ናይሎቲካዊና ኦሞ
አዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች የክፍለ አህጉሩ ነባርና ጥንታዊ
ሕዝቦች ናቸው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥትና
ሥልጣኔ የፈጠሩ ሰዎች በዓመተ ዓለም በአንደኛው ሚሊኒየም (1000-
500) ከኢየሩሳሌምና ከአረቢያ የገቡ ሴማዊ የአይሁድና የአረብ
ነገዶች ናቸው ብለው የግብፅና የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፣
የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪዎች ባለፉት 700 (1270-1974) ዓመታት
ያስተማሩት መላምት የፈጠራ ተረት ሆኖ ቀርቷል።

በሌላ በኩል እስከ ዛሬ ድረስ የተገኙ የሰነድ፣ የአርኪኦሎጂና
የሊንጉዊስቲክስ መረጃዎች ጨምረው እንደሚያስተምሩ፣ በቅርቡ
ዘመነ-ታሪክ ማለትም ባለፉት ስድስትና ሰባት ሺህ ዓመታት የሰሜን
ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ነባር የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች
ከጥንቱ የግብፅ፣ የአረቢያ፣ የግሪክና የሮም ሕዝቦችና መንግሥታት





ጋር በንግድና በሃይማኖት በተለያዩ መንገዶችና ደረጃዎች ቢያንስ
ለ5000 ዓመታት ሉአላዊ መስተጋብርና መወራረስ ነበራቸው።

ነገር ግን ከዛሬ የኢትዮጵያ በህውርታዊ ኅብረተሰብና ታሪክ
ክስተትና ዕድገት አኳያ በአጠቃላይ መንገድ ሲታይ፣ የዛሬ በሥፍራና
በጊዜ ያልተቋረጠ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ሕዝቦች
ዘመናዊ ታሪክ የተከሰተው ቢያንስ ከ2500 ዓመታት በፊት በኢትዮ
ጵያ ሰሜን ደጋአምባ ምድር ላይ በየሀ-ደአማት ነው። በዚህ ጥናት
ተደጋግሞ እንደተባለው፣ በክፍለ አህጉሩ ከየሀ-ደአማት እስከ ዘመነ
አዲስ አበባ ድረስ ባለፉት 2500 ዓመታት በአምስቱ የደአማት፣ የሳባ፣
የግሪክ፣ የግዕዝና የአማርኛ ቋንቋዎች ተጽፎ የተገኘው የኢት ዮጵያ
በህውርታዊ ታሪክ በጠባብ መልኩ ሲገመገም የነገሥታትና የካህናት
ጥምር የፖለቲካና የሃይማኖት ዘገባ ነው።

ይሁን እንጂ ከሰፊው የኢትዮጵያ በህውርታዊ ኅብረተሰብ
ክስተትና ዕድገት አኳያ ሲገመገም ደግሞ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣
ሃይማኖቶችና ባህሎች የጋራ ታሪክ ነው። የብዙ ሕዝቦች የፍለሳና
የሰፈራ እንቅስቃሴዎች ታሪክ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ረጅምና
በህውርታዊ ታሪክ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች
የመስተጋብርና የመወራረስ ታሪክ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር በተለይ ባለፉት 1700 ዓመታት ከብዙ
ተከታታይ መንግሥታዊ ሥርዓቶችና ሕዝባዊ የፍለሳና የሰፈራ እንቅ
ስቃሴዎች ጋር ለኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣
ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና ታሪክ የዛሬውን ኅብረ-
መልክ፣ ቅርጽና ይዘት የሰጡ ሶስት ማኅበራዊ ኃይሎች መለኮታዊና
አሀዳዊ የሆኑ የክርስትና፣ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ናቸው።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋ
ዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ኅብረተሰብ በግብፅና በአውሮፓ
ክርስቲያን የሃይማኖት፣ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪዎች እምነትና
ትምህርት የሚመሩ የቀድሞ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎች
በግምት ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ለ700 ዓመታት የአገሪቱን አዋማዊ
እስላማዊና ኦሪታዊ ሃይማኖቶችና ሕዝቦች በሙሉ ተቆጣጥረው
የራሳቸውን አሀዳዊ የክርስቲያን ማኅበረሰብ፣ መንግሥት፣ ቋንቋ፣
ሃይማኖት፣ ባህልና ታሪክ ለመገንባት ባካሄዱት የጦርነትና የጭቆና
ፖሊሲና ተግባር ሕዝቦችን በገዛ አገራቸውና መሬታቸው ላይ በባሪያ፣
በገባር፣ በባላባት፣ በጢሰኛ፣ በጉልተኛና በነፍጠኛ ሕጎችና ሥርዓቶች
ለምዕተ ዓመታት ሲገዙ እንደኖሩና ይህም ረጅም የመከራ ዘመንና
ሥርዓት በመጨረሻ በ1974 ሕዝባዊ አብዮት ከዘውዳዊ መንግሥትና

ሥርዓት ጋር እንዴት እንደተወገደ ይታወሳል።

## የታሪክ ትንግኤና ትምህርት በአዲሲቱ ኢትዮጵያ

ሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥትንና ዘውድን ከገዥው መደብ ጋር በማስወገድ የኢትዮጵያ ብሔሮችን፥ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን በሙሉ የመሬት፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖትና የባህል ባለቤቶችና ጌቶች ያደረገው የኢትዮጵያ አብዮት እንዲሁም የዘር፥ የጎሳ፥ የቋንቋ፥ የሃይማኖት፥ የፖለቲካ፥ የሥፍራና የጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ የሁሉንም ብሔሮች፥ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክ በአገራዊ አንድነትና በዲሞክራሲያዊ እኩልነት ሚዛን አጥንቶ ለማወቅ፥ ለመጻፍና ለማሳወቅ አመቺና አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎችን፥ መንገዶችን፥ መብቶችንና ነፃነቶችን አስገኝቷል።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል የዘር፥ የጎሳ፥ የቋንቋ፥ የፖለቲካ፥ የሃይማኖት፥ የሥፍራና የጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ የብሔሮችን፥ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ታሪክ በአገራዊ አንድነትና በዲሞክራሲያዊ እኩልነት በአዲስ መልክና መንገድ እንደገና ለማጥናት፥ ለማወቅ፥ ለመጻፍና ለማሳወቅ በወደቀው ዘውዳዊ ሥርዓት በተፈጠሩ ብዙ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶችና እንቅፋቶች የማይቻል ነገር ነው ባይባልም እጅግ በጣም አስቸጋሪና ውስብስብ ተግባር እንደሆነ በሚመለከተው ሁሉ ዘንድ በቅድሚያ በግልጽ መታወቅ አለበት።

በዚህ አኳያ አንደኛ፥ ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ለ700 ዓመታት በአንድ በኩል በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብ ላይ በጦር ኃይል የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት የሆኑ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በግብፅና በአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪ ዎች ርዕዮተ ዓለማዊ ተጽዕኖ ሥር የነበሩ የቀደሞ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎችና ታሪክ ጸሐፊዎች ከራሳቸው አንድ ማኅበረሰብ፥ ቋንቋ፥ ሃይማኖት፥ ታሪክና ባህል በስተቀር የተቀሩ የሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ነባር አዋማዊ፥ ኦሬታዊና እስላማዊ ሕዝቦችንና ሃይማኖቶችን በሙሉ በግዕዝና በአማርኛ ቋንቋዎች በተጻፉ ሰነዶች የእነርሱ ታሪካዊ ጠላቶች እንደሆኑ አድርገው በይፋ መዝግበዋል። በዚህ ሃይማኖታዊ እምነትና ትምህርት መሠረት በ1974 አብዮት እስኪወገዱ ድረስ ሰለሞናዊ ነገሥታትና ገዥዎች በጠላትነት የተፈረጁ ሕዝቦችን በገዛ መሬታቸው ላይ በልዩ የባሪያ፥ የገባር፥ የጉልተኛ፥ የመልከኛ፥ የነፍጠኛ፥ የጢሰኛና የባላባት ሕጎችና ሥርዓቶች ሲገዙዋቸው እንደኖሩ ይታወሳል። ከዚህ ዓይነት መንግሥታዊ ፖሊሲ፥





ሥርዓትና ሰነድ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦችን፥ ቋንቋዎችን፥ ሃይማኖቶችንና ባህሎችን ታሪክ ማጥናትና ማወቅ ምን ያህል አስቸጋሪ ሥራ እንደሚሆን ለማንም አስተዋይ የታሪክ ጸሐፊ፥ አንባቢ፥ ተማሪና አስተማሪ ግልጽ ነገር ነው።

ሁለተኛ፥ በ17ኛው ምዕተ ዓመት የጀርመኑ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ምሁር ዶክተር ሉዶልፍ በአገሩ ሆኖ በኢትዮጵያ አዋማዊ፥ ኦሬታዊና እስላማዊ ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ጥላቻ ከታወቁና ኢየሱሳውያን ከተሰኙ የካቶሊክ ሚሲዮናውያንና ከአንድ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ተከታያቸው ያገኛቸውን የፖለቲካ፥ የጠርነት፥ የሃይማኖት፥ የቋንቋ መረጃዎች አገናዝቦ በኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ስም የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ኃይሎችን ተረትና ታሪክ አስመልክቶ ባካሄደው ጅምር ጥናት በኢትዮጵያ ነባር አዋማዊ፥ ኦሬታዊና እስላማዊ ሕዝቦችና በሰለሞናዊ ነገሥታት መካከል ለምዕተ ዓመታት የነበረውን የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የመሬት ጠርነት ከክርስቲያን ነገሥታቱ አኳያ በኅብረ ቀለም ቀርጾ በአውሮፓ የክርስቲያን ዓለም አሰራጨ።

በ1681 የኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ ብሎ ባዘጋጀው መጽሐፍ ዶክተር ሉዶልፍ የኢትዮጵያ አዋማዊ፥ ኦሬታዊና እስላማዊ ሕዝቦችንና ሃይማኖቶችን በገዛ አገራቸው ለሰለሞናውያን የክርስቲያን መንግሥትና ሃይማኖት ታሪካዊ ጠላቶች እንደሆኑ አድርጎ ይከሳቸዋል። በተጨማሪም የጀርመኑ ጸሐፊ በተጠቀሰው መጽሐፍ ለሰለሞናዊ ነገሥታት የኢትዮጵያ እስላሞችንና የኦሮሞ አዋማዊ ማኅበረሰቦችን በተለይ ለመግዛት የአውሮፓ ክርስትያን መንግሥታት የጠብመንጃ፥ የፖለቲካና የትምህርት እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው የዓለም ገበያና ግዛት ለሚፈልጉ አውሮፓውያን ገና በዘመኑ አስተምሮዋቸዋል። ዶክተር ሉዶልፍ እንዳለውም በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሰለሞናዊ ነገሥታትና የጦር አበጋዞች በአውሮፓውያኑ ትምህርትና ጠብ መንጃ የኢትዮጵያ እስላማዊና አዋማዊ ሕዝቦችንና ሃይማኖቶችን እንደ ገዙዋቸው ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል።

ሶስተኛ፥ በ19ኛውና በ20ኛው ምዕተ ዓመታት የአውሮፓ የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ ምሁራን በአህጉራቸው ታላላቅ የባህልና የትምህርት ከተሞች፥ ማዕከላትና ተቋማት በኢትዮጵያ ስም ከአገሪቱ አራት የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች ያንዱን ብቻ ማለትም የሴም ቋንቋዎችን ብቻ መርጠው የሚያስተምሩባቸውን የጥናት ክፍሎች መሥርተው የኢትዮጵያን ጥንታዊ መንግሥት፥ ሥልጣኔና ታሪክ በአፍሪካ ምድር ላይ የፈጠሩ ከመካከለኛው ምስራቅና ከአረቢያ የገቡ የአይሁድና የአረብ ነገዶች ናቸው የሚል መላምታቸውን እስከ 1974

የሰለሞናውያን ዘውድና የገዥ መደብ ውድቀት ድረስ ሙያቸው አድርገው ሲሰብኩ ኖሩ። በሌላ በኩል እነዚህ የምዕራቡ ሴሚቲስት የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ምሁራን የአገሪቱን አኖማዊና እስላማዊ ሕዝቦችንና ሃይማኖቶችን ታሪክ ከኩሻዊ፥ ናይሎቲካዊና ኦሞአዊ ሕዝቦችና ቋንቋዎች ጋር ወደ ተጠቀሱት የጥናት ክፍሎች እንዳይገባ አድርገዋል።

ስለሆነም አሁን በድህረ አብዮት በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል በዘር፥ በጎሳ፥ በቋንቋ፥ በፖለቲካ፥ በሃይማኖት፥ በቀለም፥ በባህል፥ በሥፍራና በጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ የአገሪቱን በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪክ በአዲስና በሁለአቀፍ የጥናት ሥልትና ሚዛን ለኅብረተሰቡ በሚገባ መንገድና ቋንቋ እንደገና ማጥናት፥ መጻፍና ማስተማር ለሁሉም ያገር ዜጋ ባለሙያዎች መብትም ግዴታም ነው።

በዚህ የእውቀትና የእውነት ግንዛቤና ግዴታ ነው ይህ የኢትዮ ጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች የተሰኘ ሁለአቀፍ ጥናት ባገርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ የታሪኩ ሉአላዊ ባለቤት ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገልግሎትና ጥቅም እንዲሆን የቀረበው።

በዚህ ረገድና ተግባር በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት በሰፋትና በዝርዝር ተደጋግሞ እንደተገለጸው፥ የኢትዮጵያን ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ከውጭና ከአገር ውስጥ ክርስቲያን አስተማሪዎችና ጸሐፊዎች ሃይማኖትዊ ተጽዕኖ በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ነፃ ያወጡት ከዘመናዊ የፓሌንቶአሎጂና የሊንጉዊስቲክስ መረጃዎች ጋር የደአማት- አክሱምና የአረብ ጥንታዊ ጸሐፊዎችና ሰነዶች ናቸው።

የተጠቀሱ የውጭና የአገር ውስጥ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪዎች በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ላይ ሃይማኖታዊ ተጽዕኖ ያሳደሩት ታሪኩን በመጽሐፍ ቅዱስ ከይሁዳውያኑ የፍጥረትና የሰው ዘር መነሻና ስርጭት ትምህርት ጋር በቅርብና በጥብቅ በማያያዝ ነው።

ነገር ግን በሳይንሳዊ የኢቮሉሽን፥ የፓሌንቶሎጂና የሊንጉዊስቲክስ መረጃ ግኝትና ትምህርት መሠረት የሰው ልጅ ታሪካዊ መነሻ፥ ክስተትና ስርጭት የጀመረው ከዛሬ ሶስትና አራት ሚሊዮን ዓመታት በፊት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በኢትዮጵያ የአዋሽ-ኦሞ ወንዞች ክልል ነው። በሊንጉዊስቲክስ መረጃና ትምህርት መሠረት ደግሞ፥ የዛሬ ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ የዓለም ሕዝቦች በፍልሳና በሰፈራ





እንቅስቃሴ ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ቀይ ባሕር ተሻግረው በአረቢያና በመካከለኛው ምስራቅ የተገኙ ከዛሬ ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት በፊት በዘመነ-ታሪክ ዋዜማ ነው። በመሆኑም በዓመተ ዓለም በመጀመሪያ ሚሊኒየም (1000-500) የኢትዮጵያን ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩ ከመካከለኛው ምስራቅና ከአረቢያ የገቡ ሴማዊ የአይሁድና የአረብ ነገዶች ናቸው የሚለው ተዛማጅ የግብፅ፥ የአውሮፓና የኢትዮጵያ ክርስትያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነጽሑፍ አስተማሪዎች ትምህርት ጥሩ ተረት ብቻ ነው።

በሌላ በኩል በዓመተ ዓለም በግምት ከ500 እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1050 ዓመታት በኢትዮጵያ፥ በአረቢያ፥ በሱዳንና በግብፅ አጎራባች አገሮች በደአማት፥ በሳባ፥ በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው በተገኙና በ20ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ በደቹና በሉክሰበርጉ የጥንታዊ ጽሑፎችና ታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰሮች ድሬዊስና ሽናይደር በተተረጎሙ የደአማት-አክሱም ጽሑፎች መሠረት፥ የግዕዝ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ጨምሮ የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ በደአማት-የሀ ደጋአምባ ምድር የተፈጠረው በአገሪቱ ሉአላዊ የደአማት-አክሱም ሕዝብ ነው።

በተጠቀሱ የደአማት-አክሱም ጥንታዊ ጽሑፎች መረጃና ትምህርት መሠረት፥ በ330 ዓመተ ምህረት መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስቲያን ሃይማኖት ወደ አክሱም ከመግባቱና ቀጥሎም በ5ኛው ምዓ በዘጠኙ ቅዱሳን መጽሐፍ ቅዱስ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ከመተርጎሙ በፊት በአኖማዊው የደአማት-አክሱም ምድርና ቤተ መንግሥት የአይሁዳውያኑ የአሪት ሃይማኖት አልተገኘም። በተጨማሪም ሰነዶቹ በዘመነ-ክርስትና በመጀመሪያ 6 ምዕተ ዓለም የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በአጎራባች የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አካባቢዎች ዓለም አቀፋዊ ኃይልና ሥርዓት ሆኖ እንደተስፋፋ ጨምረው ያስተምራሉ።

## የእስልምና መነሻና ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ

ከህልውናውም ከባህልም አኳያ በአካባቢም በዓለምም ላይ የኢትዮጵያን በሀውርታዊ ኅብረተሰብና ታሪክ አንድ ልዩና አስገራሚ ሥርዓት ያደረጉት ሶስት ማኅበፊዊ ኃይሎች ከ330 እስከ 615 ድረስ በ285 ዓመታት ከመካከለኛው ምስራቅና ከአረቢያ በግሪክ ሮማውያንና በአረብ አስተማሪዎች አማካይነት ወደ አገር ውስጥ ገብ ተው በየፊናቸው የመንግሥትና የአገር ሃይማኖቶች የሆኑ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና፥ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ናቸው። ከሶስቱ የዓለም ሃይማኖቶች የእስልምና ሃይማኖት በክስተቱም በእድገቱም በውጤቱም

ከኢትዮጵያ የአክሱም መንግሥት ሥልጣኔና ታሪክ ጋር የቀረበ ታሪካዊ ግንኙነት ያለው ማኅበራዊ ኃይልና እንቅስቃሴ ነው። ይህን የኢትዮጵያና የእስልምና ሃይማኖት ታሪካዊ ግንኙነት በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት የሰነድ መረጃ ባልተገኘበት ዘመን (550-1300) ለትውልድና ለዓለም በአረብኛ ቋንቋ ጽፈው ያሳወቁ ባለውለታዎች የጥንቱ የአረብ ታሪክ ምሁራንና ጸሐፊዎች ናቸው።

በተጠቀሱ የአረብ ምሁራን ዘገባ መሠረት፥ የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በሁለት በተለያዩ ጊዜያት፥ በሮችና አካባቢዎች ነው። ከሁሉ በፊት ከእስልምና ክስተት ዋዜማ ጀምሮ በ575 ከየመን ደቡብ አረቢያ በፋርሳውያን የተባረሩ ብዙ የኢትዮጵያ ሰፋሪዎች ከ575 እስከ 661 ደረስ ለዘጠኝ አሥርታት በሰሜን ምዕራብ አረቢያ በሂጃዝ መካ ማለትም በዛሬው ሳውዲ አረቢያ ከነባር አረቦች ጋር በሥፍራ፥ በቋንቋ፥ በኢኮኖሚና በባህል ተቀላቅለው ይኖሩ እንደነበር ከታሪክ መረጃና ትምህርት ተረጋግጧል።

በ610-615 ነቢዩ ሙሐመድ መለኮታዊና አህዳዊ የእስልምናን ሃይማኖት በመካ ከተማ በሰበከ ጊዜ ለመጀመሪያ ትምህርቱን አምነው የተከተሉት በመካ ጥቂት የቁረይሽ አረብ ነገድና የኢትዮጵያ ተወላጆች እንደሆኑ የመጀመሪያ የአረብ ሙስሊም ታሪክ ጸሐፊዎች አረጋግጠዋል። በ615-616 በነቢዩ ሙሐመድ ትዕዛዝ ወደ አክሱም ከተሰደዱ የመጀመሪያ የኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች አምስት ሴቶች ጨምሮ ሀያ አንድ ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ የተጠቀሱ የአረብ ጸሐፊዎች ጨምረው አስተውሰዋል።

በአክሱም አረቦቹ ነጃሺ ማለትም ንጉሥ ብለው በሚጠሩት በአፄ አስሓማ የሚመራ የኢትዮጵያ መንግሥት ለእስልምና ሃይማኖት በቁረይሽ ተፃራሪ ኃይሎች ላይ በይፋ የመጀመሪያ ዓለማቀፋዊ እውቅናና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ሰጠ። ባጭሩ ከ610 እስከ 661 ድረስ የኢትዮጵያ ዜጎችና መንግሥት ከአምስቱ የቁረይሽ አረብ የእስልምና ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ መሥራች መሪዎች ነቢዩ ሙሐመድ፥ አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑስማንና ዓሊ ጎን በልዩ ልዩ መንገዶችና መሣሪያዎች ተሰልፈው በመካ፥ በአክሱም፥ በመዲና፥ በኢራቅ፥ በፋርስ፥ በፍልስጤም፥ በአርመን፥ በሶሪያና በግብፅ ለሃይማኖቱ ዓለማቀፋዊ ዕድገትና ስርጭት ታሪካዊ ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ እንዳደረጉ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች ለትውልድና ለታሪክ አስታውቀዋል።

በግምት ከ632 እስከ 700 ድረስ በሰባት አሥርታት እስላማዊ የአረብ ዓለማቀፋዊ ኃይልና እንቅስቃሴ በመካከለኛው ምስራቅ፥





በግብፅና በሰሜን አፍሪካ ጥንታዊ የፋርስና የሮም ዓለማቀፋዊ መንግሥታትንና ሥልጣኔዎችን በወታደራዊ የምድር ላይ ዘመቻ በሚቆጣጠሩበት ዘመን የቀይ ባሕር ደሴቶች፥ ወደቦችና ጠረፎች ገና በኢትዮጵያ መንግሥትና የባሕር ኃይል ቁጥጥር ሥር ነበሩ። ከእነዚህ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የጠረፍ ሥፍራዎች በየጊዜው ከኢትዮጵያውያን የባሕር ላይ ወንበዴዎች በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ ላይ የሚሰነዘረውን የዘረፋና የጥቃት አደጋ ከሥር ከምንጩ ለማስቀረት ከደማስቆ ሶሪያ ማዕከላቸው የአረብ ኡመያድ ባለሥልጣኖች በ700ዎቹ አካባቢ በአንድ በኩል በቀይ ባሕር የዳህላክን ደሴት በሰፋሪ ጦር በቀጥታ ያዙ። በሌላ በኩል ደግሞ ባሕሩን ተሻግረው የኢትዮጵያን የአዱሊስ ወደብ ከተማን ደመሰሱ።

በዚህ አዲስ የቀይ ባሕር ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታና ሂደት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ጠረፎችና ደሴቶች ሱዋኪንን ዜይላን በርበራንና ሞቃዲሾን ጨምሮ የአረብና የፋርስ ሙስሊም ሰፋሪዎች ብዙ እስላማዊ የንግድ፥ የሃይማኖትና የባህል ማዕከላትን፥ ወደቦችንና ከተሞችን ቆረቆሩ። እነዚህ እስላማዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የጠረፍ ወደቦችና ከተሞች ከውጭ የአረብ ሙስሊም ሃይማኖት፥ ባህልና ሥልጣኔ ወደ ክፍለ አህጉሩ መሀል አካባቢዎች የሚገቡባቸው ታሪካዊና ባህላዊ በሮችና መንገዶች ሆነው መላ ኢትዮጵያን ያገለግላሉ።

በዚህ ረገድና ተግባር ከሂጃዝ አረቢያ በአረብ ሙስሊም አስተማሪዎችና ነጋዴዎች አማካይነት በታላቁ የዜይላ በርና መንገድ የእስላም ሃይማኖት፥ ባህልና ሥልጣኔ በክፍለ አህጉሩ መሀል ደቡብ ወደ ጥንታዊና አጎራባች የሐርላና የሀዲያ ሴማዊና ኩሻዊ አገሮች ለመጀመሪያ ጊዜ እንደገቡ ብሎም ከ896 ጀምሮ በሐርላ ሴማዊ ምድር "ሸዋ" የተሰኘው የኢትዮጵያ የመጀመሪያው እስላማዊ ሱልጣኔት (መንግሥት) እንደተነሳ በኢጣሊያዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪ በዶክተር ቼሩሊ በ1936 ከሐረር ከተማ በተገኘው የአረብ ጥንታዊ ሰነድ ተገልጿል። ሁለቱም የሸዋ ቀዳሚ ሱልጣኔት (896-1285) እና ቀጣዩና ወራሹ የይፋት-ዋላስማ ሱልጣኔት (1285-1577) በሐርላ ምድርና አገር ከመካ ቁረይሽ ነገድ በቅደም ተከተል በማኽዙማዊና በሃሺማይት ጎሳ ተወላጅ ሰፋሪዎች እንደተመሰረቱ፣በዚህ ጥናት አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ተገልጿል።

በደቡብ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ እስላም ሕዝቦችና መንግሥታት ታሪክ ላይ ከ896 እስከ 1543 ድረስ ማለትም ከሸዋ ሱልጣኔት ክስተት እስከ ኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ (ግራኙ)

የ1524-1543 አመጽ ድረስ የተጻፉ አራት ቁልፍና ወሳኝ የአረብኛ ቋንቋ ሰነዶች፤

(1) በ1936 ከሐረር ከተማ የተገኘው የሸዋ ማኽዙሚ ሥርወ መንግሥትና ሱልጣኔት ታሪክ፤ (2) ከአንድ ኢትዮጵያዊ የዜይላ-ይፋቱ የሕግ ምሁር ሼክ ጀማሉዲን አብደላህ በግብፅ በተሰጠው ዝርዝር መረጃ መሠረት፣ የኢትዮጵያ ሰባቱን የይፋት፣ የደዋሮ፣ የአርባቢኒ፣ የሀዲያ፣ የሸርካ፣ የባሌና የደራ ሕዝቦችና ሱልጣኔቶች ታሪክ በሚመለከት በ1330ዎቹ በግብፁ አስተዋይ ምሁር ኢብን ፋድል አልዑመሪ የተጻፈው ታሪካዊ መጽሐፍ፤ (3) በ1430ዎቹ የይፋትን የሃሸማይት-ዋላስማ ሥርወ መንግሥትና ታሪክ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ረጅም የክርስቲያን አፄዎችንና የሙስሊም ሱልጣኖችን የመሬት፣ የንግድና የኃይል ሚዛን ጦርነት በሚመለከት "የሙስሊም ነገሥታት በሀበሻ" በሚል ርዕስ በአንድ ሌላ የግብፅ ታሪክ ጸሐፊ ማክሪዚ የተጻፈው መጽሐፍና (4) በ1530ዎቹ በኢትዮ የመኑ ተወላጅና የሕግ ምሁር ሽሃብዲን አሕመድ ቢን አብድልቃድር (አረብ ፋቂህ) የተጻፈው ታላቁ የኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም ዜና መዋዕል ናቸው። ከእነዚህ ውድና ብርቅ የታሪክ ሰነዶች የሸዋ ሱልጣኔት ታሪክና አስገራሚው የኢማም አሕመድ ዜና መዋዕል ለምዕተ ዓመታት ተጠብቀው የተገኙት ከሐረሪ ከተሜ መንግሥት ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር ከኢትዮጵያ ረጅምና ውስብስብ የእስላም መንግሥታዊ ታሪክ አኳያ በተለይ፣ ከኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪክ አኳያ በአጠቃላይ በምስራቅ ኢትዮጵያ ደጋአምባም አገር ሴማዊ፣ እስላማዊ፣ ጥንታዊ፣ ስልጡንና አናሳ የሐረሪ ሕዝብና ከተሜ መንግሥት (ኤሚሬት) ራሳቸው በራሳቸው አንድ ሕያውና አንጸባራቂ የታሪክ ምንጭ፣ መረጃ፣ ማስረጃና ሐውልት ናቸው።

በኢትዮጵያ ታሪክ የዚህን የሐረሪ ሕዝብና ኤሚሬት ታሪካዊ መነሻና ልዩ ሚና አስመልክቶ ደራሲው ካሁን በፊት የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በተሰኘው ጥናቱ አጠቃሎ እንዳ ስቀመጠው፣

*እስከ ዛሬ ድረስ በተጠቀሱ የሸዋ ማኽዙማዊና የይፋት ዋላስማ ተከታታይ ሥርወ መንግሥታት ሰነዶችና በአካባቢው የትውፊት መረጃዎች ላይ የተደረጉ ምሁራዊ የምርምር ጥናቶችና አስተያየቶች እንደሚያመለክቱት፣ በግምት ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ ከአረቢያ በአመዛኙ በኤደን ባሕረሰላጤ-በዜይላ በር በግልና በቡድን በገፍ እስላማዊ ነጋዴዎችና የሃይማኖት ሰባኪዎች ትምህርት በአፍሪካ ቀንድ በተለይ በኤደን ባሕረሰላጤና በዓባይ-ጊቤ መካከል በብዙ የአካባቢ ሱልጣኔቶች ወይም እስላማዊ መንግሥታት የተደራጁ ብዙ*





*ነባርና ተዛማጅ ሕዝቦች በዘር ኩሻዊና ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች ነበሩ።*

*ከእነዚህ በማኽዙማዊ ሥርወ መንግሥትና ሱልጣኖች ሰነድ ላይ የተካሄደው የዶክተር ኢንሪኮ ቼሩሊ ጥናት እንደሚያመለክተው፣ የሸዋ ሱልጣኔት ቋንቋ የኢትዮጵያ ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ ክፍል ማለትም ከኢትዮጵያ የግዕዝ፣ የትግረ፣ የትግሬ፣ የአማራ፣ የጋፋት፣ የጉራጌ፣ የአርጎባና የሐረሪ ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር ተመሳሳይ ነው።*

*በዚህ አኳያ በአካባቢው ከተጠቀሱ ሱልጣኔቶች በተለይ ከ896 እስከ 1577 ድረስ በሰባት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የሸዋ፣ የይፋት፣ የአዳልና የሐረር ሕዝቦች ሥርወ መንግሥታትና ሱልጣኔቶች በተለይ በኤደን ባሕረሰላጤና በአዋሽ ጨርጨር መካከል በአንድ በተወሰነ የመሬት ክልል በጊዜ፣ በሥርዓት፣ በኢኮኖሚ፣ በሃይማኖትና በባህል እርስበርሳቸው እንዴት በቅርብ እንደተያያዙና እንደተወራረሱ በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት ታይቷል። በተጨማሪም በዚህ ጥናት በሐረር ታሪካዊ ግምብ ውስጥ የአደሬ ሴማዊ የቋንቋ ማኅበረሰብ በሥፍራና በጊዜ በሃይማኖትና በባህል የጥንታዊ ሸዋ፣ ይፋት፣ አዳልና ሐረር ሱልጣኔቶች ተከታይና ወራሽ እንደሆነ ከሰነድ መረጃ ታውቋል።*

*(ከገጽ152-53)*

# ክፍል ሁለት

# የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ

## 1. የታሪክ መረጃ፣ ትርጉምና ትምህርት

### የቅድመ ታሪክና የዘመነ ታሪክ ልዩነትና ግንኙነት

በኢትዮጵያውያን *ታሪክ* በጥንቱ ግሪኮች *ኢስቶሪ*፣ በዘመናዊ አውሮፓውያኖች *ሂስትሪ* ተብሎ የሚታወቀው መሠረተ ሀሳብና ትምህርት ሁለት ተዛማጅነት ያላቸው ትርጉሞችን ያዘለ ፅንሰ ሀሳብ ነው። በአንደኛው ትርጉሙ *የሰው ልጅ ያለፈው ዘመን ሥራ* አጠቃላይ ትምህርት ነው። በሌላ ትርጉሙ ደግሞ *የሰው ልጅ የዚያ ያለፈው ዘመን ሥራ በመረጃ መሰፈርትና ሚዛን በሥፍራና በጊዜ ቀመር የሚታወቅበት ሥልተ ትምህርት ወይም የምርምር ዘዴ ነው።*

ከሁሉ በፊት የተፈጥሮን፣ የሰውን፣ የአእምሮን፣ የዕውቀትን፣ የባህልንና የማኅበራዊ ሥርዓትን ተዛማጅ መነሻ፣ መስተጋብርና መወራረስ በሚመለከት የሰው ልጅ ማዕከላዊ ተግባርና ሚና በትክክል መታወቅ ይኖርበታል። ከዚህ አኳያ የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን በራሱ ማህበራዊ የአእምሮ መሣሪያ በተወሰነ የሥፍራና የጊዜ ቀመር ውስጥ የሚያውቅና የሚለውጥ፣ በማህበራዊ ሥራው ራሱንና ባህሉን የሚፈጥር አንድ ልዩ አካል ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጅ ዘመን፣ ማህበራዊ ሥራና ባህል *ቅድመ-ታሪክና ዘመኑ-ታሪክ*[1] ተብሎ በሁለት ክፍለ ዘመናት ይከፈላል። የሁለቱ ክፍለ ዘመናት መለያ የታሪክ መረጃ ነው። በመሆኑም የታሪክ መረጃ የሰው ልጅ የሥራ አሻራ ነው። ቅድመ-ታሪክ የሰው ልጅን የዕድሜ ዘመን፣ ሥራ፣ ሕይወትና ባህል በትክክል ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ሰብአዊ የድርጅት፣ የምርት፣ የባህል፣ የቅርጽ፣ የጽሑፍ፣ የቋንቋ፣ የትውፊት ምልክቶች እና አሻራዎች፣ መሣሪያዎችና ፣መረጃዎች የማይገኙበት የጨለማ ክፍለ ዘመን ነው ለማለት ይቻላል።

*ዘመኑ-ታሪክ* ደግሞ በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጅን የማህበራዊ አኗኗር ዘዴና ሥርዓት በሥፍራና በጊዜ ቀመር ውስጥ በተግባር

[1] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፣ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ (አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት 1982) ገፅ 17-20።

መስፈርት ለይቶ ለማወቅ የሚረዱ ሰብአዊ የባህል፥ የምርት፥ የቅርጽ፥ የጽሑፍ፥ የቋንቋ፥ የትውፊት ምልክቶችና አሻራዎች፥ መሣሪያዎችና መረጃዎች የሚገኙበት የዕውቀትና የትምህርት ክፍለ ዘመን ነው።

## የታሪክ መረጃ ዓይነቶች

ዛሬ በዓለማችን ዘመናዊ የሳይንስ ጥበብና የአሠራር ዘዴ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ መሠረታዊ የታሪክ መረጃ ዓይነቶችና ምንጮች በአራት ተዛማጅ ዘርፎች ይመደባሉ። እነርሱም፦

1) የፖሌአንቶሎጂ (Paleontology) ማለትም ሰብአዊ የአጥንትና የድንጋይ መረጃ፤
2) የሰነድ (የጽሑፍ፥ የቅርፅ፥ የሥዕል) መረጃ፤
3) የሊንጉዊስቲክስ ማለትም የሥነልሳን (የቋንቋ ሳይንስ) መረጃ፤
4) የትውፊት (የኪነቃል፥ የአፈታሪክ) መረጃ ናቸው።

## የኢትዮጵያ የፖሌአንቶሎጂ መረጃ

ባጭርና በጥቅል ለማስቀመጥ፥ ታሪክ የሰው ልጅን የያለፈ ዘመን ሥራ፥ ሕይወትና ባህል በሚመለከት ከተጨባጭ የሥራ መረጃ በመነሳት የእንስሳት እርባታ፥ የእርሻ፥ የገጠር፥ የከተማ፥ የንግድና የዕደጥበብ ተግባራትን የሳይንስና የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችንና ምርቶችን ጨምሮ በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመር ውስጥ የኅብረተሰብን ማህበራዊ ድርጅትና ሥርዓት፥ የሥራ ዓይነት፥ ብዛትና ክፍፍል የሚገልፅ አንድ ልዩ ማህበራዊ ሳይንስ ወይም ጥበብ ነው። በሌላ ባሕሪው ደግሞ ታሪክ አንድ የማህበራዊ ትምህርት ዘዴ፥ የዕውቀትና የጥበብ መክፈቻ ነው። በሌላ ቃል የታሪክ መነሻውና ምንጩ በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመር ውስጥ በተጨባጭ መረጃ በትክክል የሚገለፅ ተጨባጭ የሰው ሥራ ነው። በመሆኑም ማንኛውም በታሪክ መረጃ በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመርና መስፈርት የማይታወቅና የማይገለፅ የሰው ልጅ ሥራና ሕይወት የማይጨበጥ ተረት ነው።

ከታሪክ መረጃ አኳያ፥ የቅድመ-ታሪክ የመታወቂያ ገፅታዎች በዘመናዊ የአርኪኦሎጂ ሳይንስ ከከርሰ ምድር በቁፋሮ የሚገኙ ሰብአዊና ጥንታዊ የአጥንትና የድንጋይ መሣሪያዎች ማለትም የፖሌአንቶሎጂ መረጃዎች በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመር ውስጥ እንደሚያስረዱት፥ በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ በአካልና በአእምሮ ዳብሮ የተከሰተው ከዛሬ አራትና አምስት ሚሊዮን ዓመታት በፊት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በታላቁ





የስምጥ ሸለቆ[2] ውስጥ ነው። እንዲያውም ከሀዳር፥ ከመልካ ቁንጥሬና ከኦሞ ፖሌአንቶሎጂያዊ ሥፍራዎች በቁፋሮ የተገኙ ሰብዓዊና ጥንታዊ የአጥንትና የድንጋይ መረጃዎች በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀመር ውስጥ እንደሚያረጋግጡት፥ በክፍለ አህጉሩ የሰው ልጅ ምንጭና መነሻ የሆነው ሥፍራ በሁለት የተራራ ሰንሰለቶች መካከል የኢትዮጵያ የአዋሽ-ኦሞ ወንዞች[3] ለም፥ ውሃማና ሜዳማ ምድር ነው።

ሠንጠረዥ 4

የኢትዮጵያ የፖሌአንቶሎጂና የአርኪኦሎጂ መረጃዎች ግኝት

| መረጃው የተገኘበት ሥፍራ | የመረጃው ዕድሜ በዓመት | የግኝቱ ዘመን |
|---|---|---|
| 1.የሀዳር ሰው አጽም | ከ4,000,000 ዓመት በላይ | 1973 |
| 2.የኦሞ ሰው አጽምና የድንጋይ መሣሪያ | ከ2,000,000 ዓመት በላይ | 1967-1968 |
| 3. የመልካ ቁንጥሬ ሰውና የድንጋይ መሣሪያ | ከ1,500,000 ዓመት በላይ | 1965-1976 |
| 4.የሊጋአዳ ዋሻ እንስሳት ሥዕል | 4,000 ዓመት | 1970-1978 |
| 5.የሻቤ ዋሻ እንስሳት ሥዕል | 3,000 ዓመት | በ1920ዎቹ |
| 6.የሸዋ፥ የአርሲ፥ የሐረር፥ የሲዳሞ ትክል ድንጋይ ሐውልቶች | የብዙ ሺህ ዓመታት | በ1920ዎቹ |
| 7.የደአማት-አክሱም የድንጋይ ላይ ጽሑፎች | 2,500 ዓመታት | 1959-1973 |

Source: UNESCO, History of Africa I; R. Jousssaume, Megalithisme du Harar (1974); Annales d'Ethiopie (AE), Vols. 3, 5, 6, 7, 9, 12.

## የኢትዮጵያ ታሪክ የሰነድ መረጃ

### *የጥንት-ኢትዮጵያ ታሪካዊ ክስተትና ዕድገት*

ማኅበራዊ የሥራ ዓይነት፥ ክፍፍልና ድርጅት፥ የቅርጽና የጽሑፍ መረጃዎች የዘመንና የያልጣን መለኪያ መስፈርቶችና መግለጫዎች ናቸው በተባለው መሠረትና ሚዛን፥ በዘመነ ታሪክ ከዛሬ ዘጠኝ - አሥር ሺህ[4] ዓመታት በፊት የሰው ልጆች በሰፈራ፥ በእርሻ፥ በንግድ፥ በቤት፥ በከተማ ተግባራትና ድርጅቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግሥትና የሥልጣኔ ሥራዎችንና ሥርዓቶችን ከጀመሩባቸው ታሪካዊ ሥፍራዎች አንዱ በአፍሪካ አህጉር፥ በታችኛው የዓባይ ወንዝ ሸለቆ የሚገኘው የጥንቱ ፈርኦናዊ ግብፅ እንደሆነ ከ1799[5] ጀምሮ ባለፉት 200 ዓመታት

---

[2] UNESCO, General History of Africa I; Methedology and African Prehistory (1981), I, pp. 300-301.

[3] Ibid., pp. 412-419, 438-448.

[4] General History of Africa, II.

[5] M. F. Unger, The New Unger's Bible Handbook, (Chicago: Moody Press, 1984), p. 66.

በአርኪኦሎጂ ሳይንስ ከከርሰ ምድር በቁፋሮ ከተገኙ ጥንታዊ የሃይሮ ግላፊክስ ቋንቋና ጽሑፎች በስፍራና በጊዜ መስፈርት ተረጋግጧል።

በጥንታዊ ግብፅና በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በፑንት-ኢትዮጵያ መካከል በንግድ፣ በባህልና በሃይማኖት መስኮችና ዘርፎች ከ2800 እስከ 1000 ዓመተ ዓለም ድረስ ለ1800 ዓመታት የቆየ የመስተጋብርና የመወራረስ ሥርዓትና ሂደት እንደነበር ከተጠቀሱ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ መረጃዎች ታውቋል።

ከታሪክ መረጃና ከኅብረተሰብ ዕድገት አኳያ፣ በ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ የግብፅና የፑንት ጥንታዊ ግንኙነት በትክክል ባልታወቁ ምክንያቶች ከተቋረጠ በኋላ፣ በግምት ከ1000 እስከ 500 ዓመተ ዓለም ባለው ዘመን ውስጥ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ የኢትዮጵያ የደአማት[6] ዘውዳዊ መንግሥት በአጎራባቹ ደቡብ አረቢያ ደግሞ በዕጣን፣ በሙጫ፣ በከርቤና በቀረፋ ቅመማ ቅመም ምርትና ዓለም አቀፍ ንግድ የተሰማሩና ሚናደ፣ ሳባ፣ ቀጣባንና ሃድራማዊ የተባሉ አናሳ የአረብ መንግሥታት በየፊናቸው እንደ ተከሰቱ ከታሪክ መረጃ እና ጥናት ይታወቃል።[7]

ምንም እንኳን በዓመተ ዓለም፣ በአምስተኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በደጋማው ክልል በዘውዳዊ ሥርዓት ተደራጅቶ በሰነዳዊ መረጃ በታወቀው በደአማታ ውያን መንግሥትና በጥንታዊ ፑንት መካከል በሥፍራ፣ በጊዜ፣ በቋንቋና በባህል የነበረውን ግንኙነት የሚያስረዳ ተጨባጭ ታሪካዊ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ ባይገኝም በሚከተሉት አያሌ የውስጥና የውጭ ተዛማጅ ምክንያቶችና ማስረጃዎች ሁለቱም የፑንትና የደአማት ሕዝቦች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ባንድ አካባቢ የአንዱ አዳጊ የዘውድ ሥርዓት ተከታታይ የዕድገት ደረጃዎችና ምዕራፎች እንደሆኑ መገመት ይቻላል። ምክንያቱም፤

አንደኛ፣ ከሁሉ በፊት ጥንታዊ የፑንትና የደአማት አገሮች በቅደም ተከተል የተገኙበት የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር አንድ አካባቢ ነው።

ሁለተኛ፣ ከዘመነ ፑንት እስከ ዘመነ ደአማት ድረስ በአካባቢው የፑንት-ኢትዮጵያን ጥንታዊ የመንግሥት ዕድገት እንቅስቃሴና

[6] A. J. Drewes, Inscriptions de L'Ethiopie Antique, (Leiden: Brill, 1962); Roger Scheinder, "Les Debuts de L'Histoire Ethiopienne", Documents Histoire Civilisation Ethiopienne, RCP 230, CNRS, FASC. 7 (1976).

[7] J. Doresse, Histoire Sommaire de la Corne Orientale de L'Afrique, (Paris, 1971), pp. 49, 58, 66, 84; "History of Arabia", The New Encyclopaedia Britanica, Vol. 1, pp. 1043-44; ላጵሶ ጌ ድሌቦ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ ገፅ 28-29።





አቅጣጫ የሚያደናቅፍ ውጫዊ ግፊት ሆነ ውስጣዊ ተፅዕኖ መከሰቱን የሚያሳይ ምንም ዓይነት ምክንያት ወይም መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም።

ሦስተኛ፣ የደአማታውያን መንግሥትና ሥልጣኔ በዓመተ ዓለም በአምስተኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታውቆ በሰነድ መረጃ የተገኘበት ወቅትና ሁኔታ የመንግሥቱ ታሪካዊ መነሻ መቼና እንዴት እንደነበር በዝርዝር ስለማያመለክትና አንድ መንግሥት በባህላዊና በማህበራዊ ዕድገት በራሱ ፊደልና ጽሕፈት በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የታወቀበት ጊዜ ገና የተፈጠረበት ዘመን ነው ተብሎ በዘልማድ ስለማይታሰብ በታላቁ የሰሜን ምስራቅ ክፍለ አህጉር ረጅም ታሪክ፣ የዘመነ ፑንት ፍጻሜና የዘመነ ደአማት መባቻ ቢያንስ ከ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ ጀምሮ እንደሆነ መገመት ከአግባብ ውጭ አይሆንም።

አራተኛ፣ በዚህ ጥናት አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ሁሉ የሚጠቀሰው ዘመናዊ የአፍሮ-እስያ ሊንጉዊስቲካዊ ጥናት ማለትም የሥነ ልሳን ወይም የቋንቋ ሳይንስ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉርና በዓባይ ሸለቆ በጥንቱ ተዛማጅ የግብፅና የፑንቱ ብሎም በዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ቋንቋዎች መካከል ለረጅም ዘመን የኖረውን የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታና ሂደት በአጠቃላይ መን ገድና መልክ ስለሚያመለክት በክፍለ አህጉሩ በፑንትና በደአማት ሕዝቦችና ቋንቋዎች መካከል ዘላቂ መስተጋብርና መወራረስ እንደ ተካሄደ መገመትም ይቻላል።

## የኢትዮጵያ ረጅም የሰነድ መረጃ ታሪክ

በአንፃራዊ አባባል በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በዓለም ላይ ለረጅም ዘመን የጽሑፍ መረጃና ታሪክ ካላቸው ጥቂት ጥንታዊ ሕዝቦች አንዱ ነው። ከአገር ውጭና በአገር ውስጥ የተገኙ የኢትዮጵያ የሰነድ መረጃዎች ከጥንቱ ፈርኦናዊ ግብፅ ማለትም በዓመተ ዓለም ከ2800 ገደማ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በ5000 ዓመታት የሚቆጠር ዘመን እንዳላቸው ከላይ ባጭርና በጥቅል ተመልክቷል።

ከሁሉ በፊት የህልውናውና የሕይወት መሠረታዊ ጥያቄን በሚመለከት ሥፍራና ጊዜ የመሆንና የመኖር ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በመሆኑም የአንድ አገርም ታሪክም በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የተካበተ ጥቅል የሥራ፣ የልምድ፣ የድርጅት፣ የትዳርና የቤተሰብ የመንግሥትና የሃይማኖት ተቋማት፣ የትምህርት፣ የዕደ ጥበብ፥ የቴክኖሎጂ የሥልተ ምርትና የሥርዓተ ማህበር፣ የባህልና

የእምነት ድምር ውጤት ነው። ስለሆነም ታሪክ የዕውቀትና የማኅበራዊ ልምዶች ክምችት፥ ምንጭና ግንዛቤ ነው ለማለት ይቻላል።

ዛሬ በዘመነ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የአንድ ሕዝብን ታሪክ በጥናት እና ምርምር ሚዛን በተወሰነ የሥፍራ፥ የጊዜና የተግባር መስፈርት በትክክል አገናዝቦ ለመማር ለማሳወቅ፥ ለመጻፍና ለማስተማር፥ ለማንም ግለሰብ ከታላቅ ትዕግሥት ጋር በቅድሚያ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮችና ቅድመ ዝግጅቶች (1) ትክክለኛ የሆነ የታሪክ መረጃ፥ (2) የታሪክ ዓይነተኛ ትምህርት፥ ሙያና ፍቅር (3) የሰውና የታሪክ ተዛማጅ ፍልስፍና ናቸው።

በመሆኑም ዛሬ በድህረ አብዮት የኢትዮጵያን ረጅምና ውስብስብ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ታሪክ ከፖለቲካና ከሃይማኖት ተፅዕኖ ነፃ በሆነ ሳይንሳዊ ምርምርና ሚዛን ከሥልተ ምርትና ሥርዓተ ማህበር አኳያ በትክክል ለማጥናት፥ ለማወቅና ለማሳወቅ ከአገር ውጭና ከአገር ውስጥ የሚያስፈልጉ የታሪክ መረጃዎች ብዙ ናቸው። ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፦

1. ከአገር ውስጥ በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1050 ዓመታት ውስጥ በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች የተጻፉ የኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እንዲሁም ከወርቅ፥ ከነሐስና ከመዳብ የተሠሩ ጥንታዊ የአክሱማውያን ገንዘቦች፤
2. ከአገር ውጭ ደግሞ በግምት ከ2800-1000 ዓዓ ድረስ በ1800 ዓመታት ውስጥ የጥንታዊ ግብፃውያን ሥዕላዊ የሃይሮግላፊክስ (Hieroglyphics) ቋንቋና ጽሑፍ መረጃዎች እንዲሁም ብዙ ጥንታዊ የግሪክ፥ የሮማውያንና የአረብ ጸሐፊዎች የቀረፁዋቸው የጽሑፍ መረጃዎች፤
3. በቅርቡ ክፍለ ዘመን በግምት ከ1270 እስከ 1855 ድረስ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች በግዕዝ ቋንቋ በብራና የተጻፉ የክብረ ነገሥት፥ የፍትሐ ነገሥት፥ የነገሥታት ዜና መዋዕሎችና የቅዱሳን ገድሎች፤
4. ከአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በየጊዜው በአውሮፓ የዲፕሎማሲ መልእክተኞች፥ ሚሲዮናውያን፥ አገር ጎብኝዎችና ተመራማሪ ምሁራን ስለ ኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ በብዙ ዘመናዊ የአውሮፓ ቋንቋዎች የተጻፉ መጻሕፍት፤
5. ከአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት (1855-1868) ጀምሮ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች፥ የሕግ መዛግብት፥ እንዲሁም የመሥርያ ቤት ሰነዶች፤
6. የትውፊትና ዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስ መረጃዎች በድምር የኢትዮጵያ መሠረታዊ የታሪክ፥ የትምህርት፥ የባህልና የእውቀት ምንጮችና መሣሪያዎች ናቸው።





## የአርኪኦሎጂ ሳይንስና የኢትዮጵያ ታሪክ ግኝት

በኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ ጉዳይ ላይ የጥንታዊ ግብፃውያንን መረጃ በሚመለከት፥ በዓመተ ዓለም ከ2800 እስከ 1000 ድረስ ለ1800 ዓመታት ገደማ በሁለቱም በባሕርና በምድር ማለትም በቀይ ባሕርና በዓባይ ሸለቆ የንግድ መስመሮች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከጥንታዊው የፑንት አገር ጋር ፈርኦናዊ የግብፅ ነገሥታትና ነጋዴዎች ለረጅም ዘመን የንግድ፥ የባህልና የሃይማኖት ግንኙነቶች እንደነበሩዋቸው የክፍለ አህጉሩንም ሕዝብ፥ እንስሳት፥ እፅዋት፥ አዝዕርት፥ የእርሻ፥ የዱርና የንግድ ምርቶችን በሥዕልና በጽሑፍ የሚገልጹ ብዙ ጥንታዊ መረጃዎችን በሃይሮግላፊክስ ቋንቋና ፊደል ቀርጸው ለትውልድና ለታሪክ አቆይተዋል።

በአገር ውስጥ ደግሞ በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1050 ዓመታት ውስጥ የተፃፉና በ500 የሚቆጠሩ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ከ1804 ጀምሮ ባለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ፥ በአረቢያ፥ በሱዳንና በግብፅ አጎራባች አገሮች ከ50 በሚበልጡ ታሪካዊ ሥፍራዎች በ30 በሚቆጠሩ ተመራማሪዎች ጥናት ከከርሰ ምድር በቁፋሮ ወጥተው አሁን በብዙ ዘመናዊ ቋንቋዎች ትርጉም የታሪክ መረጃዎች ሆነዋል።[8]

ሠንጠረዥ 5

በ522-1981 የኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ያገኙ ምሁራን፥

| ያገኘው ምሁር | የተገኘበት አገር | የጽሑፉ ቋንቋ | የጽሑፍ ብዛት | የግኝቱ ዘመን |
|---|---|---|---|---|
| 1.Cosmas | Ethiopia | GR | 1 | 522 |
| 2.Schweinfurth | Ethiopia | GE | 13 | 1894 |
| 3.C. Rossini | Ethiopia | SA, DA | 7 | 1897-1905 |
| 4.Paribeni | Ethiopia | GR | 8 | 1905 |
| 5.E. Littmann | Ethiopia | GR,SA, DA | 97 | 1906 |
| 6.Franchini | Ethiopia | SA, DA | 32 | 1953-56 |
| 7.Drewes | Ethiopia | SA, GE | 105 | 1955 |
| 8.Schneider | Ethiopia | SA, DA | 3 | 1970 |
| 9.Archaeology | Ethiopia | GE, SA, DA | 160 | 1955-81 |
| 10.25 Others | ETH;ARB;SUD., | SA, GE, GR | 51 | 1804-1981 |
| Total | | | 471 | |

SOURCE: Bernand et al, Inscriptions. GR= GreekGE= Geez DA= Daamat SA= Saba

[8] E. Bernand, A. J. Drewes, R. Schneider, et F. Anfray, trs. and eds.; Recueil des Inscriptions de L'Ethiopie Periods Pre-Axoumite et Axoumite, (Forthcoming).

ሠንጠረዥ 6
በ1893-1981 የኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎችን
የተረጎሙ ምሁራን

| ተ ቁ | የድንጋይ ላይ ጽሑፎችን ወደ ዘመናዊ ቋንቋ የተረጎሙ ምሁራን | የጽሑፍ ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | E. Littmann | 105 |
| 2 | A. J. Drewes | 103 |
| 3 | R. Schneider | 38 |
| 4 | Drewes & Schneider | 51 |
| 5 | C. Rossini | 9 |
| 6 | 10 Others | 78 |
| | Total | 384 |

SOURCE: Bernand et al, Inscriptions.

ከእነዚህ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች፥ ባለፉት አሥርታት (1955-1981) ከአጎራባች ኤርትራና ትግራይ ታሪካዊ የየሀ፥ የመጠራ፥ የከስከሴ፥ የሐውልቲ፥ የአዲቀይሀ፥ የአዲጋለሞ፥ የእንዳ ጨርቆስ፥ የዳክህናሞ፥ የዘበንሞሮሮ፥ የሰሮ፥ የሰፍራ፥ የፊቅያ ወዘተ ሥፍራዎች[9] በአርኪኦሎጂ ጥናት የተገኙና በዓመተ ዓለም ከ430 እስከ 330 ድረስ ባለው በአንድ ምዕተ ዓመት ውስጥ በሁለቱም የደአማታውያንና የሳባውያን ቋንቋዎችና ፊደሎች የተፃፉ አሥራ ሦስት የነገሥታት ዜና መዋዕሎች[10] እንዲሁም በዘመነ ክርስትና መጀመሪያ ላይ በ300 አካባቢ በአንድ የአክሱም አዋሚ ንጉሥ በግሪክ ቋንቋና ፊደል ተጽፎ በአዱሊስ ወደብ ከቆመ ሀውልት ላይ በ525 በግሪኩ-ግብፃዊ ጸሐፊ ኮስማስ ተገልብጦ በቅጅ የተገኘውና በኢትዮጵያ፥ በዓባይ ሸለቆና በአረቢያ በ30 በሚቆጠሩ አገሮች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄዱ የወረራ ጦርነቶችን የሚዘረዝር አንድ ታሪካዊ ሰነድ፥ የአፄ ነገሥታት ኢዛናና ካሌብ በግዕዝ እና በግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች የተጻፉ ዜና መዋዕሎች በአንድነት የኢትዮጵያን ጥንታዊ የመነሻ ታሪክ በሚመለከት ቁልፍና ወሳኝ የመረጃ ምንጮች ናቸው።

9 E. Littmann, Sabaische, Griechische, und Altabessinische Inschriften, Deutsche Aksum Expedition Book IV (DAE) (Berlin, 1913), Inscriptions Nos. 4-11, pp. 4-35; A. Kammerer, Essai Sur L'Histoire Antique d'Abyssinie, de Royaume d'Aksm et Ses Voisines d'Arabie et de Merce (Paris, 1926), pp. 89-97; "Christian Inscriptions of Ezana"; S. H. Sellassie, Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270 (Addis Ababa, 1972); p. 103; R. Schneider, "L'Inscription Chretienne d'Ezana en Ecriture Sudarabie", AE, Vol. 10 (1976), pp. 109-117.

10 Ibid., Schneider, "Histoire", pp. 51-54.





## 2. የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ

ከጥንታዊ ግብፃውያን፥ ግሪኮች፥ ሮማውያን፥ አረቦችና ከአገር ውስጥም በተገኙ የሃይሮግላፊክስ፥ የደአማት፥ የሳባ፥ የግሪክ፥ የግዕዝ፥ የላቲንና የአረብኛ ጽሑፎች መሠረት፥ ከጥንት አንስቶ በዘመነ ክርስቶስና እስከ መጀመሪያው አሥር ምዕተ ዓመታት ድረስ በታላቁ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በተለይ በሰሜኑና በምሥራቁ የጠረፍ ክልሎችና በደጋማው መሀል ክልል የኢትዮጵያ ተከታታይ የጥንታውያን፥ የደአማታውያን፥ የአክሱማውያንና የአገው ሕዝቦችን እና መንግሥታትን አካባቢያዊ ክስተትና ዕድገት በሚመለከት ሰነዳዊ የግንዛቤ መረጃዎችና መርሐ አሳቦች በዚህ ጥናት ለውይይት ቀርበዋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በተለይም የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን የመነሻና የማንነት ጥያቄዎች በሚመለከት ከላይ የቀረቡ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የደአማታውያን ጽሑፎች በመነሻ፥ በዓይነትና በዕድገት ደረጃ በተለያዩ ሁለት ቋንቋዎችና ሁለት የጽሕፈት ሥርዓቶች (monumental writing and cursive writing) ማለትም በቁም የጌጥና በስድ የተራ ጽሕፈት ሥርዓቶች የተጻፉ ታሪካዊ ሰነዶች ናቸው።[11]

ከሁለቱ ቋንቋዎች አንዱ ከነሥልተ ጽሕፈቱ በዘመኑ በደቡብ አረቢያ ከነበረው ከሳባ ጥንታዊ ቋንቋና የቁም ጽሕፈት ሥርዓት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነና በኢትዮጵያ በአንድ ምዕተ ዓመት (430-330 ዓመተ ዓለም) ጊዜ ውስጥ ተገኝቶ በትክክል ባልታወቀ ምክንያትና መንገድ ከአገሪቱ የጠፋ ፊደልና ጽሕፈት መሆኑን በኢትዮጵያ የዘመኑ ታሪክና ጽሕፈት ዛሬ ታዋቂና መሪ በሆኑ ፕሮፌሰር ምሁራን ድሬዌስና[12] ሽናይደር[13] ከፍተኛ የጥናት ሥራዎች ተረጋግጧል።

ሁለተኛው ቋንቋ ግን ከነሥልተ ጽሕፈቱ በዘመኑ ሆነ ከዚያም በፊት ወይም በኋላ በየትኛውም የዓለም ክፍል ያልተገኘና በዓይነት አዲስና ልዩ ከመሆኑም በላይ በዕድሜ አኳያ ከሳባውያን ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት የጊዜም ቅድሚያ ያለው የአገሩ የደአማታውያን ብሔራዊ ቋንቋና ሥርዓተ-ጽሕፈት እንደሆነ, አሁንም ከምሁራኑ ድሬዌስና ሽናይደር ጥናቶች ታውቋል።

11 Drewes, Inscriptions., pp. 71-88.

12 Ibid., pp. 6, 89, 107.

13 Schneider, "Histoire", pp. 49, 51; Ibid., "On the Evolution of the Ethiopian Writing", Lecture Text (Addis Ababa, 1982), p. 5; Ibid., "On the Daamatite State, Kings, and Gods"; Written Note to the Writer (Addis Ababa, 1982).

በተጨማሪም፣ በኋላ በዘመነ አክሱም የኢትዮጵያ የግዕዝ ቋንቋ፣ ፊደልና ጽሕፈት በታሪካዊ የዕድገት ሂደት ከዚሁ ከደአማታውያን ቋንቋ፣ ፊደልና ጽሕፈት እንደተገኘ በተጠቀሱ ከፍተኛ ምሁራን በአሳማኝ መረጃና ትንተና ተገልጿል።[14] ከእዚህ ከዘመነ ደአማት ጽሑፎች መካከል፣

1) ወአረነወተ፣ ረደአመ፣ ረበህና ለመነ የተሰኙ የአራት ነገሥታትን ስሞች፣
2) ሰመአተመአከተነ የተባለች የአንዲት ንግሥትን ስም፣
3) ነረመ፣ ጸደቀነ፣ ሸመነ፣ ረበ እና አበከወደመ ተብለው የሚታወቁ የአምስት ያገር ወለድ አዋማዊ አማልክትን ስሞች፣
4) አስተር፣ ሀወበስ፣ አለመቀሀ፣ ደተሀመየመ፣ እና ደተበአደነ ተብለው የሚጠሩ አምስት በዘመኑ በመካከለኛው ምስራቅና በአረቢያ የታወቁ የውጭ አማልክትን ስሞች የያዙ በድምሩ አሥራ ሦስት በደአማትኛ ቋንቋ የተጻፉ ታሪካዊ የደአማት ነገሥታት ዜና መዋዕሎች በተለይ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክና ጂኦ-ፖለቲካ እንዲሁም መነሻና ማንነት በተመለከተ በጣም ታላቅ ዋጋ ያላቸው መሠረታዊ ሰነዶች[15] ናቸው።

በእነዚህ የታሪክ መረጃዎች መሠረት፣ በደአማት አገርና መንግሥት ስለመመፈተረነ እና ወረዋደነ የተባሉ ሁለት ተከታታይ ሥርወ መንግሥታት ወይም የነገሥታት ወገኖች ነበሩ። ከላይ ከተጠቀሱ የደአማት ነገሥታት ወአረነወተ እና ረደአመ ከመጀመሪያው ሥርወ መንግሥት እንደሆኑ በዜና መዋዕሎቹ ተመልክቷል።[16] ይህም ሁኔታ በቅድመ አክሱም የኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማት ኅብረተሰብ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች አገርና መንግሥት እንደሆነ ያመለክታል።

በአገሩ መንግሥታዊ ሰነዶች ማለትም በነገሥታት ዜና መዋዕሎች ከደአማታውያን ብሔራዊ ቋንቋ፣ ጽሕፈትና አማልክት ጋር የውጭ አገር አማልክት፣ ቋንቋና ጽሕፈት አብሮ መገኘት የኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማት ሕዝብና መንግሥት ከአካባቢው ዓለም ጋር በተለይም በአረቢያ ከሳባውያን ጋር በንግድ፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋና በባህል የቀረበ ታሪካዊና ጂኦ-ፖለቲካዊ መስተጋብርና መወራረስ

[14] Ibid., "Ethiopian Writings".

[15] R. Schneider, "Deux Inscriptions Sudaribique du Tigre", Biblothetica Orientalist, vol. 30, Nos. 516 (1973), pp. 387-89; Anfray, "Recherches Archaelogique en Ethiopia", Academic des Inscriptions et Belles- Lettres (1978), p. 715.

[16] Ibid., "Deux Inscriptions", p. 389.





እንደነበረው በተጨባጭ ያሳያል።

በዚህ ጉዳይ እንዲያውም ከደአማት ነገሥታት አንዱ የረበህ ልጅ "ድል አድራጊው" ንጉሥ ለመነ በዜና መዋዕሉ ራሱን «የደአማታውያን፣ የሳባውያን፣ የአበራውያን የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ»፣ አገሩን ደግሞ «ከምስራቅ እስከ ምዕራብ»፣ በማለት እንዲሁም «አስተር፣ ሀወበስ፣ አለመቀሀ፣ ደተሀመየመ፣ ደተበአደአኑ»[17] የተሰኙ አዋማዊ አማልክቱን ዘርዝሮ በማሳወቅ በዘመኑ የኢትዮጵያ የዘውዳዊ መንግሥትን የሕዝቦች፣ የቋንቋዎች፣ የባህሎችና የሃይማኖቶች ብዙትና አንድነት ጥምርና በጥቅል አስረድቷል።

በዜና መዋዕሉ «የደአማታውያን፣ የሳባውያን፣ የአበራውያን፣ የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ»[18] የሚለው የንጉሥ ለመነ የዙፋን ስም የደአማት መንግሥትና ኅብረተሰብ በእርግጥ እንደዛሬው ኢትዮጵያ ከመነሻው በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች አገር እንደሆን በግልፅ ያስረዳል።

በአዲስ የጥናት ዘዴ፣ በዘመናችን የኢትዮጵያን ጥንታዊ የደአማታውያንን ታሪክ፣ መንግሥትና ሥልጣኔ ከከርሰ ምድር አግኝተው ለትውልድና ለዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳወቁ ሁለቱ ከፍተኛ የኢፕግራፊ ምሁራን (epigraphists) ማለትም የጥንታዊ ጽሑፍ ተመራማሪዎች የሆላንዱ ፕሮፌሰር አብርሃም ጆሃን ድሬዌስና ሉክሰምበርጋዊው ፕሮፌሰር ሮገር ሽናይደር ናቸው።

በፕሮፌሰር ሽናይደር እንደተተረጎመው፣ ከላይ በደአማቱ «ድል አድራጊ» ንጉሥ ለመነ ዜና መዋዕል የተጠቀሱ «ሳባውያን» በዓመተ ዓለም በ4ኛው ምዕተ ዓመት በግምት ከ430 እስከ 330 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ ከአጎራባቹ የሳባ አገር ማለትም ከአረቢያ በስፈራ ይሁን ወይም በዜና መዋዕሉ በግልፅና በይፋ ባልታወቁ መንገዶችና ምክንያቶች መጥተው በሉአላዊ የደአማት መንግሥት ሕግ ሥር የሚኖሩ የውጭ አገር ዜጎች ወይም ባዕዳን ሠራተኞች፣ ገባሮች፣ ቅጥር ሙያተኞች ሊሆኑ ይችላሉ።

[17] Ibid., p.387

[18] Ibid.,

# 3. የኅብረተሰብና የሃይማኖት ግንኙነት

## የሃይማኖት ማኅበራዊ ትምህርትና ተግባር

አራቱ የአዋማዊዝም፣ የክርስትና፣ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች የኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦችና ባህሎች ታሪክ ገላጭ ማህበራዊ ኃይሎችና ሥርዓቶች ናቸው። በዚህ ረገድና ተግባር እስከ ዛሬው ዘመናዊ ሳይንስና ብሔረ እስቴት (ብሔረ መንግሥት) ክስተትና ዕድገት ድረስ በዓለም ታሪክ ሃይማኖት በተለይ የሰው ልጅን መሠረታዊ የመነሻ፣ የሕይወትና የዕውቀት፣ የሥርዓትና የሥልጣን ጥያቄዎችን በሚመለከት ለረጅም ዘመን የትምህርትና የእምነት ምንጭና መሠረት እንደነበር ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል።

የመነሻና የባሕርይ መሠረታዊ ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ የማንኛውም ሃይማኖት መሠረትና ምክንያት የተፈጥሮና የሕይወት ምሥጢር ነው ለማለት ይቻላል። ከዚህ አኳያ በአጠቃላይ መንገድ ሁሉም ሃይማኖቶች ከተፈጥሮና ከሰው በፊትና በላይ የሆነ ብሎም በውስኑና በጠባቡ የሰው ልጅ አእምሮና አሳብ በትክክል የማይታ ወቅና የማይገለፅ አንድ ኃይል ለሁሉም ነገሮችና ሁኔታዎች የመነሻ ምንጭና ምክንያት ነው ይላሉ። አንድ ዓይነት ምሥጢራዊና ፈጠሪ ኃይል እንዳለ ያስተምራሉ። ይህ ምሥጢራዊና ፈጣሪ ኃይል በሰው ልጅ አእምሮ በሥፍራና በጊዜ ቀመር ተወስኖ የማይገለጽና የማይታወቅ ረቂቅ አካል ነው። በመሆኑም ሃይማኖት በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ አንድ ምሥጢራዊ እምነት ነው። ባጭሩ ሃይማኖት በባሕሪው በሰብአዊ አእምሮ በሥፍራ፣ በጊዜና በተግባር መስፈርትና ቀመር ተወስኖ የሚገልጽ እውቀት ሳይሆን ረቂቅ እምነት ነው። አንድ ልዩዓይነት ውስጣዊ የሕይወት ስሜትና ኃይል ነው።

እንዲሁም ከትምህርትና ከተግባር አኳያ ሁሉም ሃይማኖቶች በልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች የተፈጥሮ፣ የሰው፣ የሕይወት፣ የእውቀት፣ የሥርዓትና የመንግሥት መነሻና መሠረት ከሁለቱም ማለትም ከተፈጥሮና ከሰው ውጭና በላይ የሆነ አንድ ዓይነት ፈጣሪ ኃይል እንደሆነ ያስተምራሉ። በመሆኑም

ሃይማኖት በባሕሪውም በተግባሩም ከሰው፣ ከታሪክና ከሳይንስ ውጭና በላይ የሆነ እምነት ነው ለማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል የሳይንስ ትምህርትና ጥበብ እንደሚያስተምረው፣ በአንድ በኩል ሁለቱም ማለትም የሰው አእምሮና ተፈጥሮ ተዛማጅ፣ ሕያውና አዳጊ ነገሮች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ የሰው ልጅ የዕውቀት ምንጭና መሣሪያ የሆነው የሰው አእምሮ በሥፍራ፣ በጊዜና





በተግባር ቀመር የተወሰነ ነገር ስለሆነ በዓለም ላይ የነበረውን፣ ያለፈውንና የሚሆነውን የሕይወት ነገርና ሂደት አገናዝቦ ሁሉንም በአንድ ጊዜ የማያውቅ አንድ ውስን አካል ነው። በመሆኑም እምነትና ተስፋ የሰው ልጅ የሕይወት አካልና ውስጣዊ ሞተር ነው።

## የሃይማኖት ድርጅትና ተግባር በጥንቱ አዋማዊ ግብፅ

የሰው ልጅ እምነትና ሥራ በቅርብና በጥብቅ የተያያዙ ተዛማጅ የሕይወት እንቅስቃሴዎች እንደሆኑ የሰው ልጅ የሥልጣኔ ታሪክ በሥፍራና በጊዜ መስፈርት ያስተምራሉ። በዚህ ረገድና ተግባር የሃይማኖት ተረቶች፣ እምነቶችና ትምህርቶች ሁሉ ለሰው ልጆች በየዘመናቸው የፈጠራ፣ የእምነት፣ የተስፋ፣ የትምህርት፣ የሥራ፣ የድርጅት፣ የሥርዓት፣ የሥልጣን ምንጮችና መሣሪያዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ረጅም የሰውና የሥልጣኔ ታሪክ በግልፅና በዝርዝር ያስተምራል። ለዚህ አባባል አንድ ጥሩ ታሪካዊ ምሳሌና ማስረጃ በታላቁ የዓባይ ሸለቆ የጥንታዊው ግብፅ ሥልጣኔ ነው።

በአንድ ምሁር ጥናት መሠረት የታላቁ ጥንታዊ ግብፅ ሥልጣኔ ሁለት መሠረታዊ መግለጫዎች፣ ተዛማጅ የሃይማኖትና የአርት ተቋማትና ሥራዎች ናቸው።[19] በዚህ ረገድና ተግባር የግብፅ ታላላቅ ፈርኦኖች በዓለም የሥልጣኔ ሥራና ታሪክ በከፍተኛ ደረጃ የሚታወሱት ራ፣ አሲሪስ፣ ኢሲስ፣ ሆራስ፣ ሴት፣ ነፍታይስ፣ ኑት፣ አሞን፣ ማአት፣ ሙት፣ ቾንሱ፣ ፕታ፣ ሴፍሜት፣ ቶት፣ ሃቶር፣ አምቢስ፣ ባስት፣ ሣፒ፣ ኢምሆትፕ፣ እና አቶን ተብለው በልዩ ልዩ ስሞች ለሚታወቁ አያሌ ብሔራዊና አካባቢያዊ አማልክት ክብርና ምሥጋና ባሰሩዋቸው ታላላቅ የመቅደስ፣ የመቃብር (የፒራሚድ) እና የቤተ መንግሥት ሕንፃዎችና የአርት ሥራዎች ነው።

የእነዚህ ታላላቅ የግብፅ አማልክትንና መቅደሶችን ድርጅታዊ ሀብት፣ ኃይልና የጥበብ ሥራዎች በሚመለከት ለምሳሌ አሞን የተባለው ታላቁ የሃይማኖት፣ የመቅደስና የካህናት ተቋም፣ ቴብስ፣ ሂሊኦፖሊስና መምፊስ በተባሉ ሦስት ታላላቅ የግብፅ መዲናዎችና የሃይማኖት ማዕከላት በአንድ በተወሰነ ዘመን በድምር 206,364 የመቅደስ ካህናት፣ ምሁራን፣ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች፣ 476,953 ልዩ ልዩ እንስሳት፣ 1,094 ካሬ ኪሎ ሜትሮች የመሬት ይዞታ፣ 502 ልዩ ልዩ የአበባና የአትክልት ሥፍራዎች፣ 51 ልዩ ልዩ የእርሻ ማሳዎች፣ 88 ጀልባዎችና 169 ግብርና ቀረጥ የሚከፍሉ የከተማ ዝባዎች ነበሩት።

[19] Serge Saunron, The Priests of Ancient Egypt (New York: Grove Press, 1960) Preface.

## የሃይማኖት ምሥጢራዊ ባሕሪውና ግልጽ ማኅበራዊ ፋይዳ

ባጭርና በጥቅል አነጋገር ማንኛውም ሃይማኖት በአንድ በኩል የጎሳ፥ የቋንቋ፥ የህብት፥ የባህል፥ የመደብ ምርጫና ልዩነት ሳያደርግ ሰዎችን በአንድ ምሥጢራዊ የጋራ እምነት ሥር ያስተባብራል። በሌላ በኩል ደግሞ ሕይወት፥ የሰው ልጅን ዕውቀትና የመንግሥትን ሥልጣን ጨምሮ፥ በዓይን ከሚታየውና በእጅ ከሚዳሰሰው ሰውና ተፈጥሮ ውጭና በላይ ከሆነው ከአንድ ምስጢራዊና ከኃሊ ኃይል ይመነጫል ብሎ ያስተምራል። ይህ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት እና እምነት በሰዎች ሕይወትና ተግባር ላይ መሠረታዊ የባሕርይና የአመለካከት ልዩነትና ለውጥ እንደሚያስከትል ረጅም የሰው ልጅ ታሪክ ያስተ ምራል። በሌላ ቃል የሃይማኖት ፋይዳ የሚለካው በሰው ልጅ የአእምሮ ሚዛን ሳይሆን በማህበራዊ ድርጅትና ተግባር ነው ለማለት ይቻላል።

በመሆኑም ዛሬ በድህረ አብዮት በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ታሪክ ላይ በሚካሄደው ጥናትና ምርምር የአገሪቱን ሃይማኖቶች መነሻና ማህበራዊ ፋይዳ በሚመለከት ሚዛናዊ ግምትና ትኩረት ሰጥቶ ማጥናትና ማወቅ በምንም መንገድና ምክንያት የማይታልፍ የእውነትም፥ የእውቀትም፥ የሕዝብም፥ የአገርም አንድ መሠረታዊ ጉዳይና ተግባር ነው።

ከዚህ አኳያ ከደአማት-የሀ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ባለፉት 2500 ዓመታት ውስጥ በድንጋይ፥ በብራናና በወረቀት ላይ በአምስቱ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክና የአማርኛ ቋንቋዎች የተጻፉ የኢትዮጵያ መንግሥታዊ የታሪክ መረጃዎች፥ በሙሉ ለማለት ይቻላል፥ የአማልክት፥ የሃይማኖት፥ የነገሥታት፥ የካህናትና የጦርነት ዘገባዎች ናቸው። ጽሑፎቹ የሕዝቦችን ታሪክና ባህል በግልፅ ስለማያሳዩ ከሰነዶቹ በጥናትና ምርምር ፈልፍሎ የሕዝቡንና የኅብረተሰቡን አጠቃላይ ታሪክና ባህል ማወቅ ቀላል ትግል የማይጠይቅ ታላቅ ሙያዊ ተግባር ነው።





# ክፍል ሦስት

# የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ዓይነትና ብዛት

## 1. የአዋማዊ ሃይማኖት ቀዳሚ መነሻና ሚና

### አሰቢኑስ የትሮጅሎዳውያን የፀሐይ አምላክ

በጥንታዊ የግብፃውያኑ የሃይሮግላፊክስ ቋንቋና ጽሑፍ እንደ ተመለከተው፥ በታላቁ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የፑንት-ኢትዮጵያ ዘመነ ታሪክ የተከሰተው ቢያንስ ቢያንስ ከዛሬ አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ ነው ተብሏል።

በጥንቱ አዋማዊ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ ቋንቋና ጽሑፍ አኀራባቹ የፑንት-ኢትዮጵያ ምድር የአማልክትና የቅመማ ቅመም፥ ማለትም የዕጣን፥ የከርቤ፥ የሙጫ፥ የቀረፋና የዝንጅብል አገር ተብሎ ይታወቃል።[20] በተጨማሪም የጥንቱ ግብፃውያን በታላቁ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የፑንት-ኢትዮጵያ አገር የዘራቸውና[21] የሃይማኖታቸው[22] ምንጭና መነሻ እንደሆን አድርገው ያምኑበት እንደ ነበር ተመልክቷል። በዚህ ረገድና ተግባር በጥንታዊ የግብፅ ታላላቅ አማልክት ሆሩር የሰማይ እመቤት፥ ሚን የምድረበዳው አምላክ፥ ሆራስ የፑንቱ አንበሳ እንዲሁም ቶት የጽሕፈትና የጥበብ ፈጣሪ ከምድረ ፑንት-ኢትዮጵያ የመጡ አማልክት ናቸው ተብሏል።[23]

በዓመተ ዓለም በግምት ከ2800 እስከ 1000 ድረስ በንግድ፥ በባህልና በሃይማኖት መስኮችና ጉዳዮች በጥንታዊ ግብፅና በፑንት-ኢትዮጵያ መካከል ቢያንስ ለ1800 ዓመታት የነበረው ታሪካዊ መስተጋብርና መወራረስ በትክክል በማይታወቅ ሁኔታ ከተቋረጠ በኋላ በሚቀጥለው ሚሊኒየም ውስጥ በክፍለ አህጉሩ የኢትዮጵያ አዋማዊው የደአማት መንግሥትና ሥልጣኔ ቀጥሎ እንደተከሰተ ከላይ ተገልጿል።

በዚህ ዓይነት ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት፥ በዓመተ ዓለም ከ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አንስቶ በዘመነ ክርስትና እስከ 7ኛው ምዕተ

---

[20] Doress, Histoire Sommaire, pp. 47-68: J. Leclant, "L'Exploration des Cotse de la Mer Rough: A la Queste de Pount et Secretes de la Mer-Erythree" , AE: Vol. II (1978, pp. 69-78.

[21] E. A. W. Budge, A History of Ethiopia, (1966), p.7

[22] Doresse, Histoire Sommaire, p.48.

[23] Ibid.,

ዓመት መጀመሪያ ድረስ በአንድ ሚሊኒየም ውስጥ (ከ332 ዓዓ እስከ 642 ዓም) ግብፅን በተከታታይ ይዘው በድምሩ ለ974 ዓመታት የገዙ የአውሮፓ ግሪኮችና ሮማውያን በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ በቀይ ባሕር፣ በአረቢያ፣ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በግብፅና በሜዲትራኒያን ባሕር አገሮችና ሕዝቦች መካከል በንግድ፣ በቋንቋ፣ በባህልና በሃይማኖት መስኮችና መንገዶች የመጀመሪያውን ታሪካዊ የመስተጋብርና የመወራረስ ሥርዓትና ዘመን መሠረቱ።[24]

በተጠቀሰው የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ አህጉራት የመጀ መሪያ መስተጋብርና መወራረስ ሚሊኒየም ክፍለ ዘመን፣ በግሪኮ-ሮማውያን ጸሐፊዎች የተጻፉ መረጃዎች በአንድ በኩል በአፍሪካ አህ ጉር በዓባይ ሸለቆ በሁለቱ ኩሻዊ የግብፅና የኑቢያ ሕዝቦች፣ መንግሥ ታትና ሥልጣኔዎች መካከል በሥፍራ፣ በኢኮኖሚ፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በሃይማኖትና በሥርዓት በጣም የቀረበ ግንኙነትና ትስስር ያሳያሉ።[25]

በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከሰሜንና ከምስራቅ የጠረፍ ክልሎች ጀምሮ በሰሜኑ ደጋማና ተራ ራማ ቀበሌ የትሮጅሎዳውያንን (የአፋር)፣ የአክሱማውያንንና የበር በራውያንን እንዲሁም በደቡብ ምሥራቁ ክፍል በረጅሙ የሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ቀበሌ የአዛኒያውያንን የተለያዩ ነባርና አዋማዊ ሕዝ ቦችን በሥፍራና በባህል ለይተው ይገልጻሉ።[26]

በዚህ ረገድና ተግባር በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት በ80 ገደማ በክፍለ አህጉሩ በስም የተጠቀሱ የአክሱማውያንን፣ የትሮጅሎዳውያንን፣ የበርበራውያንንና የአዛኒያውያንን መልክዓምድር፣ ኢኮኖሚ፣ ባህልና አዋማዊ ሃይማኖት ለይቶ በመግለጽ በጻፈው ትምህርታዊ መጽሐፍ፣ ሮማዊው ጸሐፊ ፕሊኔ በዘመኑ በአገራቸው በዕጣን፣ በከርቤ፣ በዝንጅብልና በቀረፋ ቅመማ ቅመም ምርትና ንግድ ተሰማርተው የሚኖሩ የትሮጅሎድ ቆለኛ ሕዝቦች በተለይ ከአክሱም ደገኞችና እንዲሁም በአረቢያ ከሚና፣ ከሳባ፣ ከቀጣባንና ከሃድራማዊ አጎራባች አገሮች ጋር በንግድ፣ በባህል፣ በሥርዓትና በሃይማኖት የነበራቸውን የቀረበ መስተጋብር፣ ትስስርና መወራረስ በዝርዝር ያስረዳል።[27]

[24] Ibid., Chap. 3, pp. 63-103: Lapiso G. Dilebo, The Italo- Ethiopian War of 1887-1896: From Dogali to Adwa, (1996), pp. 1-2.

[25] Doresse, Histoire Sommaire , pp. 63-70.

[26] Ibid., pp. 70-103

[27] Ibid., pp. 72-86.





በተጨማሪም ፕሊኔ በመጽሐፉ በትሮጅሎዳውያኑ አገር ከቀረፋ ምርትና ንግድ ጋር የተያያዘውን አሰቢኑስ ተብሎ የሚታወቅ የፀሐይ አምላክን[28] ሃይማኖታዊ ባህልና ሥርዓት እንደሚከተለው ይገልፃል። በፕሊኔ ዘገባ መሠረት፣ በትሮጅሎዳውያን አገር የቀረፋ ቅመም ምርትና ንግድ በአግባቡ የሚከናወነው በአሰቢኑስ የፀሐይ አምላክ ካህን ልዩ ትዕዛዝ፣ ፈቃድና አመራር ነው። በቅመሙ ምርት ዋዜማ ለአሰቢኑስ የፀሐይ አምላክ በአርባ የሚቆጠሩ በሬዎች፣ ፍየሎችና በጎች ለመስዋዕት ሥነስርዓት በአምላኩ ካህን አማካይነት ይቀርባሉ።

ከመስዋዕቱ ክብረ በዓል በኋላ የሚሰበሰበው የቀረፋ ምርት፣ በካህኑ እጅ በሁለት ተከፍሎ የተወሰነው ድርሻ ለአሰቢኑስ አምላክ ይሆናል። የተቀረውን ምርት አምራቾቹ ለነጋዴዎች በመሸጥ እንደ ሚጠቀሙ ፕሊኔ ጨምሮ ገልጿል።[29] በዘመኑ የትሮጅሎዳውያኑን የቅመማቅመም ምርቶች የሚገዙ ዋና ደምበኞች በአረቢያ የሚና፣ የሳባ፣ የቀጣባንና የሃይድራማዊ አጎራባች አገሮች እንደ ነበሩም በፕሊኔው ዘገባ ተመልክቷል።[30]

## የደአማታውያኑ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖት

ከላይ እንደተገለጸው በደአማት ዘውዳዊ አገርና መንግሥት ነረሙ፣ ጸደቀነ፣ ሸመነ፣ ረበ እና አበከወደመ የተሰኙ የአገር ውስጥና እስተር፣ ሀወበስ፣ አለመቀሀ፣ ደተሀመየመ እና ደተበአደነ የተባሉ የውጭ አገር በድምሩ አሥር በስም የታወቁ መንግሥታዊ አማልክት ነበሩ። በዘመኑ በሁለቱ የደአማትና የሳባ ቋንቋዎችና ፊደሎች ተጽፈው በቅርቡ ከከርሰ ምድር በአርኪኦሎጂ ጥናት የተገኙ የኢትዮጵያ ቁልፍ የታሪክ ሰነዶች ለተጠቀሱ አማልክት ክብርና መታሰቢያ በዘመኑ ነገሥታት በድንጋይ ላይ የተቀረፁ ዝክረ ነገሮች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ የኢትዮጵያ የጥንቱ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖቶች የአገሪቱ የጥንታዊ ሥልጣኔ አንድ መነሻና መገለጫ ናቸው ለማለት ይቻላል።

## የአክሱማውያኑ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖት

በ330 ዓመተ ምህረት አካባቢ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና ሃይማኖት ወደ አገሩ ከመግባቱ በፊት በአክሱማውያን አገርና ቤተ መንግሥት አስተር፣ ብሔር፣ ምድር፣ መሕርም፣ ዘዩስ፣ አሬስና

[28] Ibid., pp. 74-85.

[29] Ibid., p. 74

[30] Ibid., p. 73-84.

ፖሲዶን የተባሉ ሰባት አዋማዊ አማልክት ነበሩ። ከእነዚህ አስተር በዓመተ ዓለም ከ5ኛው ምዓ ጀምሮ ለረጅም ዘመን በደአማታውያን አገርና መንግሥት የነበረ አምላክ ነው። ዘዩስ፣ አሬስና ፖሲዶን በአካባቢው የግሪክ ንግድ፣ ቋንቋ፣ ባህልና ሃይማኖት ከተስፋፋ በኋላ የገቡ የግሪክ አዋማዊ አማልክት ናቸው።

ከረጅም የሰውና የሥልጣኔ ታሪክ አኳያ ሲታይ፣ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ አራት ምዕተ ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ በሦስቱ የግዕዝ፣ የሳባና የግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች በድንጋይ ሐውልቶች ላይ ተጽፈው ከከርሰ ምድር በዘመናዊ የአርኪኦሎጂ ጥበብና ጥናት የተገኙና ከላይ በሠንጠረዥ 4-5 የቀረቡ የታሪክ መረጃዎች በዘመኑ ነገሥታት ለእነዚህ አዋማዊ አማልክት ክብርና መታሰቢያ የተቀረፁ የጽሑፍና የሐውልት መረጃዎች የኢትዮጵያ የጥንታዊ ሥልጣኔ ቁልፍ መገለጫዎች ናቸው።

## የደቡብ ኢትዮጵያ አዋማዊ ሃይማኖቶችና የታሪክ መረጃዎች

በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በጥንታዊ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ፣ የደአማት፣ የሳባ፣ የግዕዝ፣ የግሪክ፣ የላቲንና የአረብ ቋንቋዎችና ፊደሎች ተቀርፀው በተገኙ የሰነድ መረጃዎች መሠረት በተለይም በክፍለ አህጉሩ የምስራቅና የሰሜን ጠረፍና ደጋማ ክልሎች ጥንታዊ የፑንታውያንን፣ የደአማታውያንን፣ የትሮጅሎዳውያንን የበርበራውያንን የአክሱማውያንን አዋማዊ ሃይማኖቶች ታሪካዊ መነሻና ዕድገት በሚመለከት ከላይ የታሪክ መግቢያ ቢጋር ቀርቧል።

ነገር ግን በክፍለ አህጉሩ የደቡብና የመሀል ደጋማና ጨናማ ክልሎች ጥንታዊ የሐርላ፣ የሀዲያ፣ የዳሞት-ጎንጋ፣ የጋሞ-ወላይታ ... ሕዝቦችና መንግሥታት በቅርቡ ሦስቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና፣ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ አካባቢው ከመግባታቸው በፊት ከላይ በቀረቡ የግብፅ፣ የደአማት፣ የሳባ፣ የግዕዝ፣ የግሪክና የላቲን ጥንታዊ ሰነዶች በምንም ሥፍራና ጊዜ ተጠቅሰው አልተገኙም።

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል በሐረርጌ ደጋማው ክፍል ከለጋኦደ ዋሻ፣ በሲዳሞ ከሻቤ ዋሻ በድንጋይ ላይ ተስለው የተገኙ ጥንታዊ የእንስሳትና የሰዎች እንዲሁም በደቡብ ሸዋ፣ በአርሲና በሐረርጌ ደጋ በብዙ ሥፍራዎች የሚገኙ ተክል የመቃብር ድንጋይ ሐውልቶች በጥንታዊ ግብፃውያን፣ ግሪኮች፣ ሮማውያንና አረቦች ሆነ በአክሱማ ውያን በቀጥታ ባልተደረሱ የደቡብና የመሀል ኢትዮጵያ ክልሎች ቢያንስ ገና ከዛሬ አራትና አምስት ሺህ ዓመታት በፊት ገደማ ጀምሮ





በእንስሳት እርባታ፣ በእርሻና በዕደጥበብ ተግባራት የተሰማሩና በአዋማዊ ሃይማኖቶች የተደራጁ ብዙ ጥንታዊ የሐርላና የሀዲያ ተዛማጅና አጎራባች ሕዝቦች ይኖሩባቸው እንደነበር በግልፅ ያሳያሉ።[31]

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች የተጠቀሱ የዋሻ ድንጋይ ላይ ሥዕሎችንና የመቃብር ላይ ሐውልቶችን የሠሩ ጥንታዊ ሕዝቦችን መነሻ፣ ማንነትና ታሪካዊ ዕድገት በተመለከተ እስከ ዛሬ ድረስ በደቡብ ምስራቅ በተለይም በሐረርጌ የአካባቢው ነዋሪዎች በትውፊታዊ ግንዛቤያቸው የጥንቱ የሐርላ ሕዝቦች በሚል ጥቅል ስያሜ እንደሚጠሩዋቸው ታውቋል።[32]

ከቅርብ ጊዜ ታሪክ አኳያ ደግሞ ከ16ኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ በአካባቢው በዛሬው የሱማሌ፣ የኦሮሞና የአፋር ማህበረሰቦች እስኪወረስ ድረስ በምስራቅ ኢትዮጵያ *ዛሙብራሀ፣ ባርዛራሀ፣ ያፋሳይ፣ ጃዛር፣ አረብ፣ ታከላና አሊቃ* በተባሉ በራሱ አያሌ ጎሣዎችና ማኅበረሰቦች የተከፈለ በእንስሳት እርባታ፣ በእርሻና በንግድ ተግባራት የተሰማራ ብሎም በመንግሥታዊ ሥርዓት የሚኖር አንድ «ሐርላ» የተባለ አገርና ሕዝብ እንደነበር ከዘመኑ ሰነዳዊ መረጃዎች በትክክል ለማወቅ ይቻላል።[33]

በመሆኑም በእነዚህ በተጠቀሱ የአርኪኦሎጂ፣ የትውፊትና የታሪክ መረጃዎች መሠረት፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕዝቦች አንዱ በዘር በቋንቋና በሃይማኖት በደቡብ ምስራቅ ከዛሬው የሐረሪ (አደሬ) ሕዝብ ጋር የቀረበ ታሪካዊ አንድነት ያለው *የሐርላ ሕዝብ* ነው። እንዲሁም በደቡብ ኢትዮጵያ፤

1) በግምት በምስራቅ ከዋቤ ወንዝ አንስቶ በምዕራብ እስከ ጊቤ ወንዝ ድረስ ጥንታዊ የተክል ድንጋይ ሐውልቶች እስከ ዛሬ በሚገኙበት ምድር በ15ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ *ገዳይቾ፣ ጉዳለ፣ ዲሆ፣ ሀይባ፣ ገንዛ፣ ሲጋ፣ ገበ፣ ቀቤና፣ ጎጋለና አላባ* በተባሉ አሥር የጎሳና የክልል ማኅበረሰቦችና መስተዳድሮች ተከፍሎ የነበረው የሀዲያ-ሲዳማ ሕዝብና[34] መንግሥት፤

[31] F. Anfray, "Les Stelse du Sudshoa et Sidamo", AE, Vol. 12 (1982): R. Joussoume, Legalithisme en Ethiopie: Monuments funeraires Protostorique du Harar (1974), pp. 101-103).

[32] U. Braukamper, "Islamic Principalities in South- Eastern Ethiopia between the 13th and 15th Centuries", Part I and II, Ethiopianist Notes, No. 1 (1977).

[33] G. W. B. Huntingford, tr. and ed., The Glorious Victories of Amda Seyon King of Ethiopia (1965), p. 74: Arabfaqih, Histoire de la Conquete de L'Abyssinie, tr. and ed., R. Basset, (1897), pp. 111, 124, 130, 150, 170, 171,

[34] Huntingford, Amda Seyon, pp. 19-23: Ibn Fadl A. Umari: Masalik El Absar F:

2) በደቡብ ምዕራብ ከአባያ ሐይቅ እስከ ጎጀብ ወንዝ በሚገኘው የኦሞ ሸለቆ ክልል የተለያዩ የጋሞ-ወላይታ ሕዝቦች፤[35]

3) በመሀል ምዕራብ በአዋሽ፥ በሙገር፥ በጊቤ፥ በዓባይ፥ በአንገር፥ በዲዴሳና በጎጀብ ወንዞች አካባቢ ዳሞት፥ ሂናሮ (እናርያ)፥ ቦሻ፥ ከፋ፥ ሸኮች (ሞቻ)፥ ቢዛሞ፥ ሺናሻና አንፊሎ ተብለው በልዩ ልዩ የማህበረሰብ ስሞች ለሚታውቁ አያሌ ተዛማጅ አገሮችና መንግሥታት የጋራ መነሻ የሆነው የጎንጋ፣ሕዝብ[36] ከላይ ከተጠቀሱ የሐርላ፥ የሀዲያ፥ የወላይታ፥ የጋሞ ወዘተ ማህበረሰቦችና መንግሥታት ጋር በጥንታዊ የታሪክ ሰነዶች የታወቁ ዋና ዋና የደቡብ ኢትዮጵያ ነባር ሕዝቦች ናቸው።

በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ሚሊኒየም መጨረሻ ላይ ከእነዚህ የክልሉ ሕዝቦች በደቡብ ምስራቅ የሐርላ-ሸዋና የሀዲያ-ሲዳማ አጎራባችና ተዛማጅ ማኅበረሰቦች በመሀል-ምዕራብ ደግሞ የዳሞት- ጎንጋ ማኅበረሰቦች በየአካባቢያቸው ሉአላዊ አገሮችና መንግሥታት እንደ ነበሩ እስከ ዛሬ ድረስ የተገኙ የሰነድ፥ የትውፊትና የቋንቋ መረጃዎችና ጥናቶች ያሳያሉ።[37]

ከእነዚህ ነባርና አዋማዊ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችና መንግሥታት በዘመነ ክርስትና በማምት ከመጀመሪያ ሚሊኒየም ፍጻሜ ጀምሮ ሁለቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖቶች[38] ከምስራቅና ከሰሜን ወደ መሀል አገር ከመግባታቸው በፊት በተለይ በጎንጋ ማኅበረሰቦች ዘንድ የአዋማዊ ሃይማኖት፥ ባህልና ሥርዓት በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ እንደነበር በ13ኛው ምዕተ ዓመት በዳሞቱ አዋማዊ ንጉሥ ሞተሎሚና በአማራ መነኩሴ አቡነ ተክለሃይማኖት (1215-1313) መካከል ለረጅም ጊዜ የተካሄካደው ታላቅ የሃይማኖት ትግል[39] አንድ ታሪካዊ ማስረጃ ነው። ዛሬ በደቡብ ምዕራብ

Masalik El Masar, tr. and ed., G. Demombynes, (1927), pp. 14-18: J. Perruchon, tr. and ed., Les Chroniques de Zara Yaeqob et Baeda Maryam, (1893), pp. 16-18: U. Braukamper, Geschichte der Hadiya Sud-Athiopiens, (1980): Maps 6-18.

35 C. F. Beckinham and G. W. B. Huntingford, trs and eds., Some Records of Ethiopia 1593-1646, (1954), pp. IXV-LXVII.

36 Huntingford, Amda Syon, p. 45: O. G. S. Crawford, ed., Ethiopian Itineraries 1400-1524, (1958), pp. 78-84: Tekleselassie, Susenyos 1605-1632 (unpublished) Chronicle), W. Lange, History of the Southern Conga: Southern Ethiopia, (1982).

37 Ibid., Ethiopia Itineraries, pp. 80-82: Braukamper, "Islamic Principalities", pp. 19-32.

38 J. S. Trimingham, Islam in Ethiopia, (1966), pp. 48-76.


39 Ibid., p.65:





ኢትዮጵያ የከፊችና የሻኮች የቋንቋ ማህበረሰቦች በአካባቢው ጥንታዊ የጎንጋ፥ የዳሞት፥ የእናርያ፥ የቦሻ፥ የቢዛሞ፥ የአንፊሎ፥ የሺናሻ ... ሕዝቦችና መንግሥታት ቀጥተኛ ተወላጆች ናቸው።[40]

የኢትዮጵያ የ1524 – 1543 የኢማም አህመድ ጦርነት ካርታ



ምንጭ ላጊድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።

40 Weiner J. Lange, History of the Southern Gongo (Southern Ethiopia) (1982).

# 2. የክርስትና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

## የክብረ ነገሥቱ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ትምህርት

በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት (1314-1344)፣ በ1320 ገደማ፣ ከአረብኛ ቋንቋ ረቂቅ በአክሱም ከተማ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተርጉሞ የኢትዮጵያ የክርስትያን ሃይማኖት፣ መንግሥትና ኅብረተሰብ መሪ የፖለቲካ ሰነድ በተደረገው የክብረ ነገሥት መፅሐፍ እንደተባለው፣ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱም መንግ ሥትና ሥልጣኔ በአሪት ሃይማኖትና ሕግ መሠረት ማክዳ ወይም ሳባ ከተባለች ከኢትዮጵያ አዋማዊት ንግሥትና ከይሁዳውያኑ ንጉሥ ሰለሞን ተወለደ በተባለው በቀዳማዊ ምኒልክ አመራር የተመሠረተው ከዛሬ 3000 ዓመታት በፊት በዓመተ ዓለም በ970-931 ባለው ዘመን ውስጥ ነው።[41]

በዚህ የፖለቲካ እምነትና ትምህርት መሠረት የኢትዮጵያ አዋማዊ የአክሱም ሕዝብና ቤተ መንግሥት በዘመነ ክርስትና በ330 ዓም በአፄ ኢዛና መሪነት ወደ አዲሱ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና ሃይማኖት በገባ ጊዜ በዓመተ ዓለም ከ931 ጀምሮ በዘመነ ክርስትና እስከ 330 ዓመተ ምህረት ድረስ ቢያንስ ለ1260 ዓመታት በጥንቱ መለኮታዊ ኦሪት ወይም በፅላተ ሙሴ እየተመራ ይኖር ነበር ተብሏል።

ይህንን የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያንን የመነሻና የማንነት ታሪክ በሚመለከት፣ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊ አለቃ ታዬ ገብረ ማርያም (1860-1924)፣ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ* በተሰኘው መጽሐፍ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘርና ትውልድ* በሚል ርዕስ ዘርዝረው እንዳስቀ መጡት፣

> *የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በዋናው ነገር በአራት ክፍል ይከፈላል። ነገደ ኦሪት፣ ነገደ ካም፣ ነገደ ሴም (ነገደ ዮቅጣን) ነገደ እሥራኤል ናቸው።*
>
> *ይህን ስለአልን የሕዝቡንና የመንግሥቱን ዋና ዋና የሆነ ዓይነተ ኛውን ክፍል መናገራችን ነው እንጂ በዝርዝር ግን በየዘመኑ ከእስያ እየፈለሱ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ልዩ ልዩ ዓይነት ሕዝቦች እጅግ ብዙዎች ናቸው።*
>
> *ከሁሉ በፊት አስቀድመው በመጀመሪያ ከእስያ ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አገሪቱንም ይዘው የኖሩ ነገደ ኦሪት የተባሉ ናቸው። የእነዚህም አባት በክብረ ነገሥት ከገፅ 40 እስከ 50 እንደአሳየን ከአዳም ልጆች አንዱ ኦሪ ወይም አራም የተባለው ነው። እርሱ … ከነልጅ ልጆቹ 21 ነገሥታት በኢትዮጵያ ነገሡ። በመጨረሻው ንጉሣቸው በሶሊማን ታጊ ጊዜ በኖህ ዘመን በጥፋት ውሃ ተደመሰሱ። አለቁም። የነዚህን ሕዝብና ነገሥታት ታሪክ በአዲሱ ክብረ ነገሥት ከገፅ 317 እስከ 333 ተመልከት።*
>
> *እነዚህ ሕዝቦች በማየ አይህ ከጠፉ ወዲህ የኢትዮጵያ አገርና ምድርም ሁሉ ከጥፋት ውሃ እስከ ባቢሎን ግምብ መፍረስ በቋንቋ ተለያይተው እስከ ሰዎች መበታተን 531 ዓመት ከሥር ኢትዮጵያ ሰው የሌለባት ባዶ ነበረች። ከዚህ በኋላ ነገደ ካም መጡና ወረሰዋት።[42]*
>
> *ካም ከእስያ በባብኤልመንደብ ተሻግሮ መጥቶ በኢትዮጵያ ገባ። ይህም የሆነው በ2787 ዓመተ ዓለም 2713 ዓመት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት ነው።*
>
> *ካም በኢትዮጵያ 78 ዓመት ገዝቶ እንደገና ወደ እስያ ሄዶ ሶርያንም እይዛለሁ ብሎ ከሴም ልጆች ጋር ተዋግቶ በጦር ሞተ። ልጆቹ ግን ታላቅ ወንድማቸው ኩሣን በሊየቸው አንግሠው ኢትዮ ጵያን ወረሱ። ነገደ ካም እስከ የልጅ ልጆቻቸው 25 ነገሥታት ከ2787-3515 [?] ዓመተ ዓለም 743 ዓመት ነገሡ። ኢትዮጵያንም ገዙ። ክብረ ነገሥት ከገፅ 333-348 እይ።*
>
> *በነገደ ካም ዘመን ሦስት ነገዶች በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። እነርሱም ነገደ ሻንቅላ፣ ነገደ ቅማንት፣ ነገደ ወይጦ ናቸው።[43]*

በዚህ በአለቃ ታዬ የታሪክ ትምህርትና ትንተና መሠረት፣ በነገደ ካም ሕዝቦች ላይ በመጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ሕዝቦች «ምርጥ» ሴማዊ የዮቅጣንና የእሥራኤል ነገዶች ናቸው። በአለቃው ቃልና ትምህርት መሠረት፣

> *ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ባላባቶች የሴም ዘሮች ስድስት ወገን ናቸው። እነርሱም አማራ፣ ትግሬ፣ አገው፣ በደው አስገዴ፣ በቅላ፣ ሐባብ ናቸው። በደው አስገዴ፣ በቅላ፣ ሐባብ እነዚህ ሦስቱ ነገድ ወደ እስላም ሃይማኖት ገብተው ከወንድሞቻቸው ተለይተው ልዩ ወገኖች ሁነዋል።*
>
> *አማራ፣ ትግሬ፣ አገው ግን በፊት በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ በሕገ ኦሪት ያመኑ በኋላ በክርስትና ያመኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት የጸኑ ከጥንት ጀምሮ መንግሥት ያልጠፋባቸው ባዕድ ገዥ ያልገባባቸው የእግዚአብሔር ረዴት ያልራቀባቸው ሕዝብ ናቸው።*
>
> *ከዚህም ሁሉ ጋር አማሮች፣ ትግሮች የኢትዮጵያ ዓይነተኛ ባላገሮችና ባላባቶች ከሆኑ የሴም ዘር ከነገደ ዮቁጣን ልጆች ከእሥራኤልም ዘሮች እንደሆኑ የሚያስረዳ ብዙ ምስክር አላቸው።[44]*

---

[41] E. A. B. Budge, tr. and ed., The Queen of Sheba and Her Only Son Menyelek I, (London: OUP, 1922).

[42] አለቃ ታዬ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ (አዲስ አበባ፣ 1958)፣ 6ኛ እትም ገጽ 11-12

[43] Ibid., p. 12

በክብረ ነገሥት ባሕረ መዝገብ መሠረትነ በጥንቱ አዋማዊ የኢትዮጵያ ምድርና ሕዝብ ላይ ከዛሬ 3000 ዓመታት በፊት የኦሪትን ሃይማኖትና ሕግ ምሥረታ በሚመለከት «የነገደ እሥራኤል መምጣት» በሚል መነሻ በአለቃ ታዬ መጽሐፍ እንደተባለው፤

*በእሥራኤል ንጉሥ በሰለሞን ዘመን ማክዳ የኢትዮጵያ ንግሥት በመጽሐፍ ቅዱስ የሳባ የአዜብ ንግሥት የተባለች ... የሰለሞንን ጥበብ ወሬውን ሰምታ እርሱን ሊማየትና ጥበቡን ለመስማት ከብዙ ጓዝ ጋር ወረደች። ከሰለሞን ቀዳማዊ ምኒልክን ጸንሳ ወደ አገርዋ ተመለሰች። ካገርዋም ስትደርስ ወለደችው። ስሙንም የብልሃተኛ ልጅ ስትል እብነ እልሐኪም አለችው። ከእናቱ ጋር አድጎ 22 ዓመት ሲሆነው አባቱን ሰለሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ። በዚያ ሕገ ኦሪትንና ሕገ መንሥግትን የዕብራጥስጥን ቋንቋም እየተማረ ሦስት ዓመት ተቀመጠ። ከዚህ በኋላ አባቱ ንጉሥ ሰለሞን በኢትዮጵያ እንዲነግሥ ከእሥራ ሁለት ነገደ እሥራኤል 12000 የበኩር ልጆቻቸውን ብልሆችና አዋቂዎች የሆኑትን መርጦ ከተማሩት ከካህናት ልጆችና ከመኳንንት ልጆች 22 ታላላቆች ሹሞ ልጁ ቀዳማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሥ ይሆን ዘንድ ልብሰ መንግሥት አሰፍቶ ቅብአ መንግሥት በሊቀ ካህናቱ እጅ አስቀብቶ ሕገ ኦሪትን ሥርዓተ መንግሥት ሰጥቶ ወደ ኢትዮጵያ መልሶ ሰደደው። ክብረ ነገሥት ገጽ 188-189 እይ።[45]*

## በኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የኦሪት መገኘት ጥያቄ

የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊ አለቃ ታዬ በኢትዮጵያ የፈላሻ ኦሪትንና የክርስትና ሃይማኖትን መነሻና መስተጋብር በተመለከተ የሚከተለውን ማብራሪያ አቅርበዋል።

*ስለ ፈላሾች ነገር ታሪክ ሦስት የታመነ ነው ያልነው እንዲህ ነው። በኢትዮጵያ ያሉ ፈላሾች ሥራቸውና ምንጫቸው ያለ ጥርጣሬ ከእሥራኤል ዘር ናቸው። ከፖለስቲና ከእሥራኤል አገር ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ግን በየዘመኑ ሦስት ጊዜ ነው።*

*መጀመሪያ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከእሥራኤል ሕዝብ አብረው የመጡ ናቸው። በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የኢትዮጵያ ሕዝብና ነገሥታት የመንግሥትም ዘር ሁሉ በወንጌል ቃል አምነው ክርስትና ሲገቡ እነርሱ ግን ከወንድሞቻቸው ከሕዝባቸውም ተለይተው በወንጌል ቃል አናምንም ክርስትና አንገባም ሕገ ኦሪትን አንለቅም ብለው ተለይተው የቀሩ ናቸው።*

*ሁለተኛ፥ አስብያኖስና ጢጦስ የሮም ነገሥታት ኢየሩሳሌምን ባፈረሰዋት ቤተ መቅደስንም ባቃጠሉና እሥራኤልንም በፈጆዋቸው ጊዜ ከሞት የተረፉ እሥራኤል በያገሩ ሲበታተኑ አንድ ክፍል ከፖለስቲና ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ።*

*ሦስተኛ በጉዲት ዘመን ከምስር ንጉሥ ሸሽተው ከጉዲት ጋር ኢትዮጵያ ገብተው የክርስቲያንን መንግሥት የገለበጡና ያፈረሱ የአክሱምንም ቤተ ክርስቲያን ያቃጠሉና ክርስቲያንን ያረከሱ ናቸው። እነዚህም የፊተኞች ፈላሾች ከኋለኞች ጋር ተቀላቅለው ጉዲትን ረድተው መንግሥትን ቢያፈርሱ በክርስቲያን ላይም ግፍ እየሰሩ ሃይማኖተ ወንጌል ቢያረክሱ ጉዲት በሞተች ጊዜ የክርስቲያን ንጉሥ አንበሳ ውድም በነገሠ ጊዜ እነዚህን ፈላሾች ፈጃቸውና የክርስቲያንን ደም ብድር መለሰ።*

*ከዚህ በኋላ ጥቂት ከሞት የተረፉ በዱር በገደል የነበሩ ፈላሾች ሁሉ ማረን ስለ እግዚአብሔር ብለህ ይቅር በለን ብለው ደንጊያ እየተሸከሙ ... ገብተው ቢለምኑት ንጉሡም ነፍሳችሁን ምሬአችኋለሁ ከርስት ከጉልት ግን ነቅያችኋለሁ ብሎ ነቀላቸው። በዚህም ከጉልት ተነቅለው ስደተኞች የክርስቲያን ዜጎች ጥገኞችና ጢሰኞች ሁነው ኖሩ። ስለዚህም ፈላስያን ተባሉ። ፈላስያን ማለትም ስደተኞች ማለት ነው። በዘመኑ ብዛትም ፈላሻ ተባሉ።*

*እነዚህ ሕዝቦች እስከ አጼ ዓምደ ፅዮን ዘመን (1313-1344) ከዚያም ወዲህ እስከ አጼ ሠርፀድንግል ዘመን (1563-1597) ድረስ በክርስቲያን መንግሥት እየሸፈቱ ያውኩ ነበር። በዚያም ምክንያት ነገሥታት ቀጠቀጥዋቸው። አደከምዋቸው። ያለ ምህረት አጠፍዋቸው። አጠቁዋችው። ዛሬ ግን የቀሩት ጥቅቶቹ በክርስቲያን ላይ ራሳቸውን የማያቀኑ የተጠቁ ሆኑ። በያገሩ ጥቂት ጥቂት አሉ። የሚበዙ ግን በጭልጋ፥ በጋባ፥ በአርማጭሆ፥ በወልቃይት፥ በጠገዴ፥ በቆላ ወገራ፥ በጎንደር ከተማ ዙርያ ይኖራሉ።*

*እነዚህ ሕዝቦች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ከመግደላቸውና ለወንጌል ሃይማኖት ካለመታዘዛቸው በላይ ደሙ በእኛ በልጆቻችንም ላይ ይሁን ያሉት መርገም ደርሶባቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመባል ፈንታ በዓለም ላይ ተበታትነው ነበር። እንደዚሁም ብዙ ችግርና መከራ ደርሶባቸው በብዙዎች ዘንድ ተጠልተውና ተንቀው ይኖሩ ነበር። ... ስለ ነገደ ፈላሻ ታሪክ በክብረ ነገሥት በገፅ 195-197 ተመልከት።[46]*

## በአለቃ ታዬ የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የቀረበ ሂስ

በትንሹ፥ ባለፉት አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት ውስጥ በታላቁ የሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በተለይ በጥንቱ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ፥ በደአማት፥ በሳባ፥ በግዕዝ፥ በግሪክ፥ በላቲንና

---

[44] Ibid., p. 21

[45] Ibid., p. 27

[46] Ibid., p. 34-35

በአረብኛ ቋንቋዎች በልዩ ልዩ ሥፍራዎች፣ ጊዜያት፣ መንገዶች፣ መግለጫዎችና ምክንያቶች ተቀርጸው የሚገኙትን የኢትዮጵያ ጥንታዊ የታሪክ መረጃዎችን የማያውቁ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ከ1270 ወዲህ የአገሪቱን ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በመካከለኛው ምስራቅ ከጥንታዊ ይሁዳውያኑ የሃይማኖት ትምህርትና ትውፊት ጋር በቅርብ አዛምደው በማቅረብ ከላይ በክብረ ነገሥትና በአለቃ ታዬ የቀረበውን የተረት ቅኝት አድርገውታል።

በዚህ በክብረ ነገሥትና በአለቃ ታዬ የኢትዮጵያ ታሪክ ግድፈት ላይ በ1984 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር መጽሔት ውይይት ቅፅ 1 ቁጥር 2 «ተረትና ታሪክ በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ከፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት የሚከተለው ሂስ ቀርቧል። በፕሮፌሰሩ ሂስ እንደተባለው፣ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ታሪክን ከሃይማኖት ጋር አያይዘው በማቅረብ ተግባር ዕውቅ ባለሙያዎች ናቸው። በፕሮፌሰሩ ቃል፦

> ... በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የጥንት ጸሐፊዎች በጣም የታወቁ ናቸው። ለምሳሌ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ከሀገራችን ታሪክ ጋር በቅርብ ያዛምዱታል። ሕዝቡ ሳይቀር ከጥንት እሥራኤል አገር የመጣ ነው እያሉ ይተርታሉ። የንግሥት ሳባና የቀዳማዊ ምኒልክ ተረት ይህንን ነው የሚያስተምረው። ካህናቱ እንደእውነት አድርገው ተቀብለውታል። በየመድረኩም ይሰብኩታል። በካህናት እንደበት የሚነገር ደግሞ እንደሃይማኖት አጥብቆ ስለሚያዝ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ትውፊትና አፈታሪክ ውስጥ በጣም ዘልቆ ገብቷል። ነገሥታቱ፣ መኳንንቱ፣ ካህናቱና ተራው ሕዝብ እንኳ ሳይቀር፣ ዘር ሲቆጥሩ ወይም ከንግሥት ሳባና ከልጇ ከቀዳማዊ ምኒልክ ወይም ከምኒልክ ጋር የእሥራኤልን ታቦት ሠርቀው መጡ ከሚባሉት ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ካንደኛው ነው የሚጀምሩት። ሰለሞናዊ የሚባለው ሥርወ መንግሥት መነሻው ከዚሁ ተረት ነው፣ የፈላሻ ሕዝብም እንደዚሁ።
>
> ይህ ተረት ከየብራና መጻሕፍቱ ሲገለባበጥ፣ በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በሃያኛው መጀመሪያ ላይ እስከተነሱት የታሪክ ጸሐፊዎቻችን ድረስ ደርሷል። በተለይ አለቃ ታዬ የጻፉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በዚህ ነገር እጅግ ተበክሏል።...
>
> አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእሥራኤል ወይም ከከነዓን እንደመጣ አድርገው ነው የጻፉት። ይህ ነገር አሁን እኛ ለምና ደርገው የታሪክ ምርምር አንዳንድ ችግር እየፈጠረ ነው። ብዙ ጊዜ ቃለመጠይቅ የምናቀርብላቸው አዛውንት በዚህ ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ የታተመውን የአለቃ ታዬ መጽሐፍ ያነበቡ ናቸው። ታዲያ እንደሕዝባቸው ታሪክ አድርገው መልሰው የሚነግሩን ከአለቃ ታዬ ያገኙትን ይሆንብናል። ሌላው የታሪክ





ጸሐፊያችን አቶ አጽሜ ግን ስለ ንግሥት ሳባና ቀዳማዊ ምኒልክ ተረት የተለየ አስተያየት አላቸው። ከቀድሞ ጀምሮ የሚነገረውን ይመዘግቡና ሲጨርሱ እንዲህ ሲሉ በፈገግታ ይደመድሙታል። 'ይህ ነገር እንቅፋት፣ ጥፋት ነው እውነቱ ከውሸት ስለአልተለየ። በዘንዶ መቅደስ ጽላተ ሙሴ ገብቶበት።'

ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከእሥራኤል ጋር የማያያዝ ነገር ተጨባጭ የታሪክ ማስረጃ የለውም። እንዲያውም ያሉን አስተማማኝ የታሪክ ቅሪቶች በቀጥታ ይቃወሙታል። ቀዳማዊ ምኒልክና ጓደኞቹ የእሥራኤል ወጣቶች ከኢየሩሳሌም ታቦት ሰርቀው አክሱም ከተማ ቤተ መቅደስ አኖሩት በሚባልበት ጊዜ አክሱም ገና አልተቆረቆረችም። አክሱም ከተማና የታሪክ ዘመን የሚጀምረው የቀዳማዊ ምኒልክ አባት ነው ከሚባለው ከንጉሥ ሰለሞን 800 ዓመታት ያህል ቆይቶ ነው። የአይሁዶችም ሃይማኖት በዚያን ጊዜ ተመሥርቶ፣ ንጉሡ፣ ተከታዮቹና ሕዝቡ ሁሉ ተቀብለውት፣ በዚያው ጊዜ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ከእብራይስጥ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞ ነበር የሚባለውም እንዲያው የሃይማኖት ተረት ነው እንጂ የታሪክ መሠረት የለውም። ግዕዝ የመጻፊያ ቋንቋ የሆነው ከሰለሞን በኋላ 1150 ዓመታት ያህል ቆይቶ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል። የአክሱምም ሆነ የቅድመ አክሱም ነገሥታት፣ የክርስትና ሃይማኖት በ350 ዓም አካባቢ ከመመሥረቱ በፊት የነበሩት በሙሉ በአምልኮ ጣኦት ይኖሩ ነበር እንጂ የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች እንዳልነበሩ በሚገባ ታውቋል። በተለይ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ነው አቶ አጽሜ በኢትዮጵያ ያለውን ሃይማኖት «በአሪት ቅመም የተቀመመ፣ በአረመኔ ቅቤ የተጣፈጠ ክርስትና ነው» ብለው በረቀቀ አንደበት ሂስ ያቀረቡት።

ተረቱ መቼ እንደጀመረ ቁርጥ ያለ መረጃ ገና የለንም። ግን ከአክሱም ዘመነ መንግሥት የመጡልን አስተማማኝ ሰነዶች አይጠቅሱትም። ይህም በዚያን ዘመን ተረቱ ገና እንዳልተፈጠረ ያመለክተናል። ለመጀመሪያ ጊዜ ሁኔቱ ከኢትዮጵያ ጋራ ተያይዞ የምናገኘው በ350 ዓም አካባቢ ባንድ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጽሐፍ ነው፣ ማለትም የአክሱም መንግሥት ከወደቀ በኋላ፣ 'የጨለማ ዘመን' ተብሎ በሚጠራው ዘመን። ይህም መሆኑ አያስደንቅም። ምክንያቱም እንደዚህ ያሉ ተረቶች የሚያብቡት ተጨባጭ የታሪክ መረጃ በማይገኝበት 'በጨለማ ዘመን' ነው። በሀገር ውስጥ የመንግሥት ኃይል ወድቆ የሥነ ጽሑፍ ሥራ ተዳክሞ የትምህርት ተቋሞች ተበታትነው፣ የታሪክ ቅርስ ለማቆየት በማይቻልበት ጊዜ ነው በተለይ አፈታሪክ የሚስፋፋው። ከዓመታት በኋላ በጽሑፍ ይሰፍርና ይተላለፋል፣ ሥር ይሰዳል። የንግሥት ሳባና የቀዳማዊ ምኒልክ ተረት መልክ ይዞ በመጽሐፍነት ተቀናብሮ፣ ክብረ ነገሥት በሚል አርዕስት የተጻፈው በአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመን

(1313-44) መሆኑ ተረጋግጧል። ያጸጸፉም ዋና ሂደት በአደፋ/ላሊበላ መንግሥትና በኋላ ሰለሞናዊ ነኝ ብሎ በሚነሣው አዲስ ሥርወ መንግሥት መካከል ከነበረው የሥልጣን ትግል ጋር የተያያዘ መሆኑን ብዙ ነጥቦች ያመላክቱናል። የሰለሞናዊያን ንግሥና ከተቋቋመ በኋላ የሕገ መንግሥትነት ባሕርይ አግኝቶ አጼ ኃይለ ሥላሴ (1930-74) ከሥልጣን እስኪወርዱ ድረስ ይቆያል።

ሌሎችም በተመሳሳይ ዓይነት የተፈጠሩ ተረቶች በታሪካችን ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ ያላቸው ሞልተዋል። የፈላሾች ጥንታዊ አይሁድነት ጉዳይ አንደኛው ነው። በየመጽሐፉ ጉዲት እየተባለች የምትጠራዋ ሴትም በሚነገርላት ታሪክ አንፃር እንዲያው የተረት ፈጠራ ናት። በዚያው 'የጨለማ ዘመን' በተባለው ጊዜ ነው የተፈጠረችው። የአክሱምን ትልቅ ኃይል አውዳደቅ በተጨባጭ ታሪክ ማስረዳት ሲያውክ አንድ የታወቀች ሴት ከሌላ ዘመን ከሌላ ሕዝብ ከሌላ አካባቢ ተወስዳ በአክሱም ታሪክ ላይ የተወረወረች ኀበዝ መሪ ናት።

ስለነዚህ ትረታዎች ይዘት መሠረታዊ ችግር ትክክለኛውን መስመር የሚያመለክቱ አንዳንድ የታሪክ ጸሐፎች ቀርበዋል። ነገር ግን የእምነት ኃይል ጠንካራ ስለሆነ ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ አክሱማዊነት የዘውድ ሥርዓት ደጋፊ ከሆኑ ግለሰቦች ጀምሮ እስከ ተራ ቤተሰቦች ድረስ ይነገራል። ካሁኑም ይተርተዋል። በገና ደርዳሪውም ሥነጥበቡ ከዚያ የተገኘው ነው እያለ ያወሳናል። የጉዲትም ተረት መነገር ቀጥሏል። እዚህ ላይ ማንሳት የተፈለገው ዋና ነጥብ ከአባቶች የሚነገሩን አፈ ታሪኮች ሁሉ እንዳሉ እንደታሪክ መወሰድ እንደሌለባቸው፥ በታሪክ ምርምር ዘዴ አስተማማኝነታቸው መለካት እንደሚችልና ትክክለኛ ሥፍራቸውን ማግኘት እንደሚገባቸው ነው። ይልቁንም አሁን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የሚወስኑበት ሥርዓት በተዘረጋበት ጊዜ የየብሔረሰቡ ምሁራን የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። ያልተጣሩ ተረቶችና አፈታሪኮች ይዞ መሯሯጥ ለሕዝቡ የዘለቄታ ታሪክ ይዘት ጥፋት እንደሚያወጣ መገንዘብ ያሻል።

## የክርስትና ታሪካዊ መነሻና ትምህርት

ከዚህ በላይ በቀረቡ የጥናት ርዕሶችና ትችቶች በአንድ በኩል በ330 የክርስትና ሃይማኖት ወደ አክሱማውያን አገርና ቤተ መንግሥት ከመግባቱ በፊት ለ1260 ዓመታት በኢትዮጵያ መለኮታዊ የኦሪት ሃይማኖትና ሕግ ነበር የሚለው የክብረ ነገሥትና የእነአለቃ ታዬ ተዛማጅ መጻሕፍት ትምህርት ላለፉት ሰባት ምዕተ ዓመታት (1270-1974) በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በእጅጉ ተስፋፍቷል።

በሌላ በኩል በተጠቀሰው ረጅም የታሪክ ዘመን በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክና የላቲን ቋንቋዎች በልዩ ልዩ





ስፍራዎች፥ ጊዜያት፥ መንገዶች፥ መሣሪያዎችና ምክንያቶች የተቀረጹ የታሪክ መረጃዎች የኢትዮጵያ ጥንታዊ ደአማታውያን፥ ትሮጆሎዳውያን፥ አክሱማውያን፥ የሐርላ፥ የሀዲያ፥ የጎንጋ ሕዝቦችና መንግሥታት ሁሉም በየአካባቢያቸውና በየዘመናቸው ገና አዋማዊ አማልክትንና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ሕዝቦች እንደሆኑ ያሳያሉ።

በመሆኑም ከመካከለኛው ምስራቅ በአውሮፓዊ ግሪኮ-ሮማውያን ፍሬምናጦስና አዶስዩስ አማካይነት መለኮታዊ የክርስትና ሃይማኖት በ330 ዓም ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ቀጥሎም በ5ኛው ምዕተ ዓመት አረጋዊ፥ ጰንጠሌዎን፥ ገሪማ፥ ሊቃኖስ፥ ይምአታ፥ ፅሕማን፥ ጉባ፥ አፍጼና፥ አሌፍ የተሰኙ ጻድቃን በአክሱም ከተማ መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ከመተርጎማቸው በፊት የኦሪት ሃይማኖትና ሕግ በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት መገኘቱን የሚያመለክት የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ ገና አልተገኘም።

በዚህ ረገድና ተግባር በዓመተ ዓለም ከ2100 አካባቢ ጀምሮ ለ2000 ዓመታት ማለትም ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ ድረስ በመካከለኛው ምስራቅና በግብፅ በረሀብና በጦርነት ችግሮች ዘወትር ከአገር ወደ አገር ሲሰደድና ሲጓዝ እንደኖረ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚነገርለት ሴማዊ የይሁዳውያኑ እናሳ ዘላን ሕዝብ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከጥንታዊ የፑንት-ኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጋር በንግድ ሆነ በባህል ወይም በሃይማኖት በምንም መስክና መንገድ ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረጉን የሚያሳይ አንዳችም የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ የለንም።

በሌላ በኩል በእስትራቴጂያዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የፑንት-ኢትዮጵያ ነባር ሕዝብና መንግሥት በዓመተ ዓለም ከ2800 አካባቢ ጀምሮ እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ በድምሩ ቢያንስ ለ3440 ዓመታት ከሦስቱ ታላላቅና ተከታታይ የግብፅ፥ የግሪክና የሮማውያን መንግሥታትና ሥልጣኔዎች ጋር በንግድ፥ በባህልና በሃይማኖት በየዘመኑ የቀረበ መስተጋብርና መወራረስ እንደነበረው በዚህ ጥናት ከላይ በተጠቀሱ የሃይሮግላፊክስ፥ የግሪክና የላቲን መረጃዎች በሥፍራ፥ በጊዜና ተግባር ቀመር ውስጥ በትክክል ተረጋግጧል።

ከላይ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው በዓመተ ዓለም ከ2800 እስከ 1000 ድረስ ለ1800 ዓመታት በመር ከብና በሲራራ የንግድ ጉዞዎች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከፑንት-ኢትዮጵያ ምድር ወደ ግብፅ በሚወሰዱ ብዙ ዓይነት የማዕድን፥ የእንስሳት፥ የአዝዕርት፥ የእፅዋት፥ የአዕዋፍና የአራዊት ምርቶች ዝርዝር ልዩ ልዩ የብረታብረት፥ የወርቅ፥ የብር፥ የነሐስ፥ የመድሐኒትና የጌጣ ጌጥ ዕቃዎችና

ቀለሞች፣ የሙጫ፣ የዕጣን፣ የከርቤ፣ የቀረፋና የዝንጅብል ቅመማ ቅመም፣ የዝሆን ጥርስ፣ የአውራሪስ ቀንድ፣ የሰጎን ላባና እንቁላል፣ ድብና የድብ ቆዳ፣ ቀጭኔ፣ ቀበሮ፣ ዝንጀሮ፣ ሶሎግ ውሻ፣ አህያ፣ በሬ፣ ጥጃ፣ ልዩ ልዩ የእንጨት ምርቶች ለዓይነት የሚጠቀሱ የክፍለ አህጉሩ የተፈጥሮና የእርሻ ሀብቶችና ምርቶች ናቸው።[47]

በዓመተ ዓለም ከ332 እስከ 30 ድረስ ግብፅን በቀጥታ ይዘው ለ300 ዓመታት የገዙ ግሪኮች ቀክፍለ አህጉሩ በቀይ ባሕር፣ በኤደን ባሕረ ሰላጤና በሕንድ ውቅያኖሲ ጠረፎች ላይ ቋሚ የንግድ ኬላዎችን፣ ከተሞችንና ዘበያዎችን መስርተው በንግድ በባህልና በሃይማኖት ከግብፅ፣ ከመካከለኛው ምስራቅና ከሜዲትራኒያን ባሕር ሕዝቦችና ሥል ጣኔዎች ጋር በቅርብ በማገናኘት በተጠቀሱ ጥንታዊ የአፍሪካ፣ የእስያና የአውሮፓ ሕዝቦችና በኢትዮጵያ አዳጊ የአክሱም መንግሥት መካከል በንግድ፣ በባህልና በሃይማኖት የመጀመሪያ ግንኙነቶችን ፈጠሩ።

ቀጥሎም ከ30 ዓመተ ዓለም እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ በግሪኮች እግር ተተክተው ግብፅንና አካባቢውን እስከ እስላማዊ የአረቦች ዓለማቀፋዊ እንቅስቃሴ ድረስ ለሰባት ምዕተ ዓመታት የገዙ ሮማውያን በአራቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ የዓባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕርና የአረቢያ እስትራቴጂያዊ አካባቢዎች ላይ ለአክሱም መንግሥት እና ሥልጣኔ ዕድገትና መስፋፋት ብሎም ለሶስቱ መለኮታዊ የክርስ ትና፣ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ መግባት ምቹ ሁኔታዎችንና መንገዶችን ፈጠሩ።

ከዚህ በላይ ባጭርና በጥቅል ለቀረቡት የጥንታዊ ግብፃውያን፣ ግሪኮችና ሮማውያን ተጨባጭ ግንኙነቶች በኢትዮጵያ ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ ተገቢ ግምትና ዋጋ አልተሰጠም። በሌላ በኩል ግን በግሪኮ-ሮማውያን ምዕመናን ትምህርትና አመራር ሁለቱ የክርስትናና የኦሪት ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊትም ሆነ በኋላ ከኢት ዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ጋር በምንም ሥፍራ፣ ጊዜና መንገድ ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ግንኙነት ሳልነበረው የይሁዳውያኑ ዘሳን ሕዝብና ታሪክ በዘመነ ክርስትና ከ1270 ወዲህ ከዚህ በላይ በተዛማጅ የክብረ ነገሥትና የአለቃ ታዬ መጻሕፍት የቀረበውና ከኢትዮጵያ የታሪክ እውነታና እውቀት ጋር በፍጹም አብሮ የማይሄድ ታላቅ ሃይማኖታዊ ግምት ተሰጥቷል።

በዘመነ ክርስትና በ4ኛው ምዕተ ዓመት በሶሪያ አገር የጢሮስ ከተማው ሩፊኑስ የተባለው የሃይማኖት አስተማሪ ከአገሩ ፍሬምና ጦስና አዶስዩስ የተባሉ ሁለት ግሪኮሮማዊ ስደተኛ ነጋዴዎች በ330

[47] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ ገጽ 58።





አካባቢ የአክሱምን አዋማዊ ቤተ መንግሥት ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንደለወጡና በኋላ ከሁለቱ ስደተኞች አንዱ ማለትም ፍሬምናጦስ በእስክንድርያ ከተማ በግብፁ ቤተ ክርስቲያን መሪ በፓትርያርክ አጥናቴዎስ (328-356) የአክሱማውያን ቤተ ክርስቲያን አስተማሪና መሪ ተደርጎ እንደ ተሾመ በትክክል ጽፏል።[48] በፍሬምናጦስ-አዶስዩስ ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተለወጠው የአክሱም የመጨረሻው አዋማዊና የመጀመሪያው ክርስቲያን ንጉሥ አጼ ኢዛና እንደሆነ ንጉሡ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከመግባቱ በፊትና ከገባ በኋላ በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች ከጻፋቸው ዜና መዋዕሎች በትክክል ታውቋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ እስከ ዛሬ ድረስ በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች በድንጋይ ሐውልቶች ላይ የተፃፉና የንጉሡን ወታደራዊ ዘመቻዎች የሚገልፁ ብዙ ታሪካዊ የአጼ ኢዛና ዜና መዋዕሎች ተገኝ ተዋል።[49] ከ330 ዓም በፊት ገና አዋማዊ በነበረ ዘመን በተጻፉ ዜና መዋዕሎቹ አጼ ኢዛና «አባቶቼ» ለሚላቸውና አርስ፣ መሕርም፣ አስተር፣ ብሔርና ምድር ተብለው በአገርና በዓለም ደረጃ ለሚታወቁ አምስት አዋማዊ አማልክት ከብርና ምስጋና አምስት የወርቅ፣ የብርና የመዳብ ሐውልቶችን እንዳቆመላቸው በጽሑፎቹ ተገልጿል።

ነገር ግን በመጨረሻ አጼ ኢዛና ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከገባ በኋላ በሁለቱ የግዕዝና የግሪክ መንግሥታዊ ቋንቋዎች ተጽፎ በቅርቡ (1969) በአክሱም ከተማ በተገኘ በአንድ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፍ በግሪኩ ቅጅ በፊት «አባቶቼ» የሚላቸውን ከላይ የተጠቀሱ አዋማዊ አማልክትን ትቶ አሁን «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ... በእግዚአብሔር ልጅ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ»[50] በተሰኘ አዋጁ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ክርስቲያን ንጉሥ መሆኑን ለትውልድና ለታሪክ በይፋ አሳውቋል።

ከዘመኑ የታሪክ መረጃዎች እንደሚታወቀው፣ የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአንድ በኩል በአገሪቱ ጥንታዊና አዋማዊ መንግሥት ምርጫ፣ ፈቃድና አመራር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በህብረተሰቡ ነባር ሥልተ ምርትና ሥርዓተ ማኅበር ላይ አዲስ ማህበራዊ የለውጥ ሁኔታና ሂደት አላመጣም።

[48] A. H. M. Jones and E. Monroe, A History of Ethiopia, (London L OUP, 1966), pp. 26-27.

[49] Littmann, DAE, Inscriptions Nos. 4, 6-11; Kammerer, Essai sur L' Histoire, pp. 89-97; "Christian Inscription of Ezana", S. Hablesellassie, History, p. 103.

[50] Ibid., "Christian Inscription".

በመሆኑም የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ነባሩ አዋማዊ ህብረተሰብና መንግሥት ዘንድ በባህል ሆነ በእምነት ወይም በፖለቲካ ሥርዓት ተጓዳኝና ተዛማጅ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ፣ ለውጥና ውድ ቀት አላስከተለም። እንዲያውም በተቃራኒው ራሱን ከአገሪቱ ነባር አዋማዊ ሃይማኖት፣ ባህልና ሥርዓት ጋር በማቀናጀትና በማዋሃድ ከላይ በተጠቀሰው በአቶ አፅሜ ጥናት እንደተባለው «በአሪት ቅመም የተቀመመ በአረመኔ ቅቤ የተጣፈጠ» የኢዎማዊዝም፣ የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች፣ ባህሎችና ትምህርቶች ቅይጥ ሥርዓት ይሆናል።

## በኢትዮጵያ የክርስትና አባት አስተማሪዎች

በኢትዮጵያ ለአዋማዊዝም፣ ለክርስትናና ለአሪት አማልክት፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ሥርዓታዊ መስተጋብር፣ መወራረስና ውህደት ብሎም ለኢትዮጵያ ጥንታዊና ዘውዳዊ የፖለቲካ ሥርዓት ቀጣይ ህልውና፣ ዕድገትና መስፋፋት በ5ኛውና በ6ኛው ምዕተ ዓመታት በግምት ከ470 እስከ 550 ድረስ ባለው የስምንት አሥርታት ዘመን ውስጥ ታላቅ ድርጅታዊ፣ ትምህርታዊና ባህላዊ አስተዋጽኦ ያደረጉ ብሎም የኢትዮጵያ የሕዝብና ያገር ባለውለታዎች የሆኑ ከላይ የተጠቀሱት ግሪኮ-ሮማዊ ጻድቃን ናቸው።

አንደኛ፣ የተጠቀሱት ጻድቃን መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተረጎሙ። የጻድቃኑ የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ለሁለቱም የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች ዕድገት ትምህርታዊ፣ ባህላዊና ድርጅታዊ መሠረትና መሣሪያ ይሆናል።

ሁለተኛ፣ የተጠቀሱ ግሪኮ-ሮማዊ የሃይማኖት ምሁራን የግዕዝ ቋንቋን ታላቅ የሥነጽሑፍ መሣሪያ አድርገው በመግባት በኢትዮጵያ ለመንግሥትና ለሃይማኖት ሥርዓቶች ዕድገት እና መስፋፋት ብሎም ለአገሪቱ የባህልና የሥነ ጽሑፍ ድርጅታዊ ህልውና ወሳኝ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ እሙን ነው።

ሦስተኛ፣ በምሥጢረ ሥላሴ እምነታቸውና ትምህርታቸው ምክንያት ከአገራቸው መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን መከራና ሥቃይ ደርሶባቸው በሽሽት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ስደተኛ ምሁራን በተጨማሪ በአገሪቱ የገዳምና የምንኩስና ሥራና የአሪት ሥርዓት በማቋቋም ለተዛማጅ የክርስትናና የአሪት ሃይማኖቶች ዕድገትና መስፋፋት ሌላ ድርጅታዊ መሠረት፣ መንገድና መዋቅር ገነቡ። በዚህ ረገድና ተግባር በአክሱምና አካባቢው እስከ ዛሬ ድረስ ለኢትዮጵያ የክርስትና ትምህርትና ባህል መሠረቶችና ማዕከላት የሆኑ ደብረዳሞ፣ አባ ገሪማና የመሳሰሉ ታሪካዊ የገዳም ተቋማትን መሠረቱ።





በዚህ የኢትዮጵያን ታላቅ የክርስትና ሃይማኖትና ባህል ግምባታ ተግባር በሚመለከት በግምት ከ330 እስከ 550 ድረስ በመጀመሪያ 220 ዓመታት ዘመን ከላይ በስም ከተጠቀሱት ግሪኮሮማዊ አስተማሪዎች ጋር የኢትዮጵያ አጼ ነገሥታት ኢዛና (320-44)፣ አላአሜዳ (478-86)፣ ታዜና (486-93)፣ ካሌብ (493-534) እና ገብረ መስቀል (534-548) ከታላቁ የሃይማኖት ምሁር ያሬድ ጋር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሥራችና ገምቢ አባቶች እንደሆኑ ለምን ጊዜም በትውልድና በታሪክ ዘንድ ሙሉ እውቅና የማይነፈግ የታሪክ እውነታና እውቀት ነው።

## የኢትዮጵያ የ550-1300 'ጨለማ' ዘመን

በግምት ከአክሱሙ ንጉሥ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት (534-548) እስከ ሰለሞናዊ ንጉሥ አምደፅዮን ዘመነ መንግሥት (1314-1344) ድረስ በስምንት ምዕተ ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ሆነ ቤተ ክህነት በወቅቱ የተጻፉ የነገሥታት ዜና መዋዕሎችና የጻድቃን ገድሎች ማለትም የታሪክ መረጃዎች የማይገኙ በት ረጅም «የጨለማ[51] ዘመን» ነው።

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊ በአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ቃል «አሁን ያለው የአክሱሙም የዛጉየውም ታሪክ መዘጋጀት የጀመረው በ14ኛው መቶ ዓመተ ምህረት ላይ በአጼ አምደፅዮን ጊዜ ነው። ታሪክ ነገሥታት የምንለው በየበኩሉ ወይም በየዘመኑ አንዳንድ የዘመኑ ሊቅ ያዘጋጀው»[52] ዜና መዋዕል ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎችን አጠቃላይ የታሪክ መረጃ፣ ሥልትና ትምህርት በሚመለከት ከአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በቀረበው ሂስ እንደተባለው፣

> *ክርስትና ከገባ ወዲህ በአክሱምም በላስታም በሸዋም በጎንደርም የነበሩ የኛ ሊቃውንትና ጸሐፊዎች ከቤተ ክህነት መንፈሳዊና ከቤተ መንግሥት ዘመናዊ አገልግሎት ወይም የነገሥታቱን ዜና መዋዕል ከመጻፍ በቀር ይልቅኑም ከጽርዕ (ከግሪክ) ከዕብራይስጥ ከአረብና ከኮፕት እንደሰንኩሳር እንደ ሃይማኖተ አበው እንደግንዘት የመሳሰለውን መንፈሳዊ ጽሑፍ ከመተርጎምና ከመገልበጥ በቀር በታሪክ ረገድ መመርመርና መጻፍ መሰብሰብ እየሰበሰቡም በቀድሞው ላይ መጨመር ምንም ያህል አስፈላጊነቱ በዚያን ጊዜ የተሰማቸው አይመስልም። ያለውን በቂ አድርጎ በመመልከት በአክሱምና በዙሪያው በአዱሊስ በከስከሴ በየሀ በቆሃሂት ታሪካዊ ጽሑፍ ተሸክም ቆሞ*

[51] Budge, History, pp. X-XI, 204, 563

[52] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ አክሱም ዛጉዌ፣ (አዲስ አበባ፣ 1966) ገጽ 344።

*ይኖር የነበረው ልዩ ልዩ ሐውልትና ዙፋን በዘመን ብዛት የቆመው ሲወድቅ የወደቀው ከነጽሕፈቱ ለመበስበስ ሲደርስ የነገሩን ቁም ነገረኛነት ተመልክቶ የሐውልቱን ሥዕል ለማንሣት ጽሑፉን ለማስገልበጥና ለመገልበጥ ለመተርጐም በፊተኛው ዘመን የሞከረ ከኛ ወገን የለም።*[53]

በተጠቀሰው ረጅም የ550-1300 'ጨለማ' ዘመን በወቅቱ በአጎራባቹ የአረብ ዓለምና ሕዝቦች ዘንድ በዘልማድ «ሀበሻ» ብሎም በኋላ በአውሮፓውያኑ ትርጉም «አቢሲኒያ» ተብሎ በሚጠራው በዛሬው የሰሜን ኢትዮጵያ ተራራማ ክልል የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት፣ «የፈላሻ» ሕዝብ የኦሪት ሃይማኖት፣ ክስተትና ዕድገት፣ የአገው ክርስቲያን መንግሥትና የገዥው መደብ ዕድገትና ውድቀት እንዲሁም በመጨረሻ በ1270 በሁለት የአማራ መነኩሴዎች ኢየሱስ ሞዓ እና አቡነ ተክለሃይማኖት ትምህርት ይኩኖ አምላክ በተሰኘው የጦር አበጋዝ መሪነት በከነዓን ከጥንት ይሁዳውያኑ «ምርጥ» የአብርሃም፣ የሙሴ፣ የዳዊት፣ የሰለሞን ዘር በመሆኑ የአገው ዘውድና ዙፋን ሕጋዊ ወራሽ ነኝ ብሎ ራሱን የሰየመው አዲስ «ሰለሞናዊ» መንግሥትና የገዥው መደብ ክስተትና ዕድገት የመሳሰሉ ታላላቅ የፖለቲካ ሁኔታዎች፣ ኃይሎች፣ ሂደቶችና እንቅስቃሴዎች እንደተካሄዱ፣ እንደ ተፈጸሙ፣ በተረት መልክና መንገድ ይታወቃል። የተጠቀሱ ሁኔታ ዎችንና እንቅስቃሴዎችን መነሻ፣ ተዋንያን፣ ክስተትና ዕድገት አስመ ልክቶ በወቅቱ የተመዘገቡ ተጨባጭ የታሪክ መረጃዎች እስከዛሬ ድረስ ስላልተገኙ የዘመኑ ታሪክ በሙሉ የተረት ቅኝት ሆኖ ቀርቷል።

## የክርስትና የዕድገትና የመስፋፋት ዘመን 1270-1524

በ470-550 ዘጠኙ ጻድቃን በአንድ በኩል መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በመተርጐም፣ በሌላ በኩል ደግሞ የገዳምና የምንኩስና ሥርዓት በማቋቋም ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በአክሱም ከተማና አካባቢው በጠንካራ መሠረትና መንገድ እንደገነቡት ይታውሳል።

አሁን ደግሞ ከላይ ከተመለከተው የጨለማ ምዕተ ዓመታት ዘመን በኋላ በ1270 በመሀል ሰሜን በምድረ አማራ (በቤተ አማራ) ማለትም በዛሬው የወሎ ክልል የአገውን የክርስቲያን መንግሥትና የገዢው መደብ አጥፍተው የመንግሥት ሥልጣን የያዙ ሰለሞናዊ ነገሥታትና ካህናት በብዙ አዳዲስ የወንጌል፣ የድርጅት፣ የፖለቲካ፣ የትጥቅና የሥነጽሑፍ ሥራዎች በመሀል የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የአዋማዊዝም፣ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶችን

[53] Ibid., pp. 102-103





ከሚከተሉ ብዙ ነባር ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር ዘውትር እየተዋጉ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁለተኛውንና ታላቁን የዕድገትና የመስፋፋት ዘመን (1270-1524) ፈጠሩ።[54]

በዚህ ረገድና ተግባር አንደኛ፣ በተጠቀሰው የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና መስፋፋት ዘመን መባቻ ላይ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ያገር ተወላጅ የሃይማኖት መምህራን ማለትም የሐይቁ ገዳም መምህር ኢየሱስ ሞዓ (1211-1292) በመሀል ሰሜን፣ የደብረሊባኖሱ ገዳም መሥራች አቡነ ተክለሃይማኖት (1215-1313) በደቡብ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ሰንበት[55] መሥራች መነኩሴ አዎስጣጤዎስ (1273-1352) በሰሜኑ ክልል፣ በየአካባቢያቸውና በየዘመ ናቸው የቤተ ክርስቲያኑ ጠንካራ አስተማሪዎች ሆነው ተነሱ።

እነዚህ የብተ ክርስቲያኑ ብርቱ አስተማሪዎች ከብዙ ተማሪዎቻ ቸውና ተከታዮቻቸው ጋር በጥንቱ ዘጠኝ ጻድቃን ጅምር የወንጌል፣ የገዳምና የግዕዝ ሥነጽሑፍ ሥራዎች መሠረትና ሞዴል መመሪያ በክፍለ አህጉሩ መሀል አካባቢዎች በየክልላቸው የየራሳቸውን ብዙ አዳዲስ የወንጌል፣ የገዳምና የግዕዝ ብራና ጽሑፍ ሥራዎችን እንቅስ ቃሴዎችና የአሠራር ሥልቶች አዳብረው በመጠቀም በተጠቀ ሰው ዘመን የክርስትና ሃይማኖትን በሰሜን ከምፅዋ-ሐማሴን በምዕራብ እስከ ጎጃም፣ ዳሞትና እናርያ ገዳማትን እንደመሠረቱ በዘመኑ በብዙ የኢትዮጵያ፣ የአረብና የአውሮፓ ጸሐፊዎች በልዩ ልዩ ሥፍራዎችና ጊዜያት የተጻፉ የታሪክ መረጃዎች ያሳያሉ።[56]

ሁለተኛ፣ በዚህ የክርስትና ሃይማኖት ዕድገት እና መስፋፋት ጉዳይ፣ በወደቀው የአገው መንግሥትና የገዢው መደብ ላይ ከቤተ ክርስቲያኑ አመራር ጋር የፖለቲካ ጥቅምና ትብብር የነበራቸው፣ ራሳቸውን «ምርጥ» የሰለሞን ዘርና የዘውድ ወራሽ ነጋሢያን ነን ብለው የሰየሙ አፄ ነገሥታት በተለይ ይኩኖ አምላክ (1270-1285)፣

[54] Taddesse Tamrat, "The Abbots of Dabra-Hayq", 1248-1535", JES? Vol. 8, No. 1 (1970), pp. 87-117; ibid., Church and State in Ethiopia 1270-1527 (London: OUP, 1972).

[55] Ibid., Church and State, pp. 206-207.

[56] Ibid., Champs. 5, 6; Ibn Fadl A. Umari, Masalik El Absar fi Mamalik El Masar, tr. and ed., G. Demombynes, (Paris, 1927); Maqrizi, The Book of the few knowledge of the Moslem Kings in Abyssinia, tr. by G. W. B. Huntingford (Typescript, 1955); Crawford, Itineraries; Arabfaqih, Conquete; F. Alvarez, The Prester John of Indies, 2 Vols., trs and ed., C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford (1961); Bahrey, History of the Galla, C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford, trs. and eds., Some Records of Ethiopia 1593-1646, (London: 1954).

ዓምደፅዮን (1314-1344)፣ ዳዊት (1372-1413)፣ ይስሐቅ (1414-29)፣ ዘርዓያዕቆብ (1434-68) እና በዕደማርያም (1468-78) በክፍለ አህጉሩ የአዋማዊዝም፣ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ነባር ሕዝቦችንና መንግሥታትን በክርስቲያኑ ግዛት ሥር በማምጣት ለክርስትና ሃይማኖት ዕድገትና መስፋፋት የበለጠ አመቺ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ፈጠሩ።

ከዚህ በላይ ባጭርና በጥቅል የቀረበውና ከዘመነ አክሱም ጀምሮ በ16ኛው ምዕተ ዓመት እስከ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ ግራኝ የአመፅ ጦርነት ድረስ ለረጅም ዘመን በክፍለ አህጉሩ ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ወደ ምዕራብና ወደ ምስራቅ አካባቢዎች የተካሀደው የክርስቲያን ሃይማኖትና መንግሥት የዕድገትና የመስፋፋት እንቅስቃሴ በታላቁ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለዛሬው የኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ኅብረ ተሰብና መንግሥት ዕድገት ታሪካዊ መነሻዎችና መሣሪያዎች ከሆኑ ብዙ ታላላቅ ሕዝባዊ የፍለሳ፣ የጦርነት እና የሰፈራ እንቅስቃሴዎች አንዱና የመጀመሪያው ሆነ።





# 3. የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻ፣ ዕድገትና ውድቀት

## የሰሜን/ፈላሻ የጂኦ-ፖለቲካ ታሪካዊ ፋይዳ

ራሱን «አይሁድ» እና «ቤተ እሥራኤል»[57] ብሎ በተለዋጭ ስሞች የሚጠራውና በሌላ በኩል ደግሞ ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት መዛግብት ብሎም በውጭ ሰዎች «ፈላሻ»[58] ማለትም ስደተኛ፣ መጤ፣ ባዕድ ተብሎ የሚታወቀው የኢት ዮጵያ አንድ የጎንደር አማራ ማኅበረሰብ ሲሆን አሁን በቅርቡ በመካከለ ኛው ምስራቅ የጥንት አገሬና ሕዝቤ ወደሚለው ወደ እሥራኤል አገር ከሞላ ጎደል ጠቅልሎ በፍለሳ ገብቷል።

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የጥንቱ ታሪክ የማህበረሰቡ እውነተኛ ስምና አገሩ አይሁድም፣ ቤተ እሥራኤልም፣ ፈላሻም፣ አማራም፣ ሳይሆን «ሰሜን» እንደሆነ የታሪክ መረጃና ትምህርት በሥፍራና በጊዜ መስፈርት ያሳያል። በዚህ ረገድና ተግባር በዘመነ ክርስትና በቅደም ተከተል በ300ዎቹና በ320ዎቹ አሥርታት አካባቢ በግሪክና በግዕዝ ቋንቋ ዎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው በተገኙ የአክሱም አዋማዊ ነገሥታት ዜና መዋዕሎች መሠረት የማህበረሰቡ እውነተኛ ስምና አገር «ሰሜን» ነበር። አገሩም በዛሬው ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተከዜና በዓባይ ወን ዞች የመነሻ ክልል ታላቁ የሰሜን ተራራ በሚገኝበት በዘመኑ የአክሱም መንግሥትን በምዕራብና በደቡብ ከመሀል አገር ሕዝቦችና ግዛቶች ጋር የሚያገናኝ አንድ ቁልፍ እስትራ ቴጂያዊ የጂኦፖለቲካ ምድር ነበር።

ከዚህ አኳያ በ300ዎቹ በአዱሊሱ የቀይ ባሕር ወደብ ከተማ ላይ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈበትን የድል ሀውልት «አባቶቼ» ለሚላቸው የግሪክ አማልክት አርስ፣ ዜዑስና ፖሲዶን መታሰቢያ ያቆመው አንድ አዋማዊ የአክሱም ንጉሥ በነገሡ በ27ኛ ዓመት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ በላይኛው የዓባይ ሸለቆ፣ በቀይ ባሕርና በአረቢያ በአራት ወታደራዊ እርምጃዎች የግዕዝን፣ የአጋሜን (የኢጋዚን)፣ የአገውን[59] (የአታገውስን)፣ የስጌን (የዛጋሬን)፣ የአድዋን፣ የሰሜንን[60]

57 Wolf Leslau, Falasha Anthology: The Black Jews of Ethiopia, (New York, 1951); pp. IV-X

58 Huntingford, Amba Seyon, pp. 61-62.

59 Cosmas, Christian Topography of Cosmas, tr. & ed., J. W. MaCrindle (London, 1897); p. 61.

60 Ibid.,

(የፈላሻን) የቤጃን፣ በምዕራባዊ አረቢያ ጠረፍ በለኡኮመና በኤደን የወደብ ከተሞች መካከል ደግሞ የአራብቱንና የኪናይኮደልፕቱን አገሮች ጨምሮ በአራቱ አኅራባች አካባቢዎች በድምር በ30 የሚቆጠሩ አሮችንና ሕዝቦችን ባገሩ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በምድርና በመርከብ ዘመቻዎች እንዴት እንዳስገበራቸው በሐውልቱ ሰነድ ይተርካል።

የአክሱምን ግዛተ አፄ በሁለቱ አኅራባች የአፍሪካና የእስያ አህጉራት ላይ መሥራች እንደሆነ የሚነገርለት ይህ የአክሱም ንጉሥ በአክሱምና በላስታ አካባቢዎች የግዕዝን፣ የአጋሜን፣ የአድዋንና የአገውን አገሮች ጨምሮ ብዙ ሉአላዊ መንግሥታትን ካስገበራቸው በኋላ ከአክሱም ከተማ በደቡባዊ ምዕራብ አቅጣጫ የተከዜን ወንዝ በጦር ተሻግሮ፣ ዓመቱን በሙሉ ዝናብ፣ ብርድ፣ ውርጭና በረዶ በማይጠፋባቸውና ለመውጣትም በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ከፍተኛ ተራሮች ላይ በሚኖረውና «ሰሜን» በሚል የአገርና የሕዝብ ስያሜ በሚታወቀው በአንድ ሉአላዊ ሕዝብና መንግሥት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ያካሄደውን የወረራ ጦርነት በአንክሮ ይገልጻል።

ይህ በአዱሊስ ሐውልት ላይ በንጉሡ ተጽፎ በኋላ በ522 በግሪኩ መነኩሴ ኮስማስ ተገልብጦ ለትውልድና ለታሪክ የተላለፈው የጦርነት ዘገባ በሁለቱ አኅራባች የአክሱምና የሰሜን ሕዝቦችና መንግሥታት መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት ታሪካዊ መግለጫ ነው።

ይህ በጥንቱ አኅራባች የአክሱም ሕዝብና ታሪክ «ሰሜን» በሚል የሕዝብና የአገር ስም የሚታወቅ አንድ ነባር ኩሻዊ መንግሥት ከጥንት ጀምሮ በ16ኛው ምዕተ ዓመት እስከ አፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት (1605-1632) ድረስ በአክሱማውያኑ የደቡብ ምዕራብ ጂኦ-ፖለቲካ ወሰን ላይ በተከዜና በአባይ ወንዞች መካከል የዛሬውን የሰሜን፣ የወልቃይት፣ የፀለምት፣ የወገራ፣ የአርማጭሆ፣ የጭልጋ፣ የደምቢያና የቋራ አውራጃዎችን[61] አጠቃሎ በሰሜን ተራራና በጣና እስትራቴጂያዊ ክልል የነበረ አንድ ሉአላዊ አገርና መንግሥት ነው።

በዘመነ ክርስትና በ300ዎቹ በአዱሊስ የወደብ ከተማ ላይ የድል መታሰቢያ ሐውልት ያቆመው የአክሱም ንጉሥ በተከዜ-ዓባይ ወንዞች እስትራቴጂያዊ ምድር ላይ ጦርነት ከከፈተበት ጊዜ ጀምሮ

[61] Teklesellassie, Susnyos 1605-1632, Champs. 41-44; R. Hess, "An Outline of Falasha", Proceedings of the 3rd International Conference of Ethiopia Studies, (1966), pp. 99-112; Ibid., "Chapter 4: Toward A History of the Falasha", Deneil F. McCaall, ed., Eastern African History, (1969); pp. 107-132; Taddasse Tamrat, Church and State, pp. 196-201.





እስከ 1632 ድረስ ለ14 ምዕተ ዓመታት የሰሜን ሕዝብና መንግሥት ከተከታታይ የአክሱም፣ የአገውና የአማራ ነገሥታት ጋር የመከላከል ጦርነት ሲያካሄድ እንደኖረ በድንጋይና በብራና ላይ የተጻፉ የዘመናቱ የታሪክ መዛግብት በግልጽ ያሳያሉ።

በዚህ ረገድና ተግባር በ300ዎቹ በአዱሊሱ የወደብ ከተማ የድል መታሰቢያ ሐውልትን የተከለው የአክሱም ንጉሥ በሁለቱ የአፍሪካና የእስያ አኅራባች አህጉራት ላይ የጀመረውን የአጼ መንግሥት ግምባታ በ4ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ በሁለአቀፍ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የትምህርት ፖሊሲዎችና እርምጃዎች ወደ ከፍተኛ የዕድገትና የመስፋፋት ደረጃ ያደረሰው የአሌአሜዳ ልጅ አጼ ኢዛና ነው።[62]

የአጼ ኢዛና ታሪክ ዋና ዋና የመረጃ ምንጮች በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉ ብዙ የንጉሡ ዜና መዋዕሎች እንዲሁም በኢትዮጵያ እና በአረቢያ ከወርቅ ተሰርተው በግሪክ ቋንቋ የተጻፈባቸው ገንዘቦች ናቸው። ንጉሡ በ330 ዓመተ ምህረት ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ገና አዋማዊ በነበረበት ጊዜ በተሠሩ ገንዘቦች ላይ የጨረቃ ምልክቶች፣ ክርስቲያን ከሆነ በኋላ በተሠሩ ገንዘቦች ላይ ደግሞ የመስቀል ምልክቶች ተቀርፀው ይታያሉ። በመሆኑም አጼ ኢዛና የአክሱም የመጨረሻ አዋማዊና የመጀመሪያው ክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ነው።

በዜና መዋዕሎቹ ከአጼ ኢዛና የዙፋን ስም ጋር በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ በላይኛው የአባይ ሸለቆና በአረቢያ በድምሩ አክሱም፣ ሕሜር፣ ራይዳን፣ ኢትዮጵያ፣ ሀበሻ፣ ሳባ፣ ሰልሔን፣ ጽያሞ፣ ቤጃ፣ ካሱ (ሚሮዌ) የተሰኙ የሕዝብና የአገር ስሞች፣ አርስ፣ መሕርም፣ አስተር፣ ብሔር፣ እግዚአ ሰማይ፣ (የሰማዩ ጌታ) አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰኙ አዋማዊና መለኮታዊ የአማልክት ስሞች ጋር በተለያዩ ሥፍራዎችና ጊዜያት በይፋ ተጽፈው ተገኝተዋል።

ባጭሩ ንጉሡ «ሰዎቼ» እያለ የሚጠራቸው መሐዛ፣ ሐራ፣ ደመወ፣ ፊልሐ፣ ፅራእ፣ ሐሌን፣ ምጤን፣ ዳኬን፣ ለኬንና ሰብራት የተባሉ ወታደራዊ ድርጅቶችና «አባቶቼ» የሚላቸው አርስ፣ መሕርም፣ አስተር፣ ብሔርና ምድር የተሰኙ አማልክት በአጼ ኢዛና ዜና መዋዕሎች የመንግሥቱ፣ የዘመኑና የሥርዓቱ ማዕከላዊ ተዋንያን፣ መሣሪያዎችና መግለጫዎች ናቸው።

አጼ ኢዛና በ330 ዓመተ ምህረት የክርስትና ሃይማኖት ከመቀበሉ በፊት ገና አዋማዊ ሳለ የአዱሊስን የድል መታሰቢያ ሐውልት የተከለው ንጉሥ ያገር ግምባታ ፖሊሲና ፕሮግራም በመከተል

[62] Kammerer, Essai Sur L' Histoire. p. 86.

በ320ዎቹ ከላይ የተጠቀሱ የጦር ኃይሎችን አስከትሎ አጉዛት በተባለው በአንድ አመፀኛ የአከባቢ አገርና መንግሥት ላይ ያካሄደው ታላቅ የቅጣት ዘመቻ በሚገልፀው የግዕዝ ቋንቋ ዜና መዋዕሉ ላይ ራሱን፤ «ኢዛና የአሌአሜዳ ልጅ የነገደ ሐሌን የአክሱም፥ የሕሜር፥ የረይዳን፥ የሳባ፥ የሰልሔን፥ የጽያሞ፥ የቤጃና የካሱ (የሚሮዌ) ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕረም ልጅ» ብሎ ይጠራል።[63]

ለሚታዘዙለት ምህረት ማድረግ፥ ሥልጣንና ትዕዛዙን የማይቀበሉትን ደግሞ ያለምሕረት መቅደል ፖሊሲውና ተግባሩ የሆነው የአማል ክት ልጅ ንጉሠ ነገሥት ኢዛና በ320ዎቹ በአጉዛት አገር ላይ ዘመቻ ባካሄደ ጊዜ የአዱሊስን የድል መታሰቢያ ሐውልት ከተከለው ንጉሥ ቀጥሎ ለሁለተኛ ጊዜ የተከዜን ወንዝ በወታደራዊ ዘመቻ ተሻግሮ በሰሜንና በወልቃይት ተዛማጅ አገሮች[64] ላይ የቅጣት ጦርነት እንዳካሄደ በዜና መዋዕሎቹ ይነባባል።

ከጊዜ፥ ከተግባርና ከታሪክ አኳያ፥ በ300ዎቹ በአዱሊስ ከተማ የድል መታሰቢያ ሐውልት ባቆመው ንጉሥና በ1913 በጀርመኑ የቋንቋ ምሁር በፕሮፌሰር ኢኖ ሊትማን (1875-1958) ቁጥር 8 እና ቁጥር 9 ተብለው የተተረጎሙ የግዕዝ ዜና መዋዕሎቹን[65] በፃፈው በአጼ ኢዛና በ320ዎቹ በሰሜንና በወልቃይት አገሮች ላይ በተከታታይ የተካሄዱ ጂኦ-ፖለቲካዊ ጦርነቶች ገና በቅድመ ክርስትና ዘመን አዋማዊ የአክሱም ነገሥታት በተጠቀሱት የአካባቢ አገሮች ላይ የነበራቸውን ቋሚ የመስፋፋት ፖሊሲና ፕሮግራም በግልፅ ያሳያሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በኢትዮጵያ በዘመነ ክርስትና በግምት ከ330 እስከ 1316 ድረስ ማለትም እስከ አጼ አምደጽዮን ጊዜ ድረስ የሰሜን/ፈላሻ ስም፥ ሕዝብና አገር በታሪክ ሰነድ ላይ በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ ተጽፎ አልተገኘም።

በሌላ በኩል በዚህ ወቅት በተለይም ከ330-577 ድረስ የአክሱም ክርስቲያን አገርና መንግሥት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በላይኛው የዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ አጎራባች አገሮችና አካባቢዎች ላይ ለዝቢያና ለኃይል ሚዛን ከዘመኑ ኃያላን የሮማውያንና የፋርሳውያን የአጼ መንግሥታት ጋር የሚወዳደር አንድ ጠንካራ የዓለም ኃይል ሆኖ እንዳደገ ይታወቃል።[66] በመሆኑም በዚህ የሦስት

[63] Ibid., p. 89

[64] Ibid.,

[65] Ibid., pp. 89-90

[66] Y. M. Kobishchanov, Axum, (1979).





ምዕተ ዓመታት የሽግግር ዘመን የአክሱም መንግሥትና ነገሥታት በሰሜን/ ፈላሻ አጎራባች አገር ላይ የመስፋፋት ግፊት አላደረጉም።

ይሁን እንጂ በ577 የአረብ የነፃነት ኃይሎች ከአጎራባቹ የፋርሳውያን ባላንጣ መንግሥት ጋር በኅብረት በአረቢያ የአክሱማውያንን የባሕር ማዶ ግዛት ደመሰሱ።[67] ቀጥሎም ከዚህ በታች በዝርዝር እንደሚታየው፥ ከ632 እስከ 642 ድረስ አዲሱ የአረቦች እስላማዊ ዓለም አቀፍ ኃይልና እንቅስቃሴ በአንድ በኩል በአረቢያ፥ በመካከለኛው ምስራቅና በግብፅ የሮማውያንንና የፋርሳውያን መንግሥታት ደመሰሰ።[68]

በሌላ በኩል ደግሞ አክሱማውያን በቀይ ባሕርና በላይኛው የዓባይ ሸለቆ በሮችና ጠረፎች በኩል ከጥንት ጀምሮ ከውጭ ዓለም ጋር በቀጥታ የነበራቸውን የንግድና የባህል ግንኙነት በማዳከም በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለአክሱማውያኑ መንግሥትና ነገሥታት ከሰሜን ወደ መሀል፥ ደቡብ፥ ምዕራብና ምስራቅ አቅጣጫዎች በተለይም በአገው፥ በሰሜን/ፈላሻና በወልቃይት የቅርብ አካባቢዎችና አገሮች ላይ ለመስፋፋት አስገዳጅ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታዎችንና ግፊቶችን ፈጠረ።

## አሪታዊ የሰሜን/ፈላሻና የክርስቲያን ነገሥታት የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት

### *የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀትና የመንግሥቱ የመስፋፋት ታሪክ*

በቲዮሪም በተግባርም መንግሥትና ሥልጣኔ ሁለት በቅርብ የተያያዙ ነገሮች ናቸው። መንግሥት በሰፊ ትርጉሙ በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የአንድ የተወሰነ መሬት፥ ሕዝብና የፖለቲካ ሥርዓት የድርጅታዊና ሕጋዊ ትስስር ነው። ከሦስቱ መሠረታዊና አስፈላጊ አካላት አንዱ እንኳን ባይኖር በቲዮሪም በተግባርም መንግሥት የሚባል የፖለቲካ አሳብና ድርጅት አይኖርም። በሌላ በኩል ደግሞ በመሬት፥ በሕዝብና በፖለቲካ ሥልጣን ቅንጅት የሚፈጠረው የመንግሥት ድርጅት የሰለጠነም ያልሰለጠነም ሊሆን ይችላል። ከትርጉምና ከግንዛቤ አኳያ የመንግሥት መሠረታዊ መግለጫ የፖለቲካ ሥልጣን ሲሆን የሥልጣኔ መግለጫ ደግሞ የባህል ዕድገት ደረጃ ሚዛን ነው።

በተግባራዊ ትርጉሙ ሥልጣኔ የከተማና የገጠር ተግባራት ዕድገትና ክፍፍል፥ የእርሻና የንግድ ተግባራት፥ የግል መሬት ይዞታ፥

[67] S. Hablessllassie, History, p. 155.

[68] J. Cuoq, L'Islam en Ethiopie des Origines Au XVI Siecle, (1981), pp. 35-36.

የጽሕፈትና የገንዘብ አገልግሎት ያሉት አንድ ባህላዊ የህብረተሰብ ሥርዓት ወይም የዕድገት ደረጃ ነው። ከዚህ አጭር ትርጉም እንደ ምንረዳው መንግሥት የሥልጣኔ መሠረትና ቅድመ ሁኔታ ነው። ሥልጣኔ ግን የመንግሥት ገላጭ ባህርይ አይደለም። መንግሥት የአንድ በሥፍራና በጊዜ የተሰወነ መሬት፣ ሕዝብና የፖለቲካ ሥርዓት ቅንጅት ሲሆን፣ ሥልጣኔ ግን የአንድ የባህላዊና የማህበራዊ ድርጅት የዕድገት አንፃራዊ ደረጃ ነው። የመንግሥት መግለጫና የመለያ ሚዛን የፖለቲካ ኃይል ነው።

በመሆኑም፣ የተጠቀሱ ባህላዊ የሥልጣኔ ገጽታዎች ቢኖሩም ባይኖሩም በአንድ በተወሰነ መሬት ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ቅንጅት የሚፈጠር የመንግሥት ድርጅትና ሥርዓት በእርግጥ ሊኖርና ሊሠራ ይችላል። ስለዚህ የሥልጣኔ አለመኖር ወይም ለውጥ የመንግሥት አለመኖር እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱማውያን ሥልጣኔ ሲወድቅ፣ መንግሥቱ ግን በሌላ አቅጣጫ ከሰሜን ወደ ደቡብ በአጎራባች የአገው፣ የሰሜን/ፈላሻና የወልቃይት ምድር ከዚያም ባሻገር በሥፍራና በጊዜ እያደገና እየተስፋፋ መሄዱ አንድ ትምህርታዊ የታሪክ ሂደት ግንዛቤ ነው ለማለት ይቻላል።

ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱማውያን ኅብረተሰብ በአንድ በተወሰነ ሥፍራና ታሪካዊ ወቅት የአንድ የተወሰነ መሬት፣ ሕዝብና የፖለቲካ ሥልጣን ድርጅትና መግለጫ በመሆኑ አንድ ሉአላዊ መንግሥት፣ እንዲሁም ባህላዊ የእርሻ፣ የከተማ፣ የጽሕፈት እና የገንዘብ ገፅታዎችና አገልግሎቶች ያሉት የሰለጠነ ማህበረሰብ ድርጅት በመሆኑ ደግሞ አንድ ሥልጣኔ ነው ለማለት ይቻላል። ስለዚህ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ የሚለው አባባል ትክክለኛ ሀሳብና አባባል ነው።

ነገር ግን በመጨረሻ ከ7ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ በአንድ በኩል በብዙ ተፃራሪ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች፣ ሂደቶችና ኃይሎች ክስተትና ግፊት የሥልጣኔ ባህላዊ መሠረቶች፣ መኅሻዎችና መግለጫዎች ናቸው የተባሉ የአክሱማውያኑ የከተማ፣ የንግድ፣ የትምህርት፣ የዕደጥበብ፣ የኪነ ጥበብ፣ የሥነጥበብ፣ የገንዘብ መሠረቶች፣ መሣሪዎች፣ ገፅታዎች፣ ምልክቶችና ሥራዎች በከፊል ወይም በሙሉ እየፈረሱ ሄዱ።

በሌላ በኩል ግን በአንድ በሥፍራና በጊዜ ቀመር ውስጥ በተወሰነ የመሬት፣ የሕዝብና የፖለቲካ ሥልጣን ግንኙነትና ቅንጅት ለረጅም ዘመን የተመሠረተው የአክሱማውያኑ የመንግሥት ሥርዓት በራሱ ውስጣዊና ጥንታዊ የዘውድ፣ የክርስትና ሃይማኖትና የገባር





ኢኮኖሚ ድርጅቶችና ሥርዓቶች በልዩ መንገድና የዕድገት ደረጃ ተጠናክሮ በአዲስ የአገው፣ የሰሜን/ፈላሻ፣ የወልቃይትና የአማራ አጎራባች ሕዝቦችና አገሮች ላይ እያደገና እየተስፋፋ ሄዶ በመጨረሻም ለኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች ኅብረተሰብና መንግሥት ምሥረታና ዕድገት አንድ ታሪካዊ መሠረትና መሣሪያ ይሆናል።

### *የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ትምህርት መኅሻና ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ*

ከጊዜ፣ ከተግባርና ከታሪክ መረጃ አኳያ በእስትራቴጂያዊው የተከዜ-ዓባይ ወንዞች የመኅሻ ክልል በመሬትና በሥልጣን ጥያቄዎች በነባሩ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና በክርስቲያን የአክሱም፣ የአገውና የአማራ ተከታታይ መንግሥታት መካከል ረጅምና ተከታታይ ጦርነቶች የተካሄዱበት ጊዜ በአመዛኙ የታሪክ መረጃ ያልተገኘበት የ550-1300 'ጨለማ' ክፍለ ዘመን ነው። በመሆኑም አሁን የአካባቢውን ጥንታዊ ታሪክ በሥፍራና በጊዜ መስፈርት አገናዝቦ በትክክል ለማወቅና ለማስተማር ቀላል ጥረትና ተግባር እንደማይጠይቅ ግልፅ ነው።

በመሰረቱ ባለፈው ሚሊኒየም ማለትም በአንድ ሺህ ዓመታት ዘመን ውስጥ የሰሜን/ፈላሻ አካባቢ ታሪክን በተለይ የኢትዮጵያ ታሪክን በአጠቃላይ በእጅጉ ውስብስብና አስቸጋሪ ያደረጉ ነገሮች በሚሊኒየሙ መጀመሪያ ላይ የሁለቱን የአገውና የአማራ መንግሥታት ታሪካዊ መኅሻና ሕጋዊነት በሚመለከት ከግብጹ ቤተ ክርስቲያን በአረብኛ ቋንቋ ተዘጋጅተው ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የገቡ ክብረ ነገሥትና ፍትሐ ነገሥት የተሰኙ የፖለቲካ ባሕረ መዛግብት ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ በ12ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ በግብፁ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ በዳግማዊ ገብርኤል ዘመን (1131-1145) የኢትዮጵያ የአገው አመጻኛ ንጉሥ ሀርቤ[69] የአገሪቱን ቤተ ክርስቲያን ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ሞግዚትነት ነፃ ለማውጣት የወሰደውን የፖሊሲ እርምጃ ለማጥፋት የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና ምሁራን ሁለቱንም የክብረ ነገሥትና[70] የፍትሐ ነገሥት[71] መዛግብት አዘጋጅተው ወደ ኢትዮጵያ እንዳስገቡ አሁን በታሪክ መረጃና ጥናት በትክክል ተረጋግጧል።

ከሁለቱ ባሕረ መዛግብት የክብረ ነገሥት ረቂቅ መጀመሪያ በእስክንድርያ ግብፅ በኮፕቲክ ቋንቋ ከተዘጋጀ በኋላ በ1225 የረቂቁ

[69] S. Hablesellassie, History, pp. 251-254.

[70] Budge, The Queen of Sheba, p. 228.

[71] Paulos Tzadau, tr. The Fetha Nagast: The Law of The Kings (1968), pp. XV, 1-4, 18.

የአረብኛ ቋንቋ ትርጉም በጥብቅ ምሥጢር ወደ ኢትዮጵያ እንደገባና በመጨረሻ በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአጼ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት (1314-44) በ1320 ገደማ ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተር ጉሞ የኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥትና ሃይማኖት ባሕረ ሕግ ሆነ።

በዚህ ጥናት ከላይ እንደተባለው የክብረ ነገሥት ባሕረ ሕግ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ የጥንቱ የአክሱም መንግሥት ከኦሪት ሃይማኖት ጋር በ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ የተመሠረተው በኢየሩ ሳሌም ከሰለሞን ቤተ መቅደስ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ሕገ-ኦሪትን ሰርቀው ባመጡ የይሁዳውያኑ የመሳፍንትና የካህናት ልጆች ነው ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ የአገው ነገሥታትኝ በዘር ይሁዳውያን አይደሉም ይላል። በመሆኑም የአገው ነገሥታት በአገሪቱ ውስጥ በሰለሞናዊ ዙፋን ላይ መቀመጥ የማይገባቸው ስርጎ ገብ ወንበዴዎች ናቸው ብሎ ይከሳል።

ፍትሐ ነገሥት ደግሞ የአገው ነገሥታት የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለማስወገድ የፖሊሲ እርምጃ በወሰዱበትና ሳልሳዊ ቀርሌዎስ (1235-1243) የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ በነበረበት ዘመን በግብፅ ኮፕቲክ ጸሐፊ አሳል ከልዩ ልዩ የብሉይ ኪዳን፥ የአዲስ ኪዳን፥ የቤተ ክርስቲያን፥ የግሪክ፥ የሮማውያን፥ የቁራንና የአረብ ምንጮች የተሰበሰቡ የመን ግሥትና የሃይማኖት ሕግጋት ጥምር ባሕረ መዝገብ ነው።

በመጨረሻም በ15ኛው ምዕተ ዓመት በአጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1434-68)፥ ፍትሐ ነገሥት በግዕዝ ቋንቋ ትርጉም ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ከክብረ ነገሥት ጋር በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ እስከ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የ1931 ሕገ መንግሥት ድረስ ቢያንስ ለ400 ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ መሠረታዊ የመንግሥትና የሃይማኖት ጥምር ሕግ ሆኖ ኖረ።

ከጊዜና ከታሪክ አኳያ፥ ከአንድ ሚሊኒየም በኋላ በ1230ዎቹ በግብፁ ጸሐፊ አሳል በፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግ እንደተባለው፥ አርዮስ ግብፃዊው የሃይማኖት ምሁር የክርስቶስን መለኮታዊና ሰብአዊ ጥምርና ረቂቅ ባሕርያት በሚመለከት የምሥጢረ ሥላሴ ጥያቄ ላይ ባስነሳው ታላቅ ክርክር ምክንያት፥ ገና የክርስትና ሃይማኖት በ330 ዓመተ ምህረት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ አምስት ዓመታት አስቀድሞ፥ በ325 በታላቁ የኒቅያ ጉባኤ ከሮማውያኑ አጼ ቆስጠንጢኖስ (306-337) ጋር ለውሳኔ በተቀመጡ 318 የዓለም አህጉራዊ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን ከግብፃዊው አቡን በስተቀር ማንም የኢትዮጵያ ተወላጅ





በምንም ጊዜና መንገድ የአገሩ ቤተ ክርስቲያን የበላይ መሪና አስተማሪ ለመሆን አይችልም ተብሎ ተወስኗል ይላል።[72]

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ከ330 እስከ 1950 ድረስ ማለትም ለ1620 ዓመታት፥ ከመነሻው ጀምሮ ለሮማውያን፥ ለአረብና ለቱርክ ጌቶቿ በባርነት ስትገዛና ስትገብር የኖረችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ራሷ ከጥገኝነት ሳትላቀቅ የአገሪቱን ቋንቋና ባህል በማያውቁ በ110 ወኪል አቡኖቿ አማካይነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በተንኮል ስትገዛና ስትዘርፍ እንደኖረች አይረሳም።[73]

ባጭርና በጥቅል አነጋገር ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በኢትዮጵያ የመንግሥትና የሃይማኖት መሪ ሕጎች ተደርገው የኖሩ ሁለቱ የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግ ጋት የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና ሊቃውንት የሞግዚትነት ሥልጣናቸውንና ጥቅማቸውን በኢትዮጵያ ጥገኛ ቤተ ክርስቲያን ላይ የበለጠ አጠናክ ረው ለማቆየት የፈጠሩአቸው የሕግ፥ የፖለቲካ፥ የሃይማኖትና የታሪክ ቅይጥ ሥራዎች እንደሆኑ ከላይ ከቀረቡ የታሪክ መረጃዎች ለማንም አስተዋይ ግለሰብ በጣም ግልፅ ነገር ነው።

ከዚህ ከ13ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ከላይ በቀረቡ የፖለቲካ ምክንያቶችና መንገዶች ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት በገባው የክብረ ነገሥት ባሕረ ሕግና ትምህርት መሠረት፥ ባለፉት ሰባት ምዕተ ዓመታት የኢትዮጵያ የዘመኑ ነገሥታትና የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊዎች የአገሪቱን ጥንታዊ፥ ሉአላዊና በህውርታዊ ታሪክ ወስደው በመካከለኛው ምስራቅ የጥንቱ ይሁዳውያን የሃይማኖት ታሪክ አካል አድርገው አቅርበውታል። በመሆኑም በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ኅብረ ተሰብ መንግሥትና ታሪክ ላይ ታላቅ ግድፈት ፈጥረዋል።

*በአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት የሰሜን/ፈላሻ ሚና ጥያቄ*

በዚህ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ታሪክ ጥናት፥ በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ በዘመነ ክርስትና (1)፥ በ4-5ኛ ምዕተ ዓመታት ውስጥ የክርስትና ሃይምኖት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ወደ አገሪቱ ከመግባቱ በፊት የይሁዳውያኑ የኦሪት ሃይማኖትና ሕግ በኢትዮጵያ አለመገኘቱንI (2)፥ በ13-15ኛ ምዕተ ዓመታት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱ የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግጋት ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ከመግባታቸው በፊት ሰለሞናዊ የተሰኘው

[72] Ibid.,, p. 18.

[73] ማህተመ ሥላሴ ወ/መ፥ ዝክረ ነገር፥ (1962) ገጽ 891-894።

የፖለቲካ ተረት ሆነ የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ሃይማኖት እንዳልነበረና (3)፣ በ5ኛው ምዕተ ዓመት ዘጠኙ ግሪክ-ሮማዊ ጻድቃን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ የተረጎሙት መጽሐፍ ቅዱስ በአክሱምና በአካባቢው አጠናክረው ከመሠረቱት የገዳም ሥርዓትና ከግዕዝ ቋንቋ ጋር በኋላ በሁለተኛው ሚሊኒየም መጀመሪያ ምዕተ ዓመታት በሰሜኑ ደጋማ ኢትዮጵያ በአራቱ የትግሬ፣ የሰሜን/ፈላሻ፣ የአገውና የአማራ አገሮች ለሁለቱም ተዛማጅ የክርስትናና የኦሪት ሃይማኖቶች ዕድገትና መስፋፋት የጋራ መነሻና መሣሪያ እንደሆነ[74] የሚያስገነዝቡ አዳዲስ የውይይት ሀሳቦችና አስተያየቶች ወይም ቲሲሶች ቀርበዋል።

በሌላ በኩል፣ በ550-1300 የሰነድ መረጃ ባልተገኘበት 'የጨለማ' ዘመን ውስጥ በአካባቢው በተጠቀሱ አራት የፖለቲካና የሃይማኖት ማኅበረሰቦች መካከል፣ ለምሳሌ የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት፣ የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ሃይማኖት ክስተት፣ የጉዲትን ፖለቲካ ተረት ጨምሮ፣ በልዩ ልዩ ሥፍራዎች፣ ጊዜያት፣ መስኮችና መንገዶች የተካሄዱ ብዙ የግንኙነት ሁኔታዎችን፣ ሂደቶችንና ተዋንያንን በሥፍራ፣ በጊዜ፣ በቁጥርና በተግባር መስፈርት ተንትኖ ለማወቅ የታሪክ መረጃ ስላልተገኘ ሁሉም የተረት ቅኝቶች ሆነው ቀርበዋል ወይም ቀርተዋል ለማለት ይቻላል።

ይህም ብቻ አይደለም። በታሪክ፣ በፖለቲካ፣ በሃይማኖትና በመንግሥት ሥልጣን ስም በተዛማጅ የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ባሕረ መዛግብት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች፣ መምህራንና ጸሐፊዎች በኢትዮጵያ ለረጅም የጠርነትና የጥፋት መቅሰፍት፣ መነሻና መሣሪያ የሚሆን ዘረኛ ትምህርት አስተምረዋል። በተጠቀሰው የተንኮል ሥራና ሥርዓት የኢትዮጵያ የሰሜን/ፈላሻና የአገው ነባር ሕዝቦች የዚህ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ዘረኛ ትምህርት የመጀመሪያ ሰለባዎች ሆነዋል።

ከዚህ አኳያ ነባሩ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ የአክሱሙን ሥልጣኔ በወረራ ያጠፋው ባዕድ ጠላት ነው ተብሎ ይወነጀላል። በመሆኑም ውሎ ሳያድር ከቤቱ፣ ከንብረቱ፣ ከመሬቱና ከአገሩ ይፈናቀላል። በገዛ አገሩ መጤ (ፈላሻ) ተብሎ ይፈረጃል። የዜግነት መብትና ክብር እንዲያጣ ይደረጋል። እንዲሁም የአገው ሕዝብና መንግሥት በአገሩ መንበረ ሥልጣን ላይ መቀመጥ የማይገባው ባዕድ ሕዝብና መንግሥት ነው ተብሎ ይኮነናል። በመሆኑም ከሥልጣኑ እንዲወርድ ከአገሩም እንዲሰደድ ይደረጋል። ታሪኩም ይፋቃል።

---

74 Leslau, <u>The Black Jews of Ethiopia</u>, p. XIII; Taddasse Tamrat, <u>Church and State</u>. Chaps. 5-6.





*የጉዲት ተረትና የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ቅጣት*

የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብን የጥፋትና የቅጣት ታሪክ በሚመለከት አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ አክሱም-ዛጉዌ በተሰኘ መጽሐፋቸው «የፈላሻና የነገደ አገው ወገኖች ተቀስቅሰው የአክሱሙን መንግሥት ጥለው ለየራሳቸው መንግሥት ለማቆምና ባላባቶቻቸውን ለማንገሥ»[75] በአመፅ ተነሱ የሚል አስተያየታቸውን ይደግፉሉ ብለው የሚገምቱአቸውን «የውጭዎቹም ያገራችንም ደራሲዎች እነ ብሩቴን ጌታ ኅሩይ፣ እነ አለቃ ታዬ» የጻፉአቸውን ተመሳሳይ ሀሳቦችና አስተያየቶች አሰባስበውና አገናዝበው እንደ ሚከተለው አቅርበዋል። በአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ቃል፣

> *በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ብዙ የእሥራኤል ወገኖች ካህናቶችም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሕዝቡን ሕገ ኦሪት እያስተማሩ በእውነተኛ በእግዚአብሔር እንዲያምን አደረጉት። ከእነርሱም ውስጥ ብዙዎቹ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እየተጋቡ እየተዋለዱ ብዙ ዘመን ኖሩ። በአብርሃና በአጽብሐ ጊዜ አባ ሰላማ (ፍሬሚናጦስ) በአክሱም መንግሥት ክርስትናን ከአመጣ በኋላ የአክሱም ሕዝብ ክርስትናን ተቀብሎ ሲኖር የእሥራኤል ወገን የሆኑት አዲሱን ሃይማኖት ክርስትናን አንቀበልም ብለው በዚያው በቀድሞው ሃይማኖትና በኦሪት ሕግ ጸንተው ተቀመጡ። በዚህም የተነሳ ክርስቲያኖቹ ቢጨቁኗቸው ከአክሱምና ከዙሪያው እየተሰደዱ በሰሜንና በወገራ በወልቃይት በላስታም ተቀመጡ። እነዚህም ፈላሾች የሚባሉ ናቸው። ፈላሲ አገሩን ትቶ ሒያጅ ማለት ስለሆነ እነዚህም ጥንት ከኢየሩሳሌም ወደ አክሱም፣ አሁን ደግሞ ከአክሱም ወደ ሰሜንና ወደ ወገራ ስለ ተሰደዱ ፈላሲያን (ፈላሾች) ተባሉ ይባላል። ይህ በመጨረሻ የተሰደዱበት የሰሜን አገር ተራራማ ስለሆነ በዚህ ሥፍራ ሆነው በፍጥረቱ ምሽግነት እየተጠቀሙ ሊወጓቸው የሚመጣውን ሁሉ እየተከላከሉ ይመልሱት ነበር። ቁጥራቸው እየበዛ ኃይላቸው እየበረታ ሲሔድ ከመካከላቸው ጌዴዎን የሚባለውን እንደንጉሥ ሾሙት።*
>
> *ለጌዴዎን በጣም የተዋበች ልጅ ነበረችው። እርሷም ዮዲት አንዳንድ ጊዜ አስቴር የምትባለው ነች። ዮዲትንም ዘርዓያዕቆብ የሚባል የቡግና (ላስታ) ገዥ ክርስቲያን ፈላሻነቷን ሳይመረምር የመልኳን ውበትና ቁንጅናዋን አይቶ አገባት። እርሷም በውበቷና በፍቅሯ በቀን ብዛት እየሳበች በርሷ ሃይማኖት (በይሁዲ) አገባችውና ስሙንም ሰለሞን አሰኘችው።*
>
> *በዚህ ዘመን በአክሱም ዙፋን የተቀመጠው የኢትዮጵያ ንጉሥ ድግናዣን ነበር። ነገር ግን እርሱ ሰለሞት አንበሳ ውድም የሚባለው ሕጻን ልጁ ነገሠ። የነገሠው ሕጻን ለማስተዳደር አለመቻሉን ዮዲት ባወቀች ጊዜ በሰሜንና በላስታ አውራጃ የሚኖሩትን ፈላሾች ወገኖቿን ይዛ ወደ አክሱም ገሠገሠች። የአክሱም መኳንንትም ሕጻኑን ንጉሣቸውን እንደያዙ እርሷን ፈርተው ከትግሬ ወደ*

---

75 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ፣ አክሱም ዛጉዌ</u>፣ ገጽ 328።

*ሸዋ ሸሹ። ከዚህ በኋላ (በ842 ዓም) ነገሡችና በአክሱምና በዙሪያው ያሉትን ሐውልቶች እያስፈረሰች አብያተ ክርስቲያናቱን ሁሉ አቃጠለች። እንደዘመኑ ልማድ የውስጥ ጦርነት እንዳ ይቀሰቅሱ ተብሎ በደብረዳሞ ተራራ ላይ በዘበኛ ይጠበቁ የነበሩትን ከነገሥታት የሚወለዱትን መሳፍንትንት ሁሉ አሳረደቻቸው። በዚህ ጭካኔዋ ዮዲት የተባለው ስሟ ተለውጦ ጉዲት፥ አስቴር የተባለውም ቀርቶ እሳቶ ተባለች ይባላል።*

*አንበሳ ውድም ወደ ሸዋ ሸሽቶ በመጣ ጊዜ የሸዋ ሕዝብ በደስታ ተቀበለው። ዮዲት ይኸን በሰማች ጊዜ በነገሡች በ23ኛው ዓመት ብዙ ሠራዊት ስብስባ ወደ ሸዋ ላከች። አንበሳ ውድምም የመንዝን ባላገር ይዞ የዮዲትን ጦር ተዋግቶ መለሰው። ከዚህ በኋላ ራሷ ዮዲት የቀረውን ጦሯን ሰብስባ ራሷ እየመራች ወደ ሸዋ መጣች። አንበሳ ውድምም መምጣቷን ሲሰማ ከመንዝ ወደ መራቤቴ ወረደ። እርስዋም እስከ መራቤቴ ለመከታተል ሞክራ ሳለ በመካከል የአህያ ፈጅና የደባ መንገድ ገደላ ገደል ስላስቸገራት በዚህም ላይ አንበሳ ውድምን የሚረዳው የሸዋ ሕዝብ በሚያውቀው አገር ላይ እያደፈጠም ፊት ለፊትም እየወጋ አደጋ እየጣለ ስለ አወካት ከሸዋ ወደ አክሱም ተመልሳ 17 ዓመት ያህል ኖራ በሙሉ 40 ዓመት ነግሣ ሞተች።*

*አንበሳ ውድም የዮዲትን ሞት በሰማ ጊዜ ከሸዋ በግሥጋሤ ወደ አክሱም ሔደ። የትግሬ ሕዝብም በደስታ ተቀበለውና ባባቶቹ አልጋ አስቀመጠው። ሀያ ዓመት ያህልም እንደገዛ ሞተና ልጁ ድል ነዓድ ነገሠ። ቢሆንም በዮዲት ጊዜ የተቀሰቀሰው የሰሜንና የላስታ ሕዝብ በዮጊዜው እየተነሳ አላስገዛ ብሎት ሲኖር በመጨረሻ መራ ተክለ ሃይማኖት የሚባል ትርዳእ ገዘዝ የምትባለዋን (ልጅ) ይዞ ከላስታ ተነሥቶ ድልነዓድን ይወጋው ጀመር። አሁንም ድልነዓድ አቅም ስላጣ እንዳባቱ እንደአንበሳ ውድም ከአክሱም ወደ ሸዋ ሸሸ። መራ ተክለሃይማኖት ድልነዓድን ከአባረረ በኋላ በኢትዮጵያ ነገሠና የዛጉዬ መንግሥት መሠረተ።*[76]

*የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦች የጋራ መነሻና ዕድገት*

በዚህ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ታሪክ ጥናት ተደጋግመው የሚነሱና ሰለሞን፥ ሳባ፥ ምኒልክ፥ አይሁድ፥ እሥራኤል፥ ቤተ እሥራኤል፥ ፈላሻ፥ ጌዴኦን፥ ጉዲት፥ ዘርዓያዕቆብ፥ ድግናዣን፥ አንበሳ ውድም፥ ድልነዓድ፥ ትርዳእ ገበዝና መራ ተክለ ሃይማኖት ተብለው ከላይ በምንባብ የቀረቡ ገፀባሕርያት በሰሜን ኢትዮጵያ በድህረ አክሱም ሥልጣኔ ከአራቱ ነባርና ተዛማጅ የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦች ታሪካዊ ክስተትና ዕድገት ጋር በቅርብና በጥብቅ በተያያዘ ሁኔታ ከ550-1300 የጨለማ ዘመን ወዲህ በግብፅ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊዎች የተፈጠሩ የፖለቲካ ገፀ ባሕርያት ናቸው።

[76] Ibid., pp. 329-331.





ከሁለቱም ከይዘትና ከቅርፅ አኳያ የገፀ ባሕርያቱ ድርሰት በተጠቀሱ ተዛማጅ የአካባቢ ሕዝቦች መካከል ኢ-ታሪካዊ የሆነ ቅራኔ፥ ልዩነትና ጠላትነት ይፈጥራል። የተረቱ ድርሰትና ትምህርት በተጨማሪ በኅብረተሰቡ ዘንድ «ምርጥ» በተባለው መጤ ሰለሞናዊ የገዥ መደብና በነባሩ አምራች ሕዝብ መካከል በዘርና በሃይማኖት ምርጫና ልዩነት ያደርጋል። ኢትዮጵያውያንን «ሕዝብ» እና «አሕዛብ» ማለትም «ወገን» እና «ጠላት» በማለት በሁለት ተፃራሪ ሠፈሮችና ግምባሮች ይመድባል።

«ሕዝብ» ተብሎ የተፈረጀውን «ምርጥ» የሕዝብ ወገን በአዲሱ የኩብረ ነገሥት ፖለቲካ ትምህርት መሠረት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ሴማዊ ዘር ነው ከተሰኘው የይሁዲ። እሥራኤል ሕዝብ የሃይማኖት ታሪክ ጋር በቅርብ ያዛምዳል። «አሕዛብ» የተባለውን ወገን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ «የምርጡ» የይሁዲ። እሥራኤል ሕዝብ የሃይማኖት ጠላቶች ናቸው ከተባሉ አዋማዊ የከነዓን፥ የግብፅ፥ የአሶሪያ፥ የባቢሎን፥ የአረብ ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ጋር እያዛመደ በጥቁር ቀለም ያሳያል። ጥላሸት ይቀባል።

ከሁሉም በላይ በ550-1300 የሰነድ መረጃ አልባ ዘመን በሰሜኑ ደጋማ ኢትዮጵያ ከተነሱ አራቱ የአካባቢ የፖለቲካ ማኅበረሰቦች ሁለቱን የሰሜን/ፈላሻና የአገው ሕዝቦችን ለይተው የተረቱ ፈጣሪዎች «የአክሱሙን መንግሥት» ያጠፉ ጠላቶች ናቸው በማለት ይወነጅሉዋቸዋል። በመሆኑም በአጋጣሚ በአካባቢው ታላቅ የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት የሆኑ የሰሜን/ፈላሻና የአገው ሕዝቦችን ለቅጣት፥ ለጦርነትና ለዘረፋ የተፈጠሩ ጠላቶች አድርገው ያቀርቡአቸዋል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በሌላ በኩል፥ በድህረ አክሱም ሥልጣኔ በሰሜኑ ደጋማ ኢትዮጵያ የአራቱን የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦችን ታሪካዊ ክስተትና ዕድገት በተለይ፥ በታላቁ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የኢትዮጵያን ሁለአቀፍ በሠውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ኅብረተ ሰብ ክስተትና ዕድገት በአጠቃላይ አለቅራኔ የሚገለፁ ሁለቱ ታሪካዊ ኃይሎች በእርግጥ የኢትዮጵያ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ ተቋማት ናቸው። ባጭሩ የኢትዮጵያን የታሪክ ይዘት፥ ዕድገትና ሂደት በተጨባጭ መንገድና ሚዛን የሚገልፁ የእነዚህ ሁለት ኃይሎች የኢኮኖሚ ታሕታይና የፖለቲካ ላዕላይ ድርጅቶችና መዋቅሮች ናቸው።

ከዚህ አኳያ፥ በዓለም ታሪክ የክርስትና ሃይማኖትን የኅብረተሰብ ግምባታ ተግባርና ሚና በሚመለከት ዕውቁ የብሪቲሽ ምሁር

ኤድዋርድ ጊቦን (1737-1794) *The Decline and Fall of the Roman Empire (1788)* *ዘዲክላይን ኤንድ ፎል ኦፍ ዘ ሮማን ኢምፓየር* በተሰኘው መጽሐፉ፥ ክርስትና ማኅበራዊና ሥርዓታዊ ግጭት በመፍጠር ለታላቁ የሮማውያን ኢምፓየር ድክመትና ውድቀት ዓይነተኛ መነሻና ምክንያት ሆነ የሚል ቲሲስ አቅርቧል። በሮማውያን ኢምፓየር ክርስትናን መጀመሪያ የተቀበሉ የገባርና የባርያ ወገኖች ነበሩ። ይህም በኅብረተሰቡ ዘንድ የሥርዓት ግጭቶች እንዳስከተለ አይረሳም።

የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ በተቃራኒው በአገሩ ነባር መንግሥት አመራር ራሱን ከአክሱም አዋማዊ የፖለቲካና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ጋር በማዋሃድ ለነባሩ ዘውዳዊ መንግሥት ቀጣይ ዕድገትና መስፋፋት አዲስ መንገድና መሣሪያ ሆነ። ማለትም በአካባቢው በቅይጥ የአዋማዊዝም፥ የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች መሠረት በተለይ ለትግሬ፥ ለሰሜን/ፈላሻ፥ ለአገውና ለአማራ ሕዝቦች በህውርታዊ ኅብረ ተሰብና መንግሥት ዕድገት የድርጅት ላዕላይ መዋቅር ሆነ። በመሆኑም ሃይማኖቱ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሥርዓት ቀውስ አላስከተለም።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ከሁሉ በፊት በ330 የክርስትና ሃይማ ኖትና ትምህርት በሰላማዊ መንገድ ወደ አዋማዊ የአክሱም ምድርና ቤተ መንግሥት የገባው በአገሩ መንግሥትና ሕዝብ ነፃ ፍላጎትና ምርጫ ነው። በመሆኑም፥ በአክሱሙ ኅብረተሰብ ዘንድ በአዲሱ ሃይ ማኖትና ትምህርት ምክንያት በሮማውያኑ ኅብረተሰብና መንግሥት ላይ የደረሰው ማኅበራዊና ሥርዓታዊ ግጭትና ውድቀት አላደረሰም። በኅብረተሰቡና በዘመኑ የኢኮኖሚ ታህታይ መዋቅር ላይም ሆነ የፖለ ቲካ ላዕላይ መዋቅር ላይ ፈጣንና መሠረታዊ ለውጥ አልተካሄደም።

በተጨማሪም በኋላ በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በ6ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ (470-550) ላይ በአክሱም ከተማ መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በመተርጎም፥ በአዋማዊው አገር የገዳም ሥርዓትና ተቋም በማቋቋም፥ እንዲሁም የግዕዝ ቋንቋን የትምህርት፥ የሥነ ጽሑፍና የቅዳሴ መሣሪያና መገለጫ በማድረግ፥ የአክሱም ቤተ ክርስቲያንን በጠንካራ ባህላዊና ድርጅታዊ መሠረት ላይ የገነቡ ዘጠኙ ግሪክ-ሮማዊ ጻድቃን፥ በዘመኑ የቤተ ክርስቲያኑን የመዝሙርና የቅዳሴ ሥርዓቶችን ከፈጠረው ምሁር ያሬድ ጋር፥ የአክሱም ነገሥታት አልአሜዳ፥ ታዜና፥ ካሌብና ገብረመስቀል አስተማ ሪዎችና አማካሪዎች በመሆን፥ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል በፍሬምናጦስ የተጀመረውን ሰላማዊና ተግባራዊ አንድነት የበለጠ እንዳጠናከሩ ከቤተ ክርስቲያኑ ታሪክና ትውፊት በትክክል ይታወቃል።





በ330-550 የክርስትና መነሻ ዘመን ፍሬምናጦ ስና ዘጠኙ ጻድቃን በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል የፈጠሩት ሰላማዊ ግንኙነት በ550-1300 የጨለማ ዘመንም ቢሆን የበለጠ እያደገና እየጠነከረ እንደሄደ የሚያመለክቱ አንዳንድ የታሪክ መረጃ ፍንጮችና ምንጮች አሉ። ለምሳሌ አንደኛ፥ በተጠቀሰው ዘመን መጀመሪያ በ610ዎቹ ከአረቢያ እስላማዊ ስደተኞች ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት በመጡ ጊዜ በአገሩ በክርስቲያን መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን መካከል ሰላማዊ ሕይወትና ሥራ እንደነበረ የስደተኞቹ ታሪክ ያሳያል።

ሁለተኛ፥ በዘመኑ ሁሉም የአክሱምና የአገው ነገሥታት የመንግሥትም የቤተ ክርስቲያንም የበላይ መሪዎች እንደሆኑ በግብፁ አቡን ሹመት ጉዳይ ላይ በኢትዮጵያና በግብፅ ባለሥልጣኖች መካከል የተካሄዱ የሥራ ግንኙነቶች ታሪክ ይገልጻል።

ሦስተኛ፥ በአገው ነገሥታት ከላስታ ቋጥኝ ድንጋይ ተፈል ፍለው የተሰሩ አብያተ ክርስቲያናት በዘመኑ በኅብረተሰቡ ዘንድ የነበረው የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን አንድነት ታሪካዊ መግለ ጫዎች ናቸው።

## የሥርዓተ ኦሪት ታሪካዊ መነሻ በኢትዮጵያ

### *የኢትዮጵያ መምህራን ተግባር በሰሜን/ፈላሻ አገር*

በ550-1300 የጨለማ ዘመንም ሆነ ከዚያም በፊት በአካባቢው የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ሃይማኖት መከሰቱንና መኖሩን የሚጠቁም አንድም አሳማኝ የታሪክ መረጃ ፍንጭና ምንጭ ከአገር ውስጥ ሆነ ከአገር ውጭ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም።

በመሆኑም ከታሪክ አኳያ የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ሃይማኖት ክሱትትና እንቅስቃሴ የተጀመረው በ13ኛው ምዕተ ዓመት ከክብረ ነገሥት ትምህርት ና ከሰለሞናውያኑ አገር አቀፍና ሁለአቀፍ የወንጌል፥ የገዳም፥ የግዕዝ ብራና ሥነጽሑፍ፥ የፖለቲካ፥ የማትና የመስፋፋት ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች[77] ጋር በቅርብ በተያያዘ ሁኔታና መንገድ ነው ለማለት ይቻላል።

ከ550-1300 ክፍለ ዘመን በኋላ ከ13ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ጀምሮ በ15ኛው ምዕተ ዓመት እስከ አጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1434-68) ድረስ በጥንቱ ዘጠኝ ግሪክ-ሮማዊ ጻድቃን የክርስትና ትምህርትና በአዲሱ የክብረ ነገሥት የፖለቲካ ፍልስፍና ጥምር መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርቡ የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ መነኮሳትና

[77] Huntingford, Amda Seyon; Taddese Tamrat, Church and State.

መምህራን በቀይ ባሕርና በጎጃም-ሸዋ መካከል ክርስትናን ከአሪት ሃይማኖት ጋር አጣምረው እያስተማሩ ብዙ አዳዲስ የወንጌል፥ የቤተ ክርስቲያን፥ የገዳም፥ የግዕዝ ብራና ሥነጽሑፍ ሥራዎችን፥ ተቋማትንና እንቅስቃሴዎችን በማስፋፋት በአካባቢው ለሁለቱም የክርስቲያንና የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ማኅበረሰቦች የፖለቲካ ዕድገት፥ መስተጋብርና መወራረስ ሁኔታዎችን፥ መንገዶችን፥ መሣሪያዎችንና መዋቅሮችን ፈጠሩ። ባጭሩ የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ሃይማኖት ታሪካዊ ምንጩና መነሻው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነው።

በዘመኑና በአካባቢው ለተመለከተው የክርስትና እና የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ሃይማኖቶች ጥምር ዕድገት፥ መስተጋብርና መወራረስ የትምህርትና የድርጅት ሁኔታዎችን ከፈጠሩ ከፍተኛ የገዳም መነኮሳትና መምህራን፥[78]

1. በቤተ አማራ የደብረሐይቅ ገዳም መሥራች አቃቤ ሰዓት ኢየሱስሞዓ (1211-1292)፥
2. በሸዋ የደብረሊባኖስ ገዳም መሥራች አቡነ ተክለ ሃይማኖት (1215-1313)፥
3. በትግራይ የሥርዓተ ኦሪት እንቅስቃሴ መሥራች መነኩሴ እዎስጣጤዎስ (1273-1352)፥
4. በሰራየ የእዎስጣጤዎስ ደቀመዝሙርና የደብረማርያም ገዳም መሥራች አባ አብሳዲ፥
5. በእንፍራንዝ ደምቢያ የእዎስጣጤዎስ ደቀ መዝሙርና የደብረሰን ገዳም መሥራች አባ ገብረኢየሱስ፥
6. መነኩሴ ቆዝሞስ በደምቢያ ከደብረወይና ገዳም በአጼ ዳዊት ዘመን (1382-1412) ለሰሜን/ፈላሾች የሥርዓተ ኦሪት አስተማሪ፥
7. በሐማሴን የእዎስጣጤዎስ የሥርዓተ ኦሪት ትምህርትና እንቅስቃሴ መሪና የደብረቢዘን ገዳም መሥራች መነኩሴ ፊልጶስ (1323-1406)፥
8. በ15ኛው ምዕተ ዓመት የአጼ ዘርዓያዕቆብ (1434-68) ምሁርና አመጸኛው ልጅ ሰብራ፥
9. በ15ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአ ጋሜ የትንዳትንዲ ገዳም መሥራች መነኩሴ እስጢፋኖስ ከነተከታዮቻቸው በመጀመሪያ ደረጃ የሚታውሱ ታላላቅ አባቶች ናቸው።

ባጭሩ እነዚህ መምህራን በጥንቱ ዘጠኝ ጻድቃን የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥራ መሠረት ከአዲሱ ሰለሞናዊ ነገሥታት ጎን ተሰልፈው በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን ግምባታ ፖሊሲና ተግባር

[78] Ibid., Church and State, Chaps. 5, 6.





በድርጅትና በትምህርት መስኮች ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ የገዳም መምህራንና መነኩሳት ናቸው። የተጠቀሱ መምህራንና ገዳማት፥ በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና አመራር ጉዳዮች፥ ከ1337 እስከ 1450 ድረስ በአንድ ምዕተ ዓመት ዘመን ውስጥ በሁለት ተፃራሪ አንጃዎች ተከፍለው እንደነበር ታውቋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በ1270 የአማራ የጦር አበጋዝ ይኩኖ አምላክ የአገውን ክርስቲያን መንግሥት ደምስሶ አዲስ ሰለሞናዊ መንግሥት በመሠረተ ጊዜ ሁለቱ ታዋቂ የገዳም መምህራን ማለትም የደብረሐይቁ ገዳም አቃቤ ሰዓት ኢየሱስሞዓና የደብረሊባኖሱ ገዳም አቡነ ተክለሃይማኖት ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ጋር የይኩኖአምላክ (1270-1285) መንግሥት ደጋፊዎች እንደነበሩ ተረጋግጧል። ለዚሁ ወሮታ ከሰለሞናዊያኑ መንግሥት መሪዎች፥

አንደኛ፥ ለደብረሐይቁ ገዳም መሪ ኢየሱስ ሞዓና ለተከታዮቹ በአዲሱ ቤተ መንግሥት ከንጉሡ ዙፋን ቀጥሎ ከፍተኛው የሆነ የአቃቤ ሰዓት ሥልጣንና ሹመት በውርስ መብት ተሰጠ።[79] በዚሁ ውሳኔ መሠረት ለምሳሌ ከ1270 እስከ 1535 ድረስ በ265 ዓመታት ውስጥ የመንግሥታቱ ከሃያ በላይ የሚቆጥሩ የአቃቤ ሰዓት ባለሥልጣኖች[80] በሙሉ የደብረሐይቅ ገዳም መሪዎችና መምህራን ነበሩ።

ሁለተኛ፥ ለደብረሊባኖስ ገዳም መሪ ለአቡነ ተክለሃይማኖትና ለተከታዮቹ በቤተ ክርስቲያን ስም ከመንግሥቱ መሬት ሲሶው ተሰጠ።[81]

ሦስተኛ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእምነ ትና የትምህርት አመራር ቀደም ብሎ በ1238 በግብፅ አገርና ደራሲ በተጻፈው የፍትሐ ነገሥት ሕግ መሠረት ለዘለዓለም በግብፁ ሞግዚት ቤተ ክርስቲያን እንደራሴ አቡን እጅ በውርስ መብት እንዲሆን ሰለሞናዊ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተስማሙ።[82]

*የእዎስጣጤዎሳውያኑ የ1337-1450 የኦሪት አመፅና ድል*

በ1337-1450 በቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ትምህርትና ሥራ ጉዳዮች ላይ ከላይ በተጠቀሱ ታላላቅ መነኩሳትና ገዳማት መካከል የተፈጠሩ ሁለት ተፃራሪ ኃይሎችና ቡድኖች አንዱ በሰሜን ኢትዮጵያ የእዎስጣጤዎስን የኦሪት እምነት፥ ትምህርትና ሥርዓት ከክርስትና

[79] Ibid., "The Abbots of Debra Hayq 1248-1535", p.90.
[80] Ibid., pp. 88-117.
[81] ገድለ ተክለ ሃይማኖት ገጽ 74-80
[82] J. Bruce, Travels To Discover the Source of the Nile, 5 Vols., (1790), I, pp. 533-34.

ሃይማኖት ጋር አጣምሮና አዛምዶ የሚከተል በአመዛኙ በሰሜን የትግሬ[83] መነኮሳትና ገዳማት አንጃ ነበር።

ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ማለትም በሸዋና በቤተ አማራ ከላይ ከቀረበው ከአገው-አማራ የመንግሥት ለውጥ ፖለቲካ አኳያ ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮችና ከሰለሞናዊ ነገሥታት ጋር የቀረበና የጠበቀ አንድነት የነበራቸው የደብረ ሐይቅና የደብረ ሊባኖስ[84] ገዳማትና መነኮሳት አንጃ ነበር።

የዚህ የትግሬ-አማራ መነኮሳትና ገዳማት አንጃዊ ትምህርትና ፖለቲካ መነሻው በሥርዓተ ኦሪት ጉዳይ ላይ የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣ ኖች የወሰዱት አዲስ የእምነት አቋም ነው። ከዚህ አኳያ፥ በ1230ዎቹ የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ኮፕቲክ ጳሐፊ አሳል በ325 ዓም በኒቅያ ጉባኤ የተቀመጡ 318 የዓለም አህዳዊው ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን ከግብፁ ወኪል አቡን በስተቀር ኢትዮጵያዊ ተወላጅ በአገሩ ቤተ ክርስቲያን በእምነትና በሃይማኖት ጉዳይ ላይ የበላይ መሪና አስተማሪ ለመሆን አይችልም ብለው ደንግገዋል የሚለ ውን ፍትሐ ነገሥት ካዘጋጀ ወዲህ የኦሪትን የሥርዓተ ሰንበት አምልኮ በሚመለከት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ማዕቀብ እንዳ ደረጉበት ታውቋል፣[85]

የግብፁ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና አቡን ወኪሎቻቸው ይህንኑ የኦሪት ሃይማኖት ማዕቀብ በኢትዮጵያ ጥገኛ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለመጫን ብዙ ጊዜ ያልተሳካ ሙከራ እንዳደረጉ ተረጋግጧል። በዚህ ሁኔታና ሂደት በ1337 መነኩሴው እዎስጣጤዎስ በኢትዮጵያ ለሁለቱም የክርስትናና የኦሪት ሃይማኖቶች ጥምር ነፃነት፥ እኩልነትና ዕድገት መጀመሪያ በኢትዮጵያ ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ወኪል ከአቡነ ያዕቆብ ጋር በይፋ ተከራከረ። ቀጥሎም በዚያው ዓመት በግብፅ ከሞግዚት ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ቤንጃሚን (1327-39) ጋር በይፋ ተከራክሮ በእያሌ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ለ15 ዓመታት በስደት ኖሮ፥ በመጨረሻ በ1352 በአርመን አገር ሞተ።[86]

ይሁን እንጂ ከ1352 እስከ 1450 ድረስ ከላይ የተጠቀሱ የእዎስጣጤዎስ ተከታይ መነኮሳትና መምህራን አብሳዲ፥ ገብረኢየሱስ፥ ቆዝሞስና ፊልጶስ በብዙ ሺህ ከሚቆጠሩ ሌላ የገዳምና የቤተ ክርስቲያን መምህራን ጋር የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን ግዛት፥ የመንግሥትን ቅጣትና

[83] Taddasse Tamrat, Church and State, pp. 206-212.

[84] Ibid., pp. 213-219.

[85] Ibid., p. 209.

[86] Ibid., p.207.





የደብረ ሐይቅ ገዳም አቃቤ ሰዓቶችን ግፊት ተቋቁመው በመላው ሰሜን ኢትዮጵያ የሰሜን/ፈላሻን አገር ጨምሮ በቀይ ባሕርና በጎጃም መካከል በሚገኘው ክልል ከክርስትና ጎን የኦሪት ሃይማኖትን አስፋፍተው መሠረቱ።

በተጠቀሰው ዘመን አመፀኛ እዎስጣጤዎሳ ውያን መነኩሳት፥ ገዳማትና ምዕመናን በአንድ በኩል የክርስትና ሃይማኖትና ትምህርት በሚመለከት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያንና ከኢትዮጵያ ሰለሞናዊ መንግሥት እንዲሁም ከደብረ ሐይቅና ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ግንኙነት አቋረጡ።

በሌላ በኩል ደግሞ በዘመኑ በቀይ ባሕር ለግብፅ መንግሥት ገባር ከነበረውና በኢትዮጵያውያን ሥዩመ ባሕር ተብሎ ከሚጠራው እስላማዊ የዳህላክ ደሴት መንግሥት ሱልጣን ጋር ጠንካራ የንግድና የወዳጅነት ስምምነቶች ፈጠሩ።[87] በዚህ ወቅትና ጉዳይ በሐማሴን የደብረ ቢዘን ገዳም መሥራች መነኩሴው ፊልጶስ በአካባቢው የእዎስጣ ጤሳውያኑ የኦሪት አመፅ ግምባር መምህርና መሪ ሆነ።

እንደዚህ በሥፍራ፥ በጊዜና በትምህርት በፍጥነት እያደገና እየተስፋፋ የመጣውን የእዎስጣጤዎሳውያንን የኦሪት አመፅ በኃያል እርምጃ ለማጥፋት፥ በግብፁ አቡነ በርተሎሜዎስ (1399-1431) እና በደብረ ሐይቁ ገዳም አቃቤ ሰዓት ሠረቀብርሃን ጥምር ግፊት በ1400 አጼ ዳዊት (1382-1412) የአመፁ ግምባር መሪዎችና መምህራን ከየአ ከባቢያቸውና ከየገዳማቸው በቤተ አማራ በጉባኤ ላይ ተገኝተው ከአ ቡኑና ከአማራ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር በጉዳዩ ላይ በይፋ እንዲ ከራከሩበት አዘዘ።[88]

በንጉሡ ትዕዛዝ መሠረት እዎስጣጤዎሳውያኑ አመፀኛ መነኩ ሳትና መምህራን በደብረቢዘኑ መነኩሴ ፊልጶስ መሪነት በጉባኤው ላይ ቀርበው በግብፁ አቡነ በርተሎሜዎስና በደብረ ሐይቁ ገዳም አቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ከተመሩ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚ ኃይሎች የኦሪት አመፃቸውን ትተው ወደ ግብፃውያኑ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት በይፋ እንዲመለሱ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ውድቅ አድርገው በአመፃቸው የባሰ ጸኑበት። በመሆኑም ተቃዋሚ ኃይሎች የግዞት እና የሞት ቅጣት ወሰኑባቸው። በዚሁ መሠረትና ምክንያት የአማፅያኑ መሪ መነኩሴው ፊልጶስ ለአራት ዓመታት በቤተ

[87] S. Tadeschi. "Note Storiche Salle Isole Dahlack," Proceedings of The Third International Conference of Ethiopian Studies. 3 Vols., (Addis Ababa, 1966), I, p. 61.

[88] Taddasse Tamrat, The Abbots of Dabra- Hyq 1248-1535", pp. 103-4; Church and State, pp. 213-14.

አማራ በግዞት ኖረ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ለግብፃውያኑ ግዞትና ጥቅም ጥብቅና የቆመውና የካህናቱ የነፃነት አመፅ ቀንደኛው ጠላት የሆነው አቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ከሞተ በኋላ፥ በ1404 ፊልጶስ በኅብረተሰቡ ግፊት ከግዞት በነፃ ተለቀቀ። ከሁለት ዓመታት በኋላ በ1406 በ79 ዕድሜው ሞተ። አመፁ ግን ከእርሱ ጋር አልሞተም።

ከተግባርና ከታሪክ አኳያ በ1400 በቤተ አማራ ጉባኤ ላይ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን፥ እምነትና ትምህርት ላይ በሃይማኖት ስም በይፋ ባካሄዱ ብሔራዊ የነፃነት አመፅ እዎስጣ ጤዎሳውያኑ መነኮሳትና መምህራን በሁለቱ የግብፅና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች አንጃ ላይ የክርስቲያን ሕዝቡንና ኅብረተሰቡን አጠቃላይ ቁጣ ቀሰቀሱ። የሕዝበ ክርስቲያኑን የአገር ክብርና ነፃነት ስሜት አጋጋሉ።[89] ሁለቱንም ማለትም ክርስትናንና ሥርዓተ ኦሪትን የኢትዮጵያ ጥምርና ነፃ ሃይማኖቶች አደረጉ። በመሆኑ በኢትዮጵያ በግብፁ ምንደኛ ቤተ ክርስቲያን ላይ የመጀመሪያውን የእምነት፥ የርዕዮተዓለም እና የትምህርት ሽንፈት፥ ኪሣራና ውድቀት አደረሱ። በተጨማሪም በሚቀጥሉት አምስት አሥርታት የገዳማትንና የአብያተ-ክርስቲያናትን ግምባታና ትምህርት በመላው ሰሜን ኢትዮጵያ የበለጠ አስፋፉ።[90]

ባጭሩ ቄሶቹ በአካባቢው አራቱን አጎራባችና ተዛማጅ የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦችንና ማኅበረሰቦችን በግዕዝ ቋንቋና በጥምር የክርስትናና የኦሪት ሃይማኖቶች መሠረት አንድ በሀውርታዊ ኅብረተሰብ አደረጉ። ለማኅበረሰቦቹም ማኅበራዊና ባህላዊ መስተጋብርና መወራረስ መሠረትና መሣሪያ የሚሆኑ ብዙ የገዳም ድርጅቶችንና ማዕከላትን ከግዕዝ ብራና ሥነ ፅሑፍ ጋር ገነቡ። በውጭ ግንኙነት በኩልም በቀይ ባሕር ከዳህላክና ከምፅዋ ሥዩመ ባሕሮች ማለትም ሱልጣኖች ጋር ነፃ የንግድና የወዳጅነት ግንኙነቶችን የበለጠ አስፋፉ።

በዚህ ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት የኢትዮጵያ ሰለሞናዊ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት ጉዳይ በሁለት እንዳይከፈል ከፍተኛ ሥጋትና ፍርሃት ያደረበት አጼ ዘርዓያዕቆብ (1434-68) በ1450 በሸዋ ክፍለ ሀገር በምጥማቅ ቤተ ክርስቲያን በሰየመው ጉባኤ በግብፁ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን፥ እምነትና ትምህርት ላይ ሁለቱንም የክርስትናና የኦሪት እምነቶችንና ሥርዓተ በዓላትን ነፃ፥ እኩልና ሕጋዊ የመንግሥቱ እምነቶች እንዲሆኑ በመወሰን ለችግሩ በፖለቲካ ጥበብ የጥገና መፍትሔ አገኘ።[91]

---

89 Ibid., Church and State. pp. 216-17.

90 Ibid., pp. 211.

91 Ibid., pp. 219-220.





## የ1332-1632 የሰሜን/ፈላሻና የክርስቲያን ነገሥታት ጦርነቶች

### *የደቡብ ኢትዮጵያውያን አመፅ ተጽዕኖ በሰሜን/ፈላሻ ታሪክ ላይ*

በ330 ዓመተ ምህረት የክርስትና ሃይማኖት ወደ አዋማዊ የአክሱም አገርና ቤተ መንግሥት ከመግባቱ በፊት በግሪክና በግዕዝ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ በተጻፉ የአክሱም መንግሥታዊ የዜና መዋዕል ሰነዶች ግዕዝ፥ አጋሜ፥ አድዋ፥ አገው፥ ሰሜን፥ አክሱም፥ ወልቃይት፥ ዳሞ፥ ሐማሴን... ሁሉም በአካባቢው በሥፍራና በስም የታወቁ ጥንታዊ ሕዝቦችና አገሮች ናቸው።

ዛሬ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የተሰኙ የአገርና የሕዝብ ስሞች ታሪካዊ መነሻና ትርጉም በሚመለከት በጥንት ይሁዳውያኑ መፅሐፈ ኦሪት (ብሉይ ኪዳን) በአፍሪካ አህጉር በላይኛው የአባይ ሸለቆ ኩሽ (ኑቢያ) የተሰኘ አንድ ጥንታዊ የጥቁር ሕዝብና አገር ስም መጽሐፉ ከ280 ዓመተ ዓለም በኋላ በግብፁ የእስክንድርያ ከተማ ከይሁዳውያኑ ቋንቋ ወደ ግሪክ ሲተረጎም ኢትዮጵያ (ጥቁር) ተብሎ እንደተተረጎመ ታውቋል። ከሰባት ምዕተ ዓመታት በኋላ በዘመነ ክርስትና በ470-550 በአክሱም ከተማ በዘጠኙ ጻድቃን የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግዕዝ ሲተረጎም አሁንም ኢትዮጵያ ተብሎ ተገለበጠ።

በመጨረሻም በ550-1300 'የጨለማ' ክፍለ ዘመን ፍጻሜ ገደማ ማለትም በ1225 በአረብኛ ትርጉም ሀበሻ (አቢሲኒያ) በተሰኘ የአገር ስም ተጽፎ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ክብረ ነገሥት ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ በአጼ ዐምደፅዮን ዘመን (1314-44) በ1320 ገደማ በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ ይስሐቅና በአምስት ወዳጆቹ ወደ ግዕዝ ቋንቋ በተተረጎመ ጊዜ ሀበሻ የተባለው የአረብኛ ስም አሁን ኢትዮጵያ ተብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የአንድ ሕዝብና አገር መንግሥታዊ ስም ተደርጎ ተወሰደ።

ከዚያ ወዲህ ሁለቱም የግዕዙ ቋንቋ ሕገ ኦሪትና ክብረ ነገሥት መጻሕፍት ለኢትዮጵያ ሰለሞናዊ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና ምሁራን ብቻ ሳይሆን ለአጎራባቹ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥትም የሃይማኖትና የመንግሥት ሰነዶች ሆኑ። የሁለቱም ሰለሞናዊ የአማራና የሰሜን/ፈላሻ ተፃራሪ ነገሥታትና ካህናት በአንድ በኩል ራሳቸውን በኢትዮጵያ እንደመጤ ይሁዳውያን እንዲሁም የሕገ-ኦሪትና የክብረ ነገሥት መጻሕፍትን እንደየራሳቸው ታሪክና ሕግ አድርገው በመውሰድ «ምርጥ» የአብርሃም፥ የይስሐቅ፥ የዳዊትና የሰለሞን ዘርና

ልጆች ማለትም እሥራኤላውያን ነን ብለው አወጁ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ነባር ባህል፥ ሃይማኖትና ታሪክ የአረመኔዎች ጣኦትና ባህል ነው በማለት ማጥፋት ጀመሩ። በፖለቲካና በእምነት ግፊት የዘርና የስም ለውጥ አደረጉ።

ለሁለቱም ሰለሞናውያን ነን ለሚሉ ተፃራሪ ኃይሎች ሁለቱንም የኦሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች አጣምረውና አዛምደው በግዕዝ ሕገ ኦሪትና ክብረ ነገሥት መጻሕፍት የሚያስተምሩና የሚተረጉሙ ከላይ የቀረቡ የኢትዮጵያ የትግሬ-አማራ መነኩሳትና ገዳማት ናቸው። ነገር ግን በመካከላቸው እንደዚህ በተረት፥ በዘር፥ በቋንቋ፥ በሥፍራ፥ በጊዜ፥ በታሪክና በሃይማኖት የተፈጠረው የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታና ሂደት የአማራና የሰሜን/ፈላሻ አጎራባች ነገሥታትና መንግሥታት በመሬት፥ በገበያ፥ በፖለቲካና በግዛት ጉዳዮችና መስኮች ለነበራቸው ጂኦ-ፖለቲካዊ ጦርነት የሰላም አማራጭ ወይም መፍትሔ አልሰጣቸውም።

ከዚህ አኳያ በአካባቢው በግምት በተከዜና በዓባይ ወንዞች መካከል ሰሜን፥ ወልቃይት፥ ፀለምት፥ ፀገዴ፥ ወገራ፥ አርማጭሆ፥ በጌምድር፥ ጭልጋ፥ ደምቢያ፥ ቋራ የተሰኙ አገሮችን አጠቃሎ የሚይዘው እስትራቴጂያዊ ምድር፥ በዚህ ጥናት ተደጋግሞ በሰነዳዊ መረጃ እንደተገለፀው፥ ከጥንት ጀምሮ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ አገር ነው። ይህንኑ አንጡራ ያባት አገር ተጠቃሹ ሕዝብና መንግሥት በ300ዎቹና በ320ዎቹ ከአጎራባቹ የአክሱም መንግሥት ወረራ ለመከላከል ያካሄደው ታሪካዊ ትግል ከዘመኑ የግሪክና የግዕዝ ዜና መዋዕሎች ከላይ ተገልጿል።

ከዚያ ከ300ዎቹ የአክሱም-ሰሜን/ፈላሻ የመጀመሪያው የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት ሚሊኒየም በኋላ በ1332 አጼ አምደፅዮን ከክርስትና ሃይማኖት ወደ አይሁድ ሃይማኖት የገቡ አማፅያን ናቸው የሚላቸውን አራት የሰሜን፥ የወገራ፥ የፀለምትና የፀገዴ ማኅበረ ሰቦችን (የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና አገር) በኃይል ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንዲመለሱ ከዳሞት፥ ከሰቀልት፥ ከጎንደርና ከሀዲያ አገሮች የተመለመሉ ምርጥና ታዋቂ የፈረስና የእግር ጦር ሠራዊቶችን በአንድ ፀጋ ክርስቶስ በተሰኘ የበጌምድር ገዥ አዝማችነት ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ አዘመቱ ባቸው በቃሉ ይመሰክራል።[92]

[92] Huntingford, Amda Seyon, pp. 11-2; J. Perruchon, tr. and ed., Histoires des Guerres d' Amba Syon, Roi D' Ethiopie, Journal Asiatique, Ser. 8, Vol. 14 (1889). pp. 339-340.





ባጭር አነጋገር ከሁለቱ የ300ዎቹና የ320ዎቹ የአክሱም-ሰሜን/ፈላሻ ጦርነቶች ጀምሮ በአንድ ሚሊኒየም ክፍለ ዘመን ውስጥ በአጼ አምደ ፅዮን ዜና መዋዕል ነው የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና ምድር ለሦስተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ የመንግሥት ሰነድ ተጽፎ የተገኘው። በመሆኑም ከእውነትና ከእውቀት አኳያ፥ በ550-1270 ክፍለ ዘመን የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት የአክሱሙን መንግሥት ያፈረሰና ያጠፋ ባዕድ ጠላት ነው የሚለው የኢትዮጵያ የሰለሞናውያን ክስ የታሪክ መሠረት የሌለው ተረት ነው። በመሆኑም ከዚህ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ታሪክ ውጭና ውድቅ የሆነ ተረት ነው።

በሌላ በኩል ከታሪክ አኳያ፥ በተጠቀሰው የተከዜ-ዓባይ እስትራቴጂያዊ ምድር ላይ በተጨባጭ የመሬት፥ የገበያ፥ የግዛትና የእስትራቴጂ ጉዳዮችና ምክንያቶች በነባሩ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና በአዲሱ ሰለሞናዊ የአማራ መንግሥት መካከል ከ1332 እስከ 1632 ድረስ ለ300 ዓመታት ረጅም የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት እንደተካሄደና በመጨረሻ ተጠቃሹ ነባር ሕዝብ ከአገሩ እንደተነቀለ ሃይማኖቱም እንደተሰረዘ ቋንቋውና ባህሉም እንደጠፋ በድል አድራጊ ሰለሞናዊ የአማራ አጼ ነገሥታት አምደፅዮን፥ ዳዊት፥ ይስሐቅ፥ ዘርዓያዕቆብ፥ በዕደ ማርያም፥ እስክንድር፥[93] ናኦድ፥ ልብነድንግል፥ ገላውዴዎስ፥ ሚናስ፥ ሠርጸድንግልና ሱስንዮስ ዘመናት፥ ጸሐፊዎችና ዜና መዋዕሎች ተመዝግቦ ለትውልድና ለታሪክ በይፋ ተላልፈዋል።

ታሪኩን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ከእነዚህ ነገሥታት፥ አጼ ይስሐቅ (1414-1429) ተጠቃሹን ሕዝብ በክርስትና ሃይማኖት ባይጠመቅና ለክርስቲያኑ ንጉሥም ባይገብር ከአገሩ ንቅል ስደተኛ፥ ሒያጅ፥ ፈላሲ (ፈላሻ) የሚያደርግ ሕግ አወጀ።[94] ሕጉም «ፈላሻ» ለሚለው የሰሜን ሕዝብ አዲስ የስድብና የጭቆና ስም መነሻ ሆነ። አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ደግሞ የሰሜን/ ፈላሻ ሕዝብ ከሕገ ኦሪት ተመልሶ በክርስትና ሃይማኖት ባይጠመቅ በሙሉ እንዲገደል የሚያደርግ የሃይማኖት ሕግ አውጥቶ በጦር ኃይል በተግባር ላይ ለማዋል ሞከረ። ይሁን እንጂ በሁለት የሕዝብ መሪዎች ማለትም በፀለምቱ አምባ ነሐድና በሰሜኑ ፀጋይ አመፅር ሰሜን/ፈላሾች ንጉሡን በአፀፋ ጦርነት አሸንፈው መለሱት።[95] እንዲሁም የሰሜን/ፈላሻ መሪዎች

[93] Arab Faqih, Conquete, p. 458 Note 1; Conti Rossini, Sarsa Dengel p. 107.

[94] Taddasse Tamrat, Church and State, p. 201.

[95] J. Perruchon, ed., Les Chroniques de Zarayaqoeb et de Baeda Maryam, (Paris, 1893), pp. 96-97.

የንጉሡን ጦርና ሹማምንቶች እንደደመሰሱ፣ በበጌምድር በክርስቲያኖች ሕይወትና ንብረት ላይም ታላቅ ጥቃትና ጥፋት እንዳደረሱ፣ ብዙ ክርስ ቲያኖችን በኃይል ወደ ኦሪት ሃይማኖት እንደመለሱ በንጉሡ ዜና መዋዕል ተመልክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ መነኩሴው የንጉሡ ልጅ አባ ሰብራ በአመጽ ወደ ኦሪት ሃይማኖት ገብቶ በስሜን/ፈላሻ አገር የገዳም ትምህርትና ሥርዓት እንደአስፋፋ ተገልጿል።[96]

ስሜን/ፈላሾች በአጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመን በክርስቲያኑ መንግ ሥትና ጦር ላይ የከፈቱትን የማጥቃት ዘመቻ በልጁና በአልጋ ወራሹ በዕደማርያም ዘመንም (1468-78) በአምባነሐድ አዝማችነት ለሰባት ዓመታት የበለጠ አጠናክረው እንዳስፋፉና በመጨረሻ ግን የንጉሡ የበጌምድር ገዥ አዝማች ማርቆስ በፖለቲካ ተንኮል ብዙዎቹን ሰብስቦ የሙያ፣ የዕድሜና የጾታ ልዩነት ሳያደርግ በብዛት እንደገደላቸው ታውቋል።[97]

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በመጨረሻ፣ ከተግ ባር፣ ከታክቲክ፣ ከእስትራቴጂና ከውጤት አኳያ በ1332-1632 ክፍለ ዘመን በክርስቲያን ነገሥታትና በስሜን/ፈላሻ ነባር ሕዝብ መካከል የተካሄደው ረጅም የጂኦፖለቲካና የሃይማኖት ጦርነት በሁለት ርዕሶችና ክፍለ ጊዜያት ተከፍሎ ሊቀርብ ይችላል።

አንደኛ፣ ከ1332 እስከ 1524 ድረስ ክርስቲያን ነገሥታቱ ከሸዋ ማዕከላቸው በደቡብ ኢትዮጵያ ነባር አዋማዊና እስላማዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ ዘውትር የንግድ፣ የግዛትና የሃይማኖት ጦርነቶች በማካሄድ ላይ ስለነበሩ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተከዜ-ዓባይ እስት ራቴጂያዊ ክልል የሰሜን/ፈላሻን ሕዝብና አገር በተመሳሳይ የትጥቅ ፖሊሲና ተግባር ለመያዝና ለመግዛት ጊዜም አቅምም አልነበራቸውም።

በሌላ በኩል የ1337-1450 የእዎስጣጤዎሳውያኑ የኦሪት እምነት፣ ትምህርትና አመፅ በአካባቢው በአራቱ የትግሬ፣ የሰሜን/ ፈላሻ፣ የአገ ውና የአማራ ማኅበረሰቦች መካከል በሃይማኖት፣ በትምህርት፣ በባህልና በግዕዝ ሥነጽሑፍ አማካይነት መሠረታዊና ዘላቂ የሆነ የመስተጋ ብርና የመወራረስ ሁኔታና ሂደት ፈጠረ። በመሆኑም በአራቱ የአካባቢው ሕዝቦችና ማኅበረሰቦች ዘንድ የነገሥታቱ የጠረኝነትና የዘረኛነት ፖሊ ሲና ተግባር ሕዝባዊ መሠረት፣ ተቀባይነትና ድጋፍ አልነበረውም።

[96] Hess, "Falasha History", p.113.

[97] Conti Rossini (tr. & ed.,), History Regi d'Sarsa Dengle, (1907), p. 111; Budge, History, p. 316.





ሁለተኛ፣ በመጨረሻ ሁለቱ ታላላቅና ተዛማጅ የ1524-1543 የአዳሉ ኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ (1506-1543) የአመፅ ጦርነትና የ1520-1660 ታላቁ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴ በአንድነት ክርስቲያን ነገሥታትንና ሰፋሪ ኃይሎችን ከመላው ደቡብ ኢትዮጵያ በማስወጣት በአንድ በኩል በታላቁ የተከዜ-ዓባይ እስትራቴጂያዊ ምድር ለሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት ውድቀት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለአዲሱ የጎንደር አካባቢ መንግሥት (1577-1855) ክስተትና ዕድገት ሁለአቀፍ የአካባቢ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የእስትራቴጂ፣ የጎሳና የሃይማኖት ግፊቶችንና ቅድመ ሁኔታዎችን ፈጠሩ።[98]

### *በሰሜን/ፈላሻ አገር የጎንደር መንግሥት ታሪካዊ መነሻና ውጤት*

ከ1524 እስከ 1535 ድረስ ኢማም አሕመድ ግራኙ የአጼ ልብነ ድንግልን መንግሥትና ጦር ደምስሶ መላ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉርን በቀይ ባሕር እስላማዊ የዳህላክና የምፅዋ ደሴቶችን ጨምሮ ከሥሩ አዋለ።[99] ከ1535 እስከ 1543 ድረስ ለዘጠኝ ዓመታት በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሰሜን/ፈላሻ ምድር የደምቢያን ለምና ሀብታም አገር የሱልጣኔቱ (የመንግሥቱ) መሠረትና ማዕከል አድርጎ ቆረቆረ።[100] በዚህ ወቅትና ሁኔታ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት በአጼ ልብነ ድንግል መንግሥትና ጦር ላይ ከኢማም አሕመድ ግራኙ ግምባር በኅብረት ተሰለፈ።[101] ይሁን እንጂ በ1543 የንጉሡን ክርስቲያን መንግሥትና ጦር ለመርዳት ከሕንድ የመጣው የፖርቱጋል የነፍጠኞች ግብረ ኃይል የኢማም አሕመድ ግራኙን ክፍለ አህጉራዊ ሱልጣኔት ደመሰሰ።

በየካቲት 1543 በደምቢያ ክፍለ ሀገር በጣና ሐይቅ አጠገብ በወይናደጋ ጦር ሜዳ በጥምር የፖርቱጋል ነፍጠኞች ግብረኃይልና የአጼ ገላውዲዎስ ሠራዊት ኅብረት የኢማም አሕመድ ግራኙ ጦርና ሱልጣኔት ተደመሰሱ። ከዚያ በኋላ ከ1543 እስከ 1597 ድረስ ለስድስት አሥርታት ሦስቱ አጼ ነገሥታት ገላውዴዎስ፣ ሚናስና ሠርፀድንግል በክፍለ አህጉሩ በ1524- 1543 የኢማም አሕመድ ግራኙ አመፅና በታላቁ የ1520-1660 የሕዝቦች እንቅስቃሴ ጥምር ግፊት የፈረሰውን የሰለሞና

[98] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ ም 3-4

[99] Arabfaqih, Conquete, pp. 456-59.

[100] Ibid., p. 461.

[101] Ibid., pp. 458-59

ውያንን መንግሥትና ጦር በክፍለ አህጉሩ እስላማዊ፥ አዋማዊና አረ ታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ መልሰው ለመቋ ቋም ያካሄዱ የትጥቅና የሃይማኖት ጥረቶች[102] ሁሉ ሳይሳኩ ቀሩ። ነገር ግን በተለይ ሁለቱ አጼ ነገሥታት ገላውዴዎስና ሠርፀድንግል በፊት ለሰለሞናውያኑ መንግሥት ለሦስት ምዕተ ዓመታት ሁለት ታላላቅ የጂኦ-ፖለቲካ ጠላ ቶች የነበሩትን የአዳል ሱልጣኔትና የሰሜን/ ፈላሻ መንግሥት ለመጨረሻ ጊዜ በጦር ኃይል አጠፉ።[103]

ከዚህ አኳያ ከኢማም አሕመድ ግራኝ ሞት በኋላ ከየካቲት እስከ መስከረም 1543 ድረስ፥ አጼ ገላውዴዎስ ጊዜያዊ ጦር ሠፈሩን በደምቢያ አድርጎ የደምቢያ፥ የጎጃም፥ የበጌምድር፥ የላስታ፥ የሰሜን/ ፈላሻ፥ የትግሬ ሕዝቦችንና አገሮችን ከሥሩ በሹም ሽር አደራጃቸው።

በዚህ ወቅት በሌላ ግምባር እንዲሁም የሟቹ ኢማም አሕመድ ግራኝ የወንድም ልጅና አልጋወራሹ ወዚር ዓባስ አቡን ከበጌምድር የቀድሞ ግዛቱ ከኢማሙ ዝነኛዋ ሚስት ከባእትያ ድል ወንበራ ማሕፉዝ ጋር በሽሽት አምልጦ በደቡብ ምስራቅ ሦስቱን የፈጠጋር የደዋሮና የባሌ አጎራባች እስላማዊ አገሮችን በአንድነት ከሥሩ አደራጃቸው።

በደቡብ ምስራቅ በወዚር አባስ አቡን ወደሚመራው አዲሱ የአዳል መንግሥት ግምባር ከመመልሱ በፊት አጼ ገላውዴዎስ በፖርቱ ጋል ነፍጠኞች እርዳታ በደቡብ፥ በደቡብ ምስራቅና በመሀል ምዕራብ ኢትዮጵያ የሸዋ፥ የዳሞት፥ የጋፋት፥ የእናርያ፥ የቦሻ፥ የጉራጌ፥ የዋጅና የሀዲያ ሕዝቦችንና አገሮችን ከሥሩ ለማምጣት ያልተሳኩ ወታደራዊ ዘመቻዎችን በማካሄድ በአገሮቹ ላይ በሕይወ ትና በንብረት ታላቅ ጥቃታና ጥፋት አደረሰ።

በተጨማሪም በ1543 መጨረሻ በዝዋይ አዋሽ ክልል የዋጅን አገር የመንግሥቱ አዲስ ማዕከል አደረጎ ያዘ። ከ1543 እስከ 1559 ድረስ የንጉሡ የዋጅ ጦር ሠፈር በአዳልና በኦሮሞ እንቅስቃሴዎች ግምባር የአገሪቱ ዋናው የፖለቲካና የጦርነት ዞን ሆነ።

በጥቅምት 1544 አጼ ገላውዴዎስ ወዚር አባስ አቡንን በዋጅ ጦርነት ገደለ። ከዚህ ከወዚር አባስ አቡን ሞት በኋላ ከዋጅ ማዕከሉ አጼ ገላውዴዎስ በተከታታይ በሀዲያ፥ በጉራጌ፥ በዳሞት፥ በጋፋትና በእናርያ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ብዙ የቅጣት፥ የዘረፋ፥ የፀጥታና የግብር ዘመቻዎችን አካሄደ። በተጨማሪም በቢፎሌ ሉባ ዘመን (1546-1554)

---

[102] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ም 5.

[103] Ibid.,





ከአዋጅ ሠፈሩ ተነስቶ ከኦሮሞዎች ጋር በባሌ አካባቢ በአገሩ ታሪክ የመጀመሪያውን ጦርነት አካሄደ።

ከ1540ዎቹ ሁለተኛው አጋማሽ እስከ 1550ዎቹ ድረስ አጼ ገላውዴዎስ ከዋጅ የጦር ሠፈሩ ከአዳሎች፥ ከኦሮሞዎች፥ ከሀዲያዎች፥ ከፖርቱጋሎችና ከቱርኮች ጋር በትጥቅ፥ በፖለቲካና በሃይማኖት ሲዋጋ ዘመኑን በጦር ሜዳ ሞት ፈጸመ።

ከዚህ አኳያ ከ1547 እስከ 1550 ድረስ አጼ ገላውዴዎስና ሁለቱ ታላላቅ የጦር አበጋዞች ራስ ፋኑኤልና ራስ ሐመልማል ከሐረር እስከ ዜይላ «ከበር ሰዕደዲን እስከ በር አጀም ድረስ» ማለትም ከአዋሽ እስከ ኤደን ባሕረሰላጤና እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍ ድረስ በታላቁ የአዳል አገርና መንግሥት ላይ ብዙ ተከታታይ የቅጣት ዘመቻዎችን በማካሄድ በሕይወትና በንብረት ታላቅ ጥቃትና ጥፋት አደረሱ። መንደሮችን፥ ከተሞችንና መስጊዶችን አፈራረሱ። አቃጠሉ።

በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ አጼ ገላውዴ ዎስና የጦር አበጋዞቹ እንደዚህ የበቀልና የጥፋት ዘመቻዎች ሲያካ ሄዱ፥ በሌላ በኩል በ1555-57 ቱርኮች በሰሜኑ ጠረፍ የዳህላክና የምፅዋ ደሴቶችን በጦር ያዙ። በሚቀጥሉት ዓመታትና አሥርታት ቱርኮች ከምፅዋና ከሰዋኪን ተነስተው በአርኪኮ፥ በሐማሴን፥ በሰራዬ፥ በደባርዋ፥ በአከለጉዛይ፥ በቡር፥ በትግሬና በመዘጋ ከተሞች፥ ቀበሌ ዎችና አውራጃዎች ላይ ረጅም የወረራ ጦርነት ከፈቱ።

ቱርኮች በሰሜን ኢትዮጵያ ላይ የወረራ ጦርነት በከፈቱበት ዘመን አጼ ገላውዴዎስ በደቡብ ምስራቅ፥ በአዋሽ-ዝዋይ ክልል፥ በፈጠጋርና በደዋሮ አካባቢ ከኦሮሞ የምችሌ ሉባ (1554-1562) ጋር በጦርነት ላይ ነበር። በዚሁም በ1558 በሰሜን ባሕረነጋሽ ይስሐቅን ከደባርዋ ከተማ በቱርኮች ላይ አዘመተ። በ1558 አጼውና ባሕረነጋሹ በየግምባራቸው በጠላቶቻቸው ላይ ድል ከተቀዳጁ በኋላ በመጋቢት 1559 በዋጅ ከአዳሉ ኤሚር ኑር፥ የሐረር ግምብ መሥራች፥ ጋር ሲዋጋ አጼ ገላውዴዎስ ራሱ ተገደለ።[104]

በአጼ ገላውዴዎስ ሞት ወንድሙ አጼ ሚናስ (1559-1563) ነገሠ። የአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት አጭር የውጥረት ወቅት ነበር። መንግሥቱ በደቡብ በአዳል፥ በሀዲያና በኦሮሞ የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴዎች፥ በሰሜን ደግሞ በሰሜን/ፈላሻና በባሕረ ነጋሽ ይስሐቅ አመፅ እንዲሁም በፖርቱጋሎችና በቱርኮች ግፊት እንደተወጠረ አጼ ሚናስ ራሱ በየካቲት 1563 በዋግ የዘረፋና የቅጣት ዘመቻ በማካሄድ ላይ

---

[104] W. Conzelman tr. and ed., Chronique de Galawdewos (Paris, 1895).

ሳለ በድንገተኛ ሕመም ሞተ። ከዚያ በፊት በሰሜን/ፈላሻ ላይ ወረራ አካሂዶ በሽንፈት እንደተመለሰም ታውቋል።

ከአጼ ሚናስ ሞት በኋላ፥ ከ1563 እስከ 1568 ድረስ፥ በክርስቲያኑ ቤተ መንግሥት አካባቢ ረጅም የሥልጣን ባላንጣዎችና አንጃዎች ጦርነት ተካሄደ። ከዚህ አኳያ የአጼ ሚናስ ሞት እንደተሰማ በቤተ መንግሥቱ አደባባይ አንድ የባለሥልጣኖች አንጃ የሟቹን የአሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ሠርፀ ድንግልን (1563-97) መለክሰገድ በሚል የዙፋን ስም በአክሱም ከተማ እንነገሠ። በራስ ሐመልማል የተመራ አንድ ሌላ የሥልጣን አንጃ በበኩሉ በደቡብ ማለትም በሸዋ አንድ ሌላ ባላንጣ መስፍን አነገሠ። ፋሲል የተሰኘ አንድ ሌላ የጦር አበጋዝ ደግሞ በምዕራብ ማለትም በዳሞት ሦስተኛውን መስፍን አነገሠ። ይሁን እንጂ የሠርፀድንግል አንጃ መለሳይ ተብለው የሚጠሩ እስላማዊ የአዳል ምንደኛ ወታደሮችን በቅጥር በመጠቀም የሐመልማልንና የፋሲልን አንጃዎች ደምስሶ የአጼውን በትረ ሥልጣን በእጁ አደረገ።[105] እነዚህ መለሳይ የተሰኙ የአዳል ወታደሮች በፊት የኢማም አሕመድ ግራኝ ወታደሮች ነበሩ።

በአዳሉ የመለሳይ ምንደኛ ወታደሮች ድጋፍ በሥልጣን ባላንጣዎቹ ላይ ፍጹም የኃይል ሚዛን ካገኘ በኋላ፥ አጼ ሠርፀ ድንግል በ1597 እስኪ ሞት ድረስ በሦስት አሥርታት ዘመን በውስጥና በውጭ ጠላቶቹ ላይ ማለትም በደቡብ በሀዲያዎች፥ በጉራጌዎች፥ በኦሮሞዎችና በአዳሎች ላይ፥ በሰሜን በባሕረነጋሽ ይስሐቅ፥ በቱርኮችና በሰሜን/ፈላሾች ላይ፥ በሰሜን ምዕራብ በአገዎችና በጉሙዞች ላይ፥ በመሀል ምዕራብ በዳሞቶች፥ በጋፋቶች፥ በእናርያ፥ በቢዛሞ፥ በቦሻና በጎንጋ ላይ ብዙ የማጥቃት፥ የቅጣትና የዘረፋ ጦርነቶች አካሄደ። ለንጉሡ በእነዚህ የወረራና የቅጣት ጦርነቶች ድል፥ ሀብትና ኃይል ያስገኙለት መለሳይ፥ ቁርባን፥ አቄትዝር፥ ጨረቃ፥ ጊዮርጊስ ኃይሌ፥ ቱርክ፥ አፍሮአይገባ፥ ኮከብ ተብለው በልዩ ልዩ ስሞች የሚጠሩ በከፍተኛ የጦር አበጋዞች የሚመሩና በአርሶ አደሮች ምርት፥ ንብረትና ጉልበት በዘረፋ የሚኖሩ የጪዋ ማለትም የወታደር ድርጅቶችና ኃይሎች ነበሩ።[106]

ከ1569 እስከ 1577 ድረስ እነዚህን በወረራና በዘረፋ የሚኖሩ የጦር ኃይሎችን አስከትሎ አጼ ሠርፀ ድንግል ከዋጅና ከግንደበረት የጦር ሠፈሮች በደቡብ በተጠቀሱ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ ብዙ ጦርነቶችን አካሄደ። በዚህ ወቅት በመጋቢት 1577 በዋቤ ሸለቆ ጦርነት በመለሳይ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች ድጋፍ የአዳሉን የመጨረሻ

[105] Conti Rossini, Sarsa Dengel, Chaps. 1-4.

[106] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ም 84-85.





ሱልጣን መሐመድ አራተኛን ከቀድሞ የኢማም አሕመድ ግራኝ የጦር አለቆችና ከሦስት የሐረሩ ኤሚር ኑር ልጆች ጋር በመግደል የአዳልን መንግሥት ወደ ዘመነ ፍጻሜው አደረሰ።

በመጋቢት 1577 የዋቤ ሸለቆ ጦርነት የአዳልን መንግሥት ከደመሰሰ በኋላ ለአጼ ሠርፀ ድንግል በደቡብ ኢትዮጵያ በአራት የጎሳ አካባቢዎችና ግምባሮች ተከፋፍለው በፍለሳ ሰምሪት ከእንስሳት መንጋዎቻቸው ጋር የሚንቀሳቀሱ የከረዩ፥ የወሎ፥ የቱለማና የሜጫኦሮሞ ማኅበረሰቦች፥ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የአገው፥ የሰሜን/ፈላሻና የጉሙዝ ሕዝቦች እንዲሁም በሰሜኑ ጠረፍ ከምፅዋ የቱርክ ወራሪዎች ከአካባቢው አማፅያን ጋር በትጥቅ የሚፋለሟቸው የውስጥና የውጭ ዋና ዋና ጠላቶች ሆኑ።

በዚህ ሁኔታና ወቅት ከመጋቢት 1577 የዋቤ ሸበሌ ጦርነት በኋላ አጼ ሠርፀድንግል በድቡብ ኢትዮጵያ የኦሮሞዎችን ግምባር ክፍት ትቶ ከነሠራዊቱ ጋር በሰሜን ምዕራብ በሰሜን/ፈላሻ ምድር በፊት የኢማም አሕመድ ግራኝ ዋና ማዕከል የነበረውን የደምቢያ ለምና ሰፊ የእርሻ አገር የጦሩና የመንግሥቱ ቋሚ ማዕከል አድርጎ ያዘ። ማለትም በአካባቢው የጎንደር ዘመነ መንግሥት (1577-1855) ግምባታ ተግባር ጉባኤ በተባለ መንደር በንጉሡ የጦር ሠፈር ተጀመረ።

## የሠርፀ ድንግልና የሰሜን/ፈላሻ ጦርነቶች (1580-1595)

### የቱርክ ነፍጠኞችና መድፎች በሰሜን/ፈላሻ ተራሮች

በ1578 አጼ ሠርፀ ድንግል በደምቢያ ከጉባኤ የጦር ሠፈሩ የአዳልን መለሳይና የኦሮሞን ሉባ የተባሉ ወታደሮችን ጨምሮ ከልዩ ልዩ አገሮችና ሕዝቦች በክተት አዋጅ የተጠራ ግዙፍ ሠራዊት አስከትሎ ከሚያዝያ እስከ ታኅሣሥ በሰሜን ኢትዮጵያ በባሕረነጋሽ ክፍለ ግዛት በቱርክ ወራሪዎችና ከ1563-1568 የሥልጣን ጦርነት ዘመን ጀምሮ የቱርኮች ተባባሪ በሆነው ባሕረነጋሽ ይስሐቅ ላይ ዘመተ። በጦርነቱ ሁለቱም ባሕረነጋሽና የቱርኩ ጦር አዛዥ በንጉሡ ወታደሮች ተገደሉ። ሠራዊታቸውም በንጉሡ ጦር ተደመሰሰ። የደባርዋ የጦር ምሽጋቸውም ፈረሰ። በተጨማሪም ብዙ የቱርክ ነፍጦች፥ መድፎችና ወታደሮች በንጉሡ ምርኮ ተወሰዱ። እነዚህ የቱርክ ነፍጠኞች፥ መድፎችና ወታደሮች በሚቀጥለው የሰሜን/ፈላሻ ረጅምና አስቸጋሪ የ1580-1595 ጦርነት ለንጉሡ የድል ሚዛን ወሳኝ መሣሪያዎች ሆኑ። በመሆኑም በመጋቢት 1579 ድል አድራጊው ሠርፀድንግል ከሰሜኑ ጦር ግምባር ከነሠራዊቱ በአክሱም በኩል አድርጎ በደምቢያ ወደ ጉባኤ የጦር ሠፈር ተመልሶ ገባ።

*የ1580 የካሌፍ አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት*

በ300ዎቹ አሥርት በሰሜን/ፈላሻ አገር ላይ የመጀመሪያ ወረራ ያካሄደው የአክሱም አዋማዊ ንጉሥ በግሪክ ዜና መዋዕሉ አገሩን «ዓመቱን በሙሉ ዝናብ፥ ብርድ፥ ውርጭና በረዶ» የማይጠፋበት በጣም አስቸጋሪ ተራራማ አገር ነው ብሎ እንደገለጸው ይታወቃል። ከ1280 ዓመታት በኋላ በጥቅምት 30 ቀን 1580 በሰሜን ተራራ «ካሌፍ አምባ» ላይ በአጼ ሠርፀ ድንግልና በሰሜን/ፈላሻው መሪ ካሌፍ ወታደሮች መካከል በመድፍና በመርግ (በድንጋይ ናዳ) የተካሄደውን ጦርነት በአይኑ አይቶ የመዘገበው ወልደ ሃይማኖት የአጼው ዜና መዋዕል ጸሐፊ፥ «የሰሜን ምድር ክፋት»[107] በሚል ርዕስ እንደ ሚከተለው ይገልጻል።

> *አንደኛ፥ የአገሩ መንገድ ሁሉ ገደላማ ነው። ፈረሶች በቅሎችና አህዮች በሰሜን ተራሮች መንገድ ላይ አይሄዱም።*
>
> *ሁለተኛ፥ የተራሮቹ ኃይለኛ ውርጭና ብርድ ያልለመደውን የውጭ ሰው ኢያኖሩም።*
>
> *ሦስተኛ፥ በተራራው አምባዎች ላይ ሁልጊዜ በረዶ ይወርዳል። ለምሳሌ፥ በጥቅምት 30 ቀን 1580 የአገሩ መሪ ካሌፍ በአምባው ላይ በአጼ ሠርፀድንግል ጦር በተከበበ ቀን ሌሊቱን በረዶ ሲወርድ አደረ። ሲነጋም በንጉሡ ድንኳንና በጦሩ ሠፈር ዙሪያ ሙሉ የበረዶ ክምር ነበር። የሠፈሩ ሰዎች ወዲያና ወዲህ ሲንቀሳቀሱ በበረዶ ላይ መሄድ ጀመሩ።*[108]

ዘመናዊ የነፍጥና የመድፍ መሣሪያዎች በፖርቱ ጋሎችና በቱርኮች አማካይነት ወደ አገሩ እስኪገቡ ድረስ ከአጎራባች የአክሱም፥ የአገውና የአማራ ተከታታይ መንግሥታትና ነገሥታት ግፊት የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብን ብሔራዊ ነፃነት ለዘመናት ጠብቀው ካኖሩት ብዙ ሁኔታዎች እና ኃይሎች አንዱ ይኸው የአካባቢ ልዩ የተፈጥሮ ገፅታ ነው ለማለት ይቻላል።

ከዚህ ከተፈጥሮ ሁኔታ አንድ ሌላ የሰሜን/ ፈላሻ ሕዝብና አገርን ለረጅም ዘመን በሉአላዊ ነፃነት ያኖረው የራሱ የሕዝቡ አስገራሚ የመርግ ማለትም ከተራራ አናት በጠላት ላይ የሚወርደው የድንጋይ ናዳ መሣሪያ ነው። በከፍተኛ የሰሜን ተራራ አምባዎች ዙሪያ ከላይ ከገደል አፋፍ ወደታች በጠላቶች ላይ የሚለቀቁ መርጎች በመጫኛ ታሥረው ይኖራሉ።

ከዚህ አኳያ ለምሳሌ በታኅሳስ 1580 በረድ ኤት አምባ ላይ የንጉሡ የቱርክ ነፍጠኞችና መድፈኞች በአዲሱ የጦር መሣሪያና ሥልት ወረራ ባካሄዱበት ጊዜ በተጠቀሰው አምባ ዙሪያ ከአጼ

[107] Conti Rossini, Sarsa Dengel, p. 112.

[108] Ibid., p. 112.





ነገሥታት በዕደማርያም፥ እስክንድርና ናኦድ[109] ዘመናት ጀምሮ በመጫኛ የታሰሩና ብርሃን፥ ሀሳብና ባዋ ተብለው የሚጠሩ የመርግ መሣሪያዎች ከጠባቂዎች ጋር ተጠምደው እንደተገኙ የንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሓፊ ወልደ ሃይማኖት አስታውቋል። በተጨማሪም ከነሱ የሚወለደው የቋራው ካሣ-ቴዎድሮስ በኋላ እንደሚያደርገው ሰሜን/ፈላሾች በጠላት እጅ ምርኮኛ ሆነው ከመዋረድ በገደል ውስጥ በመውደቅና እርስ በርሳቸው በጉራዴ ስለት በመሰያየፍ ራሳቸውን በቅድሚያ መግደል እምነታቸውም ባህላቸውም ነበር።

እነዚህን ልዩ የተራራ ጦር መሣሪያዎችን፥ ሥልቶችንና ልምዶችን በመጠቀም አምባ ነሐድና ፀጋይ የተባሉ የሰሜን/ፈላሻ የጦር መሪዎች አፄ ዘርአያ ዕቆብንና ጦሩን ከአገራቸው በሽንፈት እንደመለሱ፥ እንደገና አምባነሐድና ተከታዮቹ ከአፄ በዕደማርያም ጋር ለሰባት ዓመታት እንደተዋጉ በ1559 ደግሞ ረድኤት የተባለ ያገር መሪ የአፄ ሠርፀድንግልን አባት የአጼ ሚናስን ወራሪ ጦር ከምድረ ሰሜን/ፈላሻ አሸንፎ እንደ መለሰው ይታወሳል።

በመጨረሻ በጥቅምት 1580 አጼ ሠርፀድንግል ራሱ ከደምቢያ ጦር ሠፈር የቱርክ ነፍጠኞችንና መድፈኞችን ጨምሮ ከትግሬ፥ ከአማራ፥ ከአገውና ከኦሮሞ ወታደሮች የተገነባና በ1578 በሰሜን ጦር ግምባር የቱርክንና የባሕረነጋሽ ይስሐቅን ሕብረ ሠራዊት በደመሰሱ የጦር አበጋዞች ሐሊቦ፥ ደሀርጎት፥ ዮናኤል፥ ተክለ ጊዮርጊስ፥ ዕቁበ ሚካኤልና አባ ንዋይ በሚባል የግምባር ጦር አዛዥ መነኩሴ በሕብረት የሚመራ ግዙፍ ሠራዊት አስከትሎ የሰሜን/ፈላሻ ጦረኛ መሪ «ረድኤት የእህል፥ የማር፥ የላምና የበግ ግብር» አልከፈለም በሚል የጠብ መቀስቀሻ በወገራና በሰሜን አጎራባች አውራጃዎች ላይ ታላቅ የዘረፋ ጦርነት በራሱ የበላይ አመራርና ቁጥጥር ከፈተ።

በመሆኑም ረድኤትና ወንድሙ ካሌፍ ባልተለመደ አዲስ የነፍጥና የመድፍ መብረቃዊ መሣሪያዎች ታጥቆ ከመጣው ጠላት ጋር በታወቀው የሰሜን/ፈላሻ የመርግ መሣሪያ በግምባር ለመጋጠም በየአምባቸው ተንቀሳቀሱ። የንጉሡ ጦር በወገራና በሰሜን አውራጃዎች «የእስላሞችንና[110] የፈላሾችን እህልና እንስሳት» በመዝረፍ ጦርነቱን ጀመረ። ካሌፍ በበኩሉ የጠላቱን እንቅስቃሴና የወረራ እርምጃ ለማሰናከል የአገሩን መንገዶች ማፍረስ፥ ቤቶችና የእህል ማሳዎች በቅድሚያ ማቃጠል ጀመረ። ቀጥሎም ካሌፍና ጦሩ ከአምባ ምሽጋቸው ሆነው ከሦስት አቅጣጫዎች አምባውን ለመያዝ የመጣ

[109] Ibid., p. 103.

[110] Ibid., p. 97.

ውን የንጉሡን ሠራዊት በመርግ ናዳ ገጠሙት። በንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሐፊ በወልደ ሃይማኖት እንደ ተገለጸው «በሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች መካከል መሻገር የማይቻል አንድ ትልቅ ገደል አለ። በዚህ ጊዜ በንጉሡ ሠራዊትና በፈላሻው ጦር መካከል ጠንካራ ውጊያ ተጀመረ። የካሌፍ ሠራዊት ከተራራው አምባ ላይ ሆኖ የንጉሡ ጦር ከታች ወደ አምባው እንዳይወጣ በመርግ ናዳ ከለከለ።»[111]

በዚህ ሁኔታና ጊዜ ንጉሡ የካሌፍን አምባ እንዲደበድቡ የቱርክ መድፈኞቹን አዘዘ። በዚህ «በድንገተኛ የመድፍ ቱኩስ ካሌፍ ታወከ። ወታደሮቹም ታወኩ። በሙሉ ተበተኑ። በላያቸው ላይ ከሰማይ መብረቅ የወረደባቸው መሰላቸው። የንጉሡ ወታደሮች ከፊትና ከኋላ ከግራና ከቀኝ ሸምቀው የመውጫ መንገዶችን ስለዘጉባቸው ካሌፍና የጦር አለቆቹ ቢታላቅ ጭንቅ አምልጠው ወደ አንድ ከፍተኛ የገደል ጫፍ ላይ ወጡ። ከካሌፍ ወታደሮች ግማሾቹ በንጉሡ ወታደሮች ተገደሉ። ብዙዎቹ ከመማረክ በገደል ወድቀው አለቁ። በእግር የሚሄዱ ሁሉ እንዲገደሉ መነኩሴው አባ ንዋይ በግዝት አዝዞ ስለነበር በካሌፍ አምባ ጦርነት የንጉሡ ወታደሮች የስሜን/ፈላሽ ሰውንና እንስሳትን በሙሉ ገደሉ»[112] በጦርነቱ የተሸነፉ ሰሜን/ፈላሾች በበኩላቸው በክርስቲያን ጠላቶቻቸው እጅ ከመማረክ በገደል ይውድቁ እንደነበር፥ በአንድ የክርስቲያን ወታደር የተማረከች እስረኛ ሴት ወታደሩን ይዛ ገደል እንደገባችና ብዙዎቹም በጠላት ከመማረክ እርስ በርሳቸው በስለት ተራርደው እንዳለቁ ጸሐፊው ወልደ ሃይማኖት ጨምሮ ገልጿል።[113]

*የ1580 የረድኤት አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት*

ከታሪክና ከጊዜ አኳያ አጼ ሠርፀድንግል በጥቅምት 1580 የካሌፍን አምባ ምሽግ በነፍጥና በመድፍ መሣሪያዎች በደመሰሰው ጊዜ የሰሜን/ፈላሻ የተራራና የመርግ ያገር መከላከያ ሥርዓት ብሎም የአገሩ ፖለቲካዊ ህልውና ወደ ፍፃሜው ዋዜማ ደረሰ። በዚህ ረገድና ተግባር፥ መድፈኛው አጼ ሠርፀ ድንግል ከኅዳር 20 ቀን እስከ ታህሣሥ 4 ቀን 1580 ድረስ መካሻ በተሰኘ ወንዝ አጠገብ የረድኤትን የአምባ ምሽግ በሁለት ሣምንታት የነፍጥና የመድፍ ከበባና ድብደባ ሰበረ። በጥንታዊ የመርግ፥ የጋሻ፥ የቀስትና የጎራዴ መሣሪያዎች በሚከለከሉ የሰሜን/ፈላሻ አምባ ምሽጎች ላይ በዘመናዊ የቱርክ ነፍጥና መድፍ መሣሪያዎች ታጥቆ የመጣበትን ያገር ጠላት

111 Ibid.,

112 Ibid., p. 101.

113 Ibid.,





መመከት እንደማይችል ከወንድሙ ካሌፍ ሽንፈት የተረዳው ረድኤት በመነኩሴው አባ ንዋይ አማካይነት ከአጼ ሠርፀድንግል ጋር በእሪትና በወንጌል ቃለ መሃላ በሰላም ስምምነት ተደራድሮና «በራሱ ላይ አመድ ነስንሶ» ማለትም ሽንፈቱን በመሃላ ቃል ተቀብሎና ምህረት ጠይቆ በታኅሣሥ 6 ቀን 1580 ለንጉሡ እጁን ሰጠ።

*የ1587 የጉሽን ወርቅ አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት*

በ1587 ጉሽንና ጌዴዎን በተሰኙ ያገር መሪዎች ጥምር አመራር በሰሜንና በወገራ አውራጃዎች በታላቁ የወርቅ አምባ ምሽግ አንድ ሌላ የሰሜን/ፈላሻ አመፅና ጦርነት ተቀሰቀሰ።[114] የወርቅ አምባ ምሽግን ከጉሽን-ጌዴዎን አማፅያን ለማስለቀቅ አጼ ሠርፀ ድንግል ከትግሬ፥ ከአማራ፥ ከአገው፥ ከኦሮሞና ከቱርክ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች የተገነባ አንድ ግዙፍ የጦር ሠራዊት በስመ ጥር አዛዦች ደሀርጎት፥ ዮናኤል፥ እቁበ ሚካኤል፥ አባ ንዋይና በሌሎችም አዝማችነት በአራት ግምባሮች ከፍሎ አምባውን አስከበበ። በከበባው መጀመሪያ በ1578 የቱርኮች ወረራ ጊዜ ታላቅ የጀብድ ሥራ የሠራ አርበኛው እቁበ ሚካኤል ከነጦሩ በተሰማራበት በሸህና ግምባር በጉሽን አማፅያን በመገደሉ ንጉሡ በኃይል ተናዶ በተጠቀሰው አምባ የሚኖሩ ሰሜን/ ፈላሾች ከአምባው አጠገብ ካለው ምንጭ ውሃ እንዳያገኙ ምንጩን በሀይለኛ የኦሮሞ ወታደሮች አስጠበቀ። የሸህና አምባ ነዋሪዎች በውሃ ጥም ተሸንፈው በአጭር ጊዜ ውስጥ የንጉሡን ምህረት ጠይቀው እጃቸውን ሰጡ። ነገር ግን ምርኮኞቹ በምሕረት ከገቡ በኋላ ለማምለጥ ሲሞክሩ ተይዘው በሙሉ ተገደሉ።

ጉሽንና ጌዴዎን ከነጦራቸውና ከተከታዮቻቸው ጋር የመሸጉበት የወርቅ አምባ በጣም ረጅምና አስቸጋሪ ሥፍራ በመሆኑ የንጉሡ ነፍጠኞችና መድፈኞች በቀጥተኛ ተኩስ መስበር ስለአቃታቸው ንጉሡ ማታ በጨለማ በመጫኛ መሰላል ወደ ተራራው ወጥተው የሚሰብሩ የአገውና የቱርክ ምንደኞችን በቅጥር አሰማራቸው። በዚሁ መሠረትና ተግባር ንፍታሌምና ገብረ ኢየሱስ የተባሉ ሁለት አገዎች በታላቅ ችግር ወደ ወርቅ አምባ አናት ላይ ወጥተው ጠባቂውን ገደሉት። ከዚያም የንጉሡ ጨዋዎች (ወታደሮች) ከቱርክ ምንደኞች ጋር ወደ አምባው አናት ላይ ወጥተው በድንገት ጦርነት ከፈቱ። በአምባው ቤቶችና የእህል ማሳዎች ላይም እሳት ለኮሱ። በዚህ ሁኔታና ጊዜ ጉሽን በ60 ከሚቆጠሩ ተከታዮቹ ጋር በአምባው ገደል ወድቆ ሞተ። ጌዴዎን ግን ከ15 ጦርና ጋሻ ከያዙ ተከታዮች ጋር በጨለማ ሸፋን

114 Ibid., p. 115-123.

ከአምባው ወርዶና ከታች ዙሪያውን በከበቡ የንጉሡ ወታደሮች ሳይታይ ለጊዜው አመለጠ። ነገር ግን በኋላ ሲሸሹ በንጉሡ ጦር በተከበቡ ጊዜ ጌዴዎንና ተከታዮቹ በጠላት እጅ ከመግረክ እርስ በርሳቸው በስለት ተራርደው[115] ሞቱ። በተጨማሪም፣ ከ300 ዓመታት በኋላ በ1868 የዚህ ኩሩና ቆራጥ የሰሜን/ፈላሻ ወገን ተወላጅ የቋራው ካሳ ቴዎድሮስ በታላቁ የመቅደላ ጦር ሜዳ እንደሚያደርገው የአርበኛው ጉሽን እናትና ሚስት ባገር ጠላት እጅ ከመውደቅ ራሳቸውን በስለት ገደሉ።[116]

አጼ ሠርጸ ድንግልና ጠፊኛው መነኩሴ አባ ንዋይ ከ1580 እስከ 1587 የሰሜን/ፈላሻን የአምባ ሕዝብና መንግሥት በነፍጥና በመድፍ ካስገበሩ በኋላ በሦስቱ የካሌፍ፣ የረድኤትና የጉሽን አምባዎች ላይ አብያተ-ክርስቲያናት መሠረቱ። በመጨረሻ በ1594 አጼ ሠርፀድንግል ከደምቢያ በስተምዕራብ የሚገኘውን የሰሜን/ፈላሻ የቋራ ጠረፍ አገር አስገበረ።[117] ይሁን እንጂ ከዚህ በታች እንደሚታየው፣ «የስጉት አምባው» ጌዴዎን ወይም ዳግማዊ ጌዴዎን ከ1590 አካባቢ ጀምሮ እስከ 1624 ድረስ በአራቱ የጎንደር አጼ ነገሥታት ሠርፀ ድንግል፣ ያዕቆብ፣ ዘድንግልና ሱስንዮስ ላይ ታላቁንና የመጨረሻውን የሰሜን/ፈላሻ አመፅ ለሦስት አሥርታት ያካሄዳል።[118]

### *የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት ውድቀት*

### *የ1603-1632 የሃይማኖት ጦርነት*

### *የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ተግባር በኢትዮጵያ*

በ1597 አጼ ሠርፀድንግል በሩቅ ምዕራብ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝና በእናርያ መካከል በሚገኘው የዳሞት አገር በፍለሳ ጦርነት በሚንቀሳቀሰው የሜጫ ኦሮሞ ጎሳ ላይ የቅጣትና የዘረፋ ዘመቻ እያካሄደ እያለ መርዛማ ዓሣ በልቶ በድንገት ሲሞት በቤተ መንግሥቱ በሰባት ዓመት ልጁ ያዕቆብ፣ በወንድሙ ጎልማሳ ልጅ ዘድንግል ልሳነክርስቶስና በአጎቱ ልጅ ሱስንዮስ ፋሲል መካከል ከ1597 እስከ 1607 ድረስ ለአሥር ዓመታት የሚቆይ ረጅም የሥልጣን ጦርነት ተቀሰቀሰ።

የጦርነቱና የዘመኑ እንቅስቃሽ የውስጥና የውጭ መሪ

[115] Hess, "Falasha History", p. 116.
[116] Conti Rossini, Sarsa Dengel, p. 123.
[117] Hess, 'Falasha History", p. 116,
[118] ተክለ ሥላሴ (ጸሐፊ ትዕዛዝ)፣ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ 1605-1632 ያልታተመ ዘና መዋዕል፣ በብሄራዊ ቤተ መጽሐፍት፣ አዲስ አበባ) ም. 43፣ 73።





ተዋንያን[119] (1) በሦስቱ ታላላቅ የጦር አበጋዞች ራስ አጥናቴዎስ፣ ራስ ክፍለዋህድና ራስ ዘሥላሴ የሚመሩ የሟቹ የአጼ ሠርፀድንግል ቁርባን፣ አቴትዝር፣ ጨረቃ፣ ጊዮርጊስ ኃይሌ፣ ቁርከ፣ ነፍጥ (ናራ)፣ አፍሮአይገባ፣ ኮከብ የተባሉ ኃይለኛ የጦር ድርጅቶችና ሹማምንቶች፣ (2) «እሥራኤላውያን» ተብለው የሚጠሩና በግሸን አምባ ግዞት የሚኖሩ የአማራ መሳፍንት፣ (3) በሰሜን ኢትዮጵያ የአማራ፣ የሰሜን/ፈላሻ፣ የአገውና የትግሬ ደጋአምባ አገሮችንና ሕዝቦችን ለመያዝ ወይም አልፎ ለመሄድ በፍለሳና በሰፈራ እንቅስቃሴ ከምስራቅ፣ ከደቡብና ከምዕራብ ኢትዮጵያ የዘወትር ጦርነት የሚካሄዱ የከረዩ፣ የወሎ፣ የቱለማና የሜጫ ኦሮሞ ጎሳዎች፣ (4) ኢየሱሳውያን የተባሉ የእስፓኝ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን፣ (5) በዳግማዊ «ጌዴዎን» ማለትም «በስጉት አምባው ጌዴዎን» መሪነት በግሸን አምባ ላይ «እሥራኤላውያን» የተሰኙ የአማራ መሳፍንትን ከጎናቸው አሰልፈው አዲሱን የጎንደር መንግሥት ለማጥፋት የሚዋጉ ሰሜን/ፈላሾች ነበሩ።

በዚህ ረገድና ተግባር በ1597 አጼ ሠርፀድንግል እንደሞተ በሟቹ ንጉሥ አማች በራስ አጥናቴዎስ የሚመራውና አገሩን የሚገዛው የሶስት ራሶች ጁንታ ከሦስቱ የዘውድ ባላንጣ ልዑላን ጎልማሳ ዘድንግልን አስሮ በራሱ ቁጥጥር ሥር ሕፃን ያዕቆብን አነገሠ። ሱስንዮስ ግን የነገሥታትን ሹም ሽር ከሚያደርገው የራሶች ጁንታ እጅ በሽሽት አምልጦ ወደ አጎራባቹ የኦሮሞ ወዳጆቹ ሄደ።

ከዚህ አኳያ የአጼ ልብነድንግል የልጅ ልጅ ሱስንዮስ ፋሲል በ1565 ገደማ ተወለደ። በ1580 አካባቢ በምርኮ ተወስዶ አንድ ቦኩ ለተባለ የቦረና ኦሮሞ የጉዲፈቻ ልጅ ተደረገ። በምርኮ ዘመኑ ሱስንዮስ የኦሮሞን ቋንቋ፣ የገዳን ሥርዓት፣ የሉባን የጦር ድርጅትና ሥልት አጠናቅቆ አወቀ። እንዲሁም በ1586 ገደማ በኦሮሞና በአማራ ምርኮኞች ልውውጥ ወደ ሠርፀድንግል ቤተ መንግሥት ከተመለሰ[120] በኋላ ሱስንዮስ የመንግሥትና የቤተ መንግሥት ወግ፣ አሠራርና ሥርዓት ጨምሮ ተማረ።

ከላይ እንደተመለከተው፣ በ1597 አጼ ሠርፀድንግል ሲሞት ባልጋወራሾቹና በጦር አበጋዞቹ መካከል የሥልጣንና የእርስ በርስ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ራስ ዘሥላሴ፣ ራስ አትናቴዎስ፣ ራስ ክፍለዋህድ፣ ዮልዮስ፣ ዮናኤል፣ ክፍሉም፣ ተክለ ጊዮርጊስ፣ ሠርፀ ክርስቶስ ...የተባሉ የዘመኑና የሥርዓቱ ከፍተኛ የጦር አበጋዞችና አገረገዥዎች

[119] ተክለ ሥላሴ፣ ሱስንዮስ ታሪክ ይህ በ98 ምዕራፍ በተክለ ሥላሴ የተጻፈው ታላቅ መጽሐፍ ሁለተኛው አስፈላጊና ዋናው የዘመኑ ታሪክ ምንጭ ነው።
[120] Bahrey, History of The Galla, p. 121.

ከላይ የተጠቀሱ የጦር ድርጅቶችን ይዘው ከ1597 እስከ 1607 ድረስ በአንድ አሥርት ዘመን ውስጥ በዙፋን ላይ ሦስቱን የጎንደር አጼ ነገሥታት ያዕቆብን ዘድንግልንና ሱስንዮስን ሹም ሽር አደረጉ።[121]

በዚህ ወቅት ከ1597 እስከ 1603 ድረስ ገዥው የራሶች ጁንታ ሕፃን ያዕቆብን አነገሠ። ከ1603 እስከ 1604 ድረስ ደግሞ ያዕቆብን ሻረና ጎልማሳ ዘድንግልን ከግዞቱ አምጥቶ አነገሠ። በ1605-1607 ዘድንግልን ሽሮና ገድሎ ያዕቆብን ለሁለተኛ ጊዜ አነገሠ። በዚሁ ዓመት የጦር አበጋዞቹ አሊቃ ራስ አትናቴዎስ የኦሮሞ ወታደሮችንና ተከታዮችን ይዞ በሽፍትነት የሚኖረውን ሱስንዮስን በራሱ ውሳኔ አነገሠ። በመሆኑ ከ1605 እስከ 1607 ድረስ አጼ ያዕቆብና አጼ ሱስንዮስ በአንድ ጊዜ በአንድ የኢትዮጵያ አገርና ሕዝብ ላይ ሁለት ባላንጣ አጼዎች ሆኑ።

በመጨረሻ በመጋቢት 10 ቀን 1607 በጎጃም ክፍለ ሀገር ደብረዘይት በተሰኝ ሥፍራ ጎል በተባለ ተራራ ሥር በተካሄደ ጦርነት አጼ ሱስንዮስ 400 የኦሮሞ ወታደሮቹን ይዞ የአጼ ያዕቆብን ግዙፍ ሠራዊት ደመሰሰ። በጦርነቱ ሁለቱም አጼ ያዕቆብና ግብፃዊው አቡነ ጴጥሮስ ተገደሉ። በመሆኑም አጼ ሱስንዮስ የጎንደር መንግሥት ብቸኛው መሪና አዛዥ ሆነ።

በዘመኑ በጎንደር መንግሥት የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርት እና ተግባር በሚመለከት፣ በ17ኛው ምዕተ ዓመት በመጀመሪያ ሦስት አሥርታት ውስጥ የእስፓኝ ኢየሱሳውያንን ዘመናዊ ትምህርት፣ የሙያ ጥበብ፣ አዲስ የቤት፣ የከተማ፣ የመንገድና የድልድይ ሥራዎችን በማየት የኢትዮጵያ ሦስቱ ነገሥታት ያዕቆብ፣ ዘድንግልና ሱስንዮስ በየበኩላቸውና በየዘመናቸው በባላንጣዎቻቸው ላይ ዘውዳዊ ሥልጣናቸውን የበለጠ ለማጠናከር በሚሲዮናውያኑ አማካይነት ከአውሮፓ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ፣ የዕደጥበብ ሙያ፣ የዕድገትና የለውጥ ሀሳቦችን ፈላጊዎች መስለው ቀረቡ።

በሌላ በኩል ማዕከላዊ ጠንካራ የዘውድ ሥርዓት በእነርሱ ላይ አፍራሽ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተፅእኖ የሚያስከትል ኃይል እንደ ሚሆን በመገመት የጦርና የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ጴጥሮስና ስምኦን በተባሉ ግብፃውያን አቡኖች መሪነት የተጠቀሰውን የሚሲዮን ትምህርት "የጸረማርያሞች" ሃይማኖት ነው በሚል ሰበብ በነገሥታቱ ላይ የገበሬዎችን፣ የቄሶችንና የወታደሮችን አጠቃላይ አመፅ ቀሰቀሱ።

በዚህ ሁኔታና ተግባር ከ1603 እስከ 1622 ድረስ በኢትዮጵያና በአካባቢው አገሮች የግዕዝ፣ የአማርኛ፣ የአረብኛና የቱርክ ቋንቋዎችን በሚናገር በሙያው አስተማሪ፣ ሰባኪ፣ ግምበኛና አናጢ በሆነ

[121] ተክለ ሥላሴ፣ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 1-21።





በአንድ አዋቂ ሚሲዮናዊ ቄስ ፔትሮ ፖያዝ (1564-1622) መሪነት የእስፓኝ ኢየሱሳውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ለሦስቱ አጼ ነገሥታት ያዕቆብ (1603)፣ ዘድንግል (1604) እና ሱስንዮን (1605-1632) ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ገብታችሁ ለሮማው ፖፖና ለእስፓኝ ንጉሥ ታዛዥ ተከታዮች ብትሆኑ በአገራችሁ የሥልጣንና የግዛት ጠላት የሆኑ የአካባቢ ጦር አበጋዞችንና የኦሮሞ ሰፋሪዎችን ለማስገበርና ለመግዛት ከእስፓኝ መንግሥት ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን እርዳታ ለማግኘት ትችላላችሁ ብለው ስለደለሉዋቸው ሦስቱም የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታይ ነገሥታት ከላይ እንደተጠቀሰው ወደ ሮማው ካቶሊክ ሃይማኖት ተለወጡ።[122]

በመጨረሻ በእስፓኝ ኢየሱሳውያን ትምህርትና ግፊት፣ አጼ ሱስንዮስ ሁለቱንም የሰሜን/ፈላሻ ኦሪትና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖቶችን በአዋጅ ሰረዛቸው።[123] ሥርዓተ ሰንበትንም ሻረው። በዚህ ተግባሩም አጼ ሱስንዮስ በአንድ በኩል የሰሜን/ፈላሻ መንግሥትን ደመሰሰ። በሌላ በኩል ደግሞ በራሱና በመንግሥቱም ላይ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ገበሬዎችንና ቄሶችን የ1616-1632 የአመፅ ጦርነት ቀሰቀሰ።[124]

### *የ1609-1624 የዳግማዊ ጌዴዎን አመፅና የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት ፍፃሜ*

በ17ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አሥርታት የኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥት፣ ሃይማኖትና ጦር መሪዎች ከነተከታዮቻቸው በሥልጣን፣ በሃይማኖትና በእርስ በርስ ጦርነቶች በሚገዳደሉበት ዘመን አጎራባቹ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት በስጉት አምባው ዳግማዊ ጌዴዎን መሪነት በተጠቀሱ የክርስቲያን ኃይሎች ላይ ገና የራሱን የነፃነት ትግል በማካሄድ ላይ ነበር።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ የአጼ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ተክለ ሥላሴ በዝርዝር እንደዘገበው፣[125] ከ1587 የወርቅ አምባ ጦርነት በኋላ፣ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት በስጉት አምባው ዳግማዊ ጌዴዎን መሪነት፣ በ1594-1624 በአራቱ የጎንደር ነገሥታት ሠርፀ ድንግል፣ ያዕቅብ፣ ዘድንግልና ሱስንዮስ ላይ በሰሜን፣ በወገራ፣ በፀለምት፣ በአበርገሌና በበጌምድር ቆላዎችና አምባዎች የመጨረሻ

[122] Getahun Delibo, "Early Portuguese Imperialism in Ethiopia, 1490-1632: Origins, Responses, and Consequences", MA. Thesis (Howard University, 1971).
[123] ተክለ ሥላሴ፣ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 44 ቁ. 62።
[124] ተክለ ሥላሴ፣ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 62-98።
[125] ተክለ ሥላሴ፣ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 33፣ 43፣ 68-73።

አመፅ ጦርነት ሲካሄድ ኖረ። በዚህ የነፃነት ጦርነት ሂደት ዳግማዊ ጌዴዎን በ1609፥ በ1613-1623 እና በ1623-1624 በአጼ ሱስንዮስ መንግሥትና ጦር ላይ በተከታታይ ተከላይ (አምዶ)፥ ከፍለማርያምና የአርዘ ልጅ የተባሉ የዘውድ ባላንጣ «እሥራኤላውያን» የአመፅ ኃይሎችንና እንቅስቃሴዎችን በማደራጀትና በመምራት፥ በ1624 እስኪገደል ድረስ፥ ለአዲሱ የጎንደር መንግሥትና ነገሥታት ታላቅ የሰላምና የፀጥታ ችግር እንደፈጠረ በተጠቀሰው ዜና መዋዕል በሥፍራና በጊዜ ተገልጿል።

በመሆኑም በ1616 አጼ ሱስንዮስ ቀደም ብሎ በሰሜን/ፈላሻ አገር ላይ የሾማቸው አገረ ገዥዎችና የጦር አበጋዞች በጣና ሐይቅና በተከዜ ወንዝ መካከል በየክፍለ ግዛታቸው የሚኖሩ ፈላሻዎችን የጾታ፥ የዕድሜና የሙያ ምርጫና ልዩነት ሳያደርጉ በሙሉ እንዲገድሏቸው አዘዘ። ራሱም ንጉሡ የፈላሻ ሴቶችንና ልጆችን ባሮቹ አደረጋቸው። ለወደደውም ሰጣቸው። እንዲሁም ንጉሡ በደምቢያ በነገሠበት አገር የሚኖሩ ፈላሾች ወደ ክርስትና እንዲገቡ ወይም በሙሉ እንዲገደሉ አዘዘ። የአይሁድን የኦሪት ሃይማኖት ለመካዳቸው ማስረጃ እንዲሆን በቅዳሚት ሰንበት ቀን ሥራ እንዲሠሩበት፥ እንዲያርሱበት በአዋጅ አስገደዳቸው። ፈላሾቹም ከገፀምድር በሞት ከመጥፋት ይልቅ በንጉሡ ሕግ መሠረት በክርስትና መጠመቅ ጀመሩ።[126]

*የጦርነቱ ታሪካዊ መነሻና ውጤት*

አጼ ሱስንዮስ ኢየሱሳውያን በተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ግፊት በ1616 የሰሜን/ፈላሻ ጥንታዊ መንግሥትና የኦሪት ሃይማኖት ከደመሰሰ በኋላ በተጨማሪ በ1620-1622 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የቅዳሚት ሰንበት ከረቡዕና ከአርብ ጾም ጋር በአዋጅ ሽሮ ራሱም በመጋቢት 1622 በይፋ ካቶሊክ ሆነ። የሽረት አዋጁንም በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ በኃይል ተግባራዊ ያደርግ ዘንድ ካቶሊክ ወንድሙን ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስን ከ7000 ወታደሮች ጋር ወደ ዳሞት ክፍለ ሀገር ላከ። ሕዝቡም ሕጉን በትጥቅ አመፅ በመቃወሙ በኦሪት ሃይማኖት ጥያቄ በኢትዮጵያ ክርስቲያን ሕዝብና መንግሥት መካከል የመጀመሪያው የሃይማኖት ጦርነት ተቀሰቀሰ።

የዘመኑን የሕዝብ እምነትና አመለካከት የአመፁንም ዓይነትና ስፋት የጦርነቱንም ሥልትና ውጤት በግልፅ የሚያሳይ አንድ ልዩ ታሪካዊ ሰነድ ስለሆነ የ1621 የዳሞት ጦርነት ዘገባ በጸሐፊ ትእዛዝ

[126] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 44።





ተክለ ሥላሴ እንደበት እንደሚከተለው ቀርቧል።

*የአይሁድን ሰንበት ከረቡዕና ከዓርብ ጾም ጋር የሚሽር ሕግ አውጥቶ ሕጉንም እንዲያስፈጽም ራስ ሥዕለክርስቶስን ወደ ዳሞት ላከ። ራስ ሥዕለክርስቶስም ንጉሡ በአይሁድ ሰንበት ቀን ሥራ እንዲሠራበት ሕግ ማውጣቱን ለዳሞት ሰዎች ነገራቸው። የዳሞት ሰዎች ግን አዋጁን ሰምተው የአይሁድ ሰንበት አይሻርም አሉ። ማን ሰው ነው ደፍሮ የሚሽረው በማለት ተቃወሙ። የድፍረት ቃልም ጨምረው አሰሙ። ራስ ሥዕለክርስቶስ በበኩሉ ለንጉሡ ሕግ ይታዘዙ ዘንድ አንድ የመልእክተኞች ቡድን ቢልክባቸውም እነርሱ ግን በድፍረት ተነሳስተው በሰልፍ ወደ በርበሬ ዛፍና በረንዝ ወጡ። በተጨማሪም የደልጋ፥ የሰና፥ የአርበዝና የጎጃም ሰዎች ጊዮርጊስ ኃይሌ ከተባሉ ጨዋዎች ጋር በንጉሡ ጦር ላይ ከዳሞት ሕዝብ ጎን ተሰለፉ። ከራስ ሥዕለ ክርስቶስ ሎሌዎችም ግማሾቹ ከዳሞት ሰዎች ወገን ሆኑ። የኪዳና የሕማማ ጥፍሮች ብቻ አልደገፉአቸውም። ሽማግሌዎች ሳይቀሩ ከራስ ሥዕለክርስቶስ ሠፈር ይልቅ በሕዝቡ ወገን በበረንዝ ተሰለፉ። ራስ ሥዕለክርስቶስ ሐመዳሚት በተባለው ቦታ ከሰፈረበት ለዳሞት ሰዎች «ለንጉሡ ሕግ ታዘዙ፥ የአይሁድን ሰንበት ሻሩ»፥ ብሎ አሁንም መልዕክተኞች ላከባቸው።*

*እነርሱም ለራስ ሥዕለክርስቶስ በሰጡት መልስ፥ ንጉሡ በእውነትም የአይሁድን ሰንበት ሻሩ ብሎ ማዘዙን ራሳችን ሄደን እንጠይቀው ዘንድ አንተ ግን መንገዱን ልቀቅልን ብለው ጠየቁት።*

*እሱም ይህን ብሎ ከሐመዳሚት ተነሳ። በኤዳውሬ ሰፈረ። ከኤዳውሬ ተነስቶ በእንዝግደም ሰፈረ። ከዚያም አዛዥ አመሃን፥ አዛዥ ምርጫን፥ የጸሐፊ ላም ሠርጸን ልጅ ገብረ ክርስቶስንና ወፍር አጽቆን ከሁለት የንጉሡ ሎሌዎችና አዳምና ወርጡ ከተባሉ ሁለት የየሀብታ ሰዎች ጋር ላከባቸው። በላከው መልእክት በቁስ እያተገዘታችሁ እኔን ለመግደል የምትተባበሩ ምን ስለ አደረኩአችሁ ነው። ተዉ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ። በንጉሡ ሕግ መሠረትም የአይሁድን ሰንበት ሻሩ። እኔንም ስለ በደላችሁኝ ካሣ ስጡኝ። ከእናንተ ጋር ያሉ ሎሌዎቼንም መልሱልኝ። እምቢ ብትሉ ግን ሰማይ ይሰማችሁ። ምድርም ታድምጣችሁ። እግዚአብሔር ይፍረድ። ሴት ልጅ ሳይለዩ በጭካኔ የሚገድሉ የየሀብታና የወረንጨሻ ሰዎች እንዳያገኙአችሁ። ተጠንቀቁ። በእኔና በእናንተ መካከል በተፈጠረው ጠብ ምክንያት ለሚፈሰው ደም ተጠያቂዎች እናንተ ናችሁ አለ።*

*የዳሞት ወታደሮች ግን ይህንን ከመልእክተኞች ሰምተው የበለጠ ለጦርነት ተነሳሱ። የተከታዮቻቸውን ብዛት፥ አንድነትና ጥንካሬ በማየት በሠፈራቸው ጸኑ ትምክህት አበዙ። ለራስ ሥዕለክርስቶስ በሰጡት መልስ የቅዳሚት ሰንበት እናከብራለን አንሽርም። ከእኛ ዘንድ የተማጸኑ ሎሌዎችንም አሳልፈን አንሰጥም ለአንተም በእኛ ላይ ምንም ካሣ የለብንም አሉ።*

*ራስ ሥዕለክርስቶስም ይህንን የድፍረት ቃል ከምልእክተኞቹ አፍ ሰምቶ ከእንዝግደም ተነሳ። በአረፋ የሚኖሩትን የዳሞት ሰዎች ወጋ። ላሞቻቸውንም በምርኮ ወሰደ። ቤቶቻቸውንም አቃጠለ። መነኩሳት ጭምር ከአመጸኞች ጋር ከተባበሩ*

ሰዎች ብዙዎቹ ተገደሉ። የአረፋን ሰዎች ከወጋ በኋላ ራስ ሥዕለክርስቶስ በየሰንበት ገበያ ሰፈረ።

በማግስቱ ሰኞ ሰዎን በከንቱ ትጠሉኛላችሁ። ከድተው ወደ እናንተ የሄዱ ሉሌዎቼን ላኩልኝ። ስለ በደላችሁኝ ካሉኝ። በንጉሡ አዋጅ መሠረት የአይሁድን ሰንበት ሻሩ በማለት ወደ ዳሞት ሰዎች በፊት የላከባቸውን አስታራቂዎች እንደገና መልሶ ላከባቸው። መልእክተኞቹም የዳሞት ሰዎች ተሰልፈው በሚገኙበት ሥፍራ ሄደው ነገሩአቸው። ሰዎቹም የራስ ሥዕለክርስቶስን መልእክት እንደገና ሰምተው እርሱ እርቅና ሰላም ከፈለገ ሰንበትን የሚሽረውን ሕግ ያንሳ። አባቶቻችንና እኛም ለብዙ ዘመናት ስናከብረው የኖረውን ሰንበት አንሽርም። ከእኛ ዘንድ የተማጸኑ ሉሌዎችንም አሳልፈን አንሰጠውም የሚል መልስ ሰጡ።

ራስ ሥዕለክርስቶስና አማካሪዎቹ ይህን መልስ ሰምተው የጦርነት ነገር ሲመክሩ አደሩ። በማግስቱ ማክሰኞ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ በማለዳ ተነሳ። ጭፍሮቹንም በየሥፍራቸው አሰለፉ። ለጦርነት ምቹ የሆነ ስፍራ ያዘ። የዳሞት ወታደሮች ከብዙ የጎጃም ሠራዊት ጋር በሁለት የእግረኛና በአንድ የፈረሰኛ ግምባሮች ማለትም በሶስት ክፍሎች ተሰለፉ። የራስ ሥዕለ ክርስቶስ ሠራዊት የሚያልፍበትን መንገድ ዘጉ። ራስ ሥዕለ ክርስቶስ በቀስትና በነፍጥ ለመዋጋት የሚያመች ቦታ ይዞ በማግሥቱ ውጊያ ለማድረግ በጠላት ግምባር ፊታውራሪ ጭፍራ አስቀመጠ። ነገር ግን የዳሞት ጦር ቀድሞ ውጊያውን ጀመረ።

ውጊያውን በጀመሩ ጊዜ ራስ ሥዕለክርስቶስ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ፊት በጉልበቱ ተንበርክኮ ሰገደ። ጌታዬ ሆይ በወንጌል እንደተጻፈው አንተን በእውነተኛ መንገድ በትክክል የማላምንህ ከሆነ ሰውነቴን ለእነዚህ ጠላቶቼ ስጥ። በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት አንተን በትክክል በእውነተኛ መንገድ የማመልክህ ከሆነ ግን በከንቱ የሚጠሉኝን እነዚህን ወንጀለኞች ስጠኝ አለ።

እንዲሁም በውሸት እንደሚጠረጥሩኝ ልጅሽን በእውነት የማላመልከው ከሆነ ለእነዚህ ጠላቶቼ ራሴን ስጭአቸው። በእውነት የማልወድሽ ከሆነ ልጅሽንም በትክክል የማላመልከው ከሆነ ሃይማኖቴም የቀና ካልሆነ ስለ ክብሬ ቀንተው ለሚጠሉኝ ለእነዚህ ጠላቶቼ ራሴን ስጭአቸው። ብሎ ወደ እመቤታችን ወደ እግዚኢትነግርያም ጸለየ።

እንደዚህ ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ በፈረሱ ላይ ወጣ። ከፈረሰኛው ጋር የጦሩን እኩሌታ በደጃዝማች ቡኮ መሪነት ወደ ፊት ላከ። እርሱም ሕናጭ ከሚባለው የምርጥ ወታደሮች ጭፍራ ጋር ወደ እግረኛው ጭፍራ ሄደ። ጠላቶቹ ከፊቱ አልቆሙም። ለራስ ሥዕለክርስቶስ ሠራዊት ጀርባቸውን ሰጡ። ብዙዎቹ ሞቱ። እንደደረቅ ቅጠል ረገፉ። በባሕር ላይ እንደረገፈ አንበጣ ረገፉ። የራስ ሥዕለክርስቶስ ሠራዊት እስከ ያገምና እስከ ደብረጊዮርጊስ እስከ ብር ወንዝና እስከ ዘንደአምባ ድረስ ገደላቸው። ላሞቻቸውንም ፈረሶቻቸውንም በምርኮ ወሰደ። በዚያን ቀን ከራስ ሥዕለክርስቶስ ሠራዊት የጋላና የአማራ ወታደሮች አሥር፥ አምስት፥ ሁለት ያልገደለ ያልሰለበ የፈረስና የላም ምርኮ ያልወሰደ አልነበረም።

ንጉሡም መሰለባቸውን ሰምቶ አዛዥ አሳኖን፥ አዛዥ ጢኖን፥ አዛዥ ሰንቡልን ያስታርቋቸው ዘንድ ላከ። እነርሱም ሄደው አስታረቁ። ያን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ሰገድ በራስ





ሥዕለክርስቶስ ከተማ በሉዶቅያ የተሰበሰቡ ሰዎችን ሌጺስ ቆጳሳትን እንዲያወግዙ አዘዘ። የቅዳሚት ሰንበትን ያልሻረ ሁሉ ገንዘቡ ይወረስ፥ ቤቱም ይበርበር ብሎ አዋጅ አስነገረ።[127]

በኢየሱሳውያን ዘገባ መሠረት በታላቁ የሰንበት ጦርነት በሕዝቡ ወገን የተሰለፉ 14,000 የአገሬው ሕዝብና 400 ቄሶች ሲሆኑ የመንግሥቱ ወታደሮች ብዛት ደግሞ 7,000 ነበር። በመንግሥቱ ጦር ከተገደሉት መካከል 118 መነኮሳት ነበሩ።[128]

በዚህ የሰንበት ጦርነት በአመፀኛው ሕዝብ ላይ ድል ከተጎናፀፈ በኋላ አጼ ሱስንዮስ በመጋቢት 1622 በቄስ ፔትሮ ፓየዝ እጅ በይፋ በካቶሊክ ሃይማኖት ተጠመቀ። በግንቦት 23 ቀን 1622 ቄስ ፔትሮ ፖየዝ ሞተ። በምትኩ በእስፓኝ ንጉሥና በሮማው ፓፓ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ተደርጎ የተላከው የእስፓኝ ተወላጅ አልፎንስ መንዴዝ ከአሥራ ዘጠኝ ተከታዮቹ ጋር በ1625 በቤይሉል በር ወደ ኢትዮጵያ ደረሰ።

በየካቲት 11 ቀን 1626፥ አጼ ሱስንዮስ አልጋወራሽ ፋሲለደስንና ወንድሞቹን ጨምሮ በጎርጎራ ቤተ መንግሥት የአገሩ ከፍተኛ የመንግሥትና የሃይማኖት ባለሥልጣኖች በተቀመጡበት ታሪካዊ ጉባኤ በፓትሪያርክ አልፎንስ መንዴዝ በኢትዮጵያ የሮማው ፓፓ እንደራሴ ፊት በጉልበቱ ተንበርክኮ በራሱ፥ በመንግሥቱና በሕዝቡ ስም የሮማ ፓፓውን መንፈሳዊ በላይነት በመቀበል የመሀላ ሥነ ሥርዓት ፈጸመ። ከንጉሡ ቀጥለው ልጁ ፋሲለደስ፥ ወንድሞቹ፥ የክፍለ ሀገር እንደራሴዎች፥ መኳንንቶች፥ ካህናትና መነኮሳት በሙሉ እንዲሁም የሮማ ፓፓውን ሃይማኖታዊ በላይነትና መንፈሳዊ አመራር በመቀበል የታማኝነት ቃል ገቡ።

በዚህ ወቅትና ሁኔታ አጼ ሱስንዮስ ከ330 ጀምሮ እስከ 1626 ድረስ ለ1290 ዓመታት የመንግሥቱ ሃይማኖት የነበረውን የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት በይፋ ሻረው። ፓትሪያርክ አልፎንስ መንዴዝ ቀጥሎ በግብፁ አቡን ይመራ የነበረውን የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ትምህርት፥ ጾምና በዓላት በሙሉ አገደ። ካህናትና መነኮሳትም በአዲሱ የካቶሊክ እምነትና ትምህርት መሠረት እንደገና እንዲጠመቁ ታዘዙ። በአገሩ የቀድሞ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሀብት በኢየሱሳውያን አስተዳዳሪነት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ እንዲሆን ተደረገ። በጎጃም፥ በደምቢያ፥ በበጌምድርና በትግራይ በ21 ኢየሱሳውያን ቄሶች መሪነት 13 የእምነት፥ የትምህርትና የሥራ ማዕከላት ተመሠረቱ።

---

[127] ተክለ ሥላሴ፥ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 63 ቁ. 273 275።

[128] Getahun Dilebo "The Portuguese in Ethiopia", p, 135.73

ከ1626 እስከ 1632 ድረስ በፓትርያርክ አልፎንሶ መንዴዝ ሥር ነቀል ፖሊሲና የተግባር እርምጃዎች ሥልጣናቸውንና የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን የተነጠቁ የኢትዮጵያ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ የክፍለ ሀገር እንደራሴዎች የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን በኢየሱሳውያን፣ በንጉሡና በራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስ ላይ በየአካባቢያቸው በአመፅ እንቅስቃሴ ተነሱ። በዚህ ታላቅ የመከራና የስቃይ ዘመን በንጉሡ፣ በራስ ቢትወደድ ወንድሙና በአልጋ ወራሽ ልጁ መካከል ብርቱ የሥልጣን ትግል ተፈጠረ። በተጨማሪም በየክፍለ ሀገሩ የንጉሡ እንደራሴዎችና የአካባቢው መሳፍንቶች በተለመደው የሥልጣን አመፅና ጦርነት ተነሱ። ባጭሩ በኢትዮጵያ ካቶሊኮችና ኦርቶዶክሶች መካከል ታላቅ የፖለቲካ ሽብርና የእርስ በርስ መገዳደል ዘመንና ሥርዓት ተጀመረ።

*የ1629-1632 የአገው አመፅና የኢትዮጵያ የካቶሊክ መንግሥት ውድቀት*

የመንግሥትን ወሳኝ ሥልጣን ከጦር ጋር በእጁ የያዘው የኢትዮጵያ የካቶሊክ ቤተ መንግሥትና ኢየሱሳውያን የተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን አንጃ በ1629-1632 በላስታ-ዋግ ተራሮች በአገው ጦረኛ መስፍን መልከአ ክርስቶስ የተመራውን ሁለአቀፍ የአካባቢ መሳፍንቶችን፣ የጦር አበጋዞችን፣ የቄሶችንና የገበሬዎችን ሕዝባዊና ብሔራዊ ፀረ-ካቶሊክ አመፅ መቆጣጠርና መግታት አቃታቸው። ይህ ጸሐፊ በሌላ ሥፍራና ሥራው በጥቅል እንዳስቀ መጠው፣[129]

> *በዚህ ሁኔታ በአንድ በኩል በቤተ መንግሥት በሱስንዮስ ወንድሞችና ልጆች መካከል ከፍተኛ የሥልጣን ትግል ተፈጠረ። በሌላ በኩል ደግሞ በዘመኑ አጠራር በጸሐፊ ትእዛዝ ተከለ ሥላሴ «ቦላድ» (ጅንጀሮ) ወይም ወምበዴ ተብሎ የሚጠራው መልከአ ክርስቶስ የአገው አመፅ መሪ ራሱን እንደንጉሥ በመቁጠር የባለሥልጣኖች ሹምሽር ማድረግ ጀመረ። ከንጉሡ በታች የካቶሊክ ሃይማኖትና የኢየሱሳውያን ዋናው ተከታይና ደጋፊ ስለነበር በጦረኛው ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስ ላይ ብዙ ተቃዋሚዎች ተነሱ። በተለይም በራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስና በአልጋ ወራሹ ፋሲለደስ መካከል ብርቱ የሥልጣን ትግል ተፈጠረ። አልጋወራሹ የአባቱ እንደራሴ ሆኖ ዘመቻ ሲመራ ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስ የአልጋወራሹን አመራር መቀበል እምቢ አለ። በመሆኑም ንጉሡ ራስ ቢትወደዱን ከነሹም ሹመት አወረደ። ሀብቱንና ጦሩን በከፊል ለአልጋወራሹ ፋሲለደስ ሰጠ። የአገው አመፅ ደግሞ በየጊዜው እየተጠናከረ ሄደ። በዚህ ሁኔታና ወቅት አዲሱን የካቶሊክ ሃይማኖት ሰርዞ ጥንታዊውን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መልሶ እንዲያድስ በንጉሡ ላይ ከአማካሪዎቹ፣*

[129] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ፣ ገጽ 232-234፣ 237።





> *ከባላሥልጣኖቹና ከጦሩ ግፊት እየበዛ ሄደ።*
>
> *በዚህ ሁኔታ በግንቦት 1632 ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስ ከ20,000 ወታደሮች ጋር ከባላዱ መልከአ ክርስቶስ ጋር በማበር ተጋጥሞ በሽንፈት ተመለሰ። ከዚያ በኋላ ንጉሡ በራሱ አመራር የኦሮሞ ወታደሮች አደራጅቶ ከደምቢያ ወደ ላስታ በመዝመት በሰኔ 2 ቀን 1632 በድንገት ከተራራው ወርዶ በሜዳ ላይ ውጊያ በገጠመው የመልከአ ክርስቶስ ጦር ላይ ብርቱ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ በመውሰድ 8,000 ሰዎችን ገደለ። ቢሆንም መልከአ ክርስቶስ ሸሽቶ በሕይወቱ አመለጠ።*

ከዚህ የመጨረሻ ድል በኋላ በሰኔ 25 ቀን 1632 አጼ ሱስንዮስ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በአዋጅ አድሶ ራሱ በመስከረም 7 ቀን 1632 በካቶሊክ ሃይማኖቱ እንደጸና በ61 ዓመቱ ሞተ። ነገር ግን ልጁና ተከታዩ አጼ ፋሲለደስ የካቶሊክ እምነቱን ክዶ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተመለሰ። ኢየሱሳውያንንም በ1633 ከአገር አስወጣ። ራስ ቢትወደድ ሥዕለክርስቶስን ጨምሮ ብዙ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ባለሥልጣኖችንና ምዕመናንን በሞት ቀጣቸው። በመጨረሻም አጼ ፋሲለደስ አውሮፓውያንና ሥልጣኔ አቸው ሁለተኛ ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ የመግቢያ በሩን እንዲዘጉ ባቸው በቀይ ባሕር ላይ ከእስላማዊ የቱርክ ባለሥልጣኖች ጋር ስምምነት አደረገ።

*የቤተ እሥራኤል/ፈላሻ ሥቃይና የስደት ፍጻሜ*

በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተከዜና በዓባይ ወንዞች መካከል በሚገኘው አገሩ ላይ በመሬቱ፣ በንብረቱ፣ በመብቱ ጥያቄ በ15ኛው ምዕተ ዓመት ከአጼ ይስሐቅ (1414-29) ጋር ከተዋጋ ወዲህ ከፖለቲካና ከመሬት ጠላቶቹ «ፈላሻ» ማለትም ስደተኛ፣ መጤ፣ ባዕድ፣ የሚል ስም የተሰጠውና ከጊዜ በኋላ እርሱ ራሱን «አይሁድ» እና «ቤተ እሥራኤል» ነኝ ብሎ በሁለት ተለዋጭ የይሁዳውያን ስሞች መጠራት የጀመረው፣ ነገር ግን በአካባቢው በጥንቱ ዘመን ገና የክርስትና ሃይማኖት በ330 ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት በግሪክና በግዕዝ ቋንቋዎች በተጻፉ የአክሱም ሰነዶች «ሰሜን» በሚል የሕዝብ፣ የአገርና የመንግሥት ስም የታወቀ ነበርና ሉአላዊ ሰሜን/ፈላሻ በግምት ከ300 እስከ 1632 ድረስ ለ1300 ዓመታት ከአጎራባቹ መንግሥታትና ነገሥታት ጋር ሲዋጋ እንደኖረ ከላይ ተረጋግጧል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በዚህ ረጅም ዘመን ከ320 ገደማ እስከ 1332 ድረስ ለአንድ ሺህ ዓመታት ዘመን ሰሜን/ፈላሻ በምንም ሥፍራና ጊዜ በታሪክ ሰነድ እንደገና ተጽፎ አልተገኘም። በዚህ ረጅም የሚሊኒየም ዘመን ውስጥ በአንድ በኩል በግሪክ-ሮማውያን አማካይነት ከይሁዳውያን መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ወደ ኢትዮጵያ የገባ

የክርስትና ሃይማኖት በሰሜኑ ደጋአምባ አካባቢ በተለይ በአራቱ ነባር፣ አዋማዊ፣ አጎራባችና ተዛማጅ የአክሱም-ትግሬ፣ የሰሜን/ፈላሻ፣ የአገውና የአማራ ሕዝቦች ዘንድ በሃይማኖትና በባህል ታሪካዊ መስተጋብርና መወራረስ በማስከተሉ አራቱም ማኅበረሰቦች በተዛማጅ የክብረ ነገሥትና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት በመካከለኛው ምስራቅ የይሁዳውያኑን ሕዝብ ጥንታዊ ታሪክና ባህል ከኦሪት ሃይማኖት ጋር በእምነት ግፊት የራሳቸው አድርገው እንደወሰዱ ይታወሳል። በሌላ በኩል ደግሞ በተጠቀሰው የሚሊኒየም ክፍለ ጊዜ በተለይ በ550-1270 ክፍለ ዘመን በሰሜኑ ደጋአምባ የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀትና «ዛጉዬ» ተብሎ የሚጠራው የአገው (በዘመኑ የግዕዝ ስያሜ ዘአገው) መንግሥት ክስተትና የዕድገት ሂደት ከታሪክ አኳያ እስከ ዛሬ ድረስ በትክክል አይታወቅም።

የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ጥንተ ኢትዮጵያዊነት ታሪክ ከፍ ብሎ በየደረጃው ከየሰነዱ በተገኘው መረጃ መሠረት እንደተጠቀሰው ሆኖ ኋላ እስከ ዛሬ ድረስ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጸሐፊዎች የኢትዮጵያን የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ስምና ታሪክ የሚያነሱት[130] (1) በክብረ ነገሥት ትውፊት መሠረት ከክርስትና ሃይማኖት በፊት በኢትዮጵያ የኦሪት ሃይማኖት ከይሁዳዊ የፈላሻ ሕዝብ ጋር ነበር የሚለውን ተረት ለማጠናከር፣ (2) ጉዲት የምትባል አንዲት ጨካኝ የፈላሻ ሴት የአክሱምን መንግሥት አጠፋች የሚለውን ክስ ለማስረዳትና፣ (3) የአክሱም መንግሥት በተጠቀሰችው የፈላሻ ሴት ከተደመሰሰ በኋላ በአካባቢው የአገው መንግሥት እንዴት፣ መቼና በማን ተፈጠረ የሚለውን ሌላ የታሪክ ጥያቄ ለመመለስ ሲፈልጉ ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ አሁን ከ1950ዎቹ ወዲህ በጥንቱ የደአማት-አክሱም ታሪካዊ ሥፍራዎች ላይ በተካሄደው ከፍተኛ የአርኪኦሎጂ ጥናት መሠረት አንደኛ፣ በ330 የክርስትና ሃይማኖት በግሪክ-ሮማውያን አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት በአዋማዊ የደአማት-አክሱም አገርና ቤተ መንግሥት መለኮታዊና አሀዳዊ የኦሪት ሃይማኖትና ትምህርት አልነበረም።

ሁለተኛ፣ ሁለቱም የክርስትናና የኦሪት ሃይማኖቶች ከ330 ወዲህ በግሪክ-ሮማውያን አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በግሪክ-ግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ ሚዲያ አማካይነት ነው።

ሦስተኛ፣ ከጊዜና ከታሪክ አኳያ ሲታይ፣ በሰሜኑ ደጋአምባ አካባቢ ሰሜን/ፈላሻ የተባለ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕዝብና መንግሥት

[130] Hess, "Falasha History", pp. 125-126.





ከ550-1270 ክፍለ ዘመን በኋላ የኦሪትን ሃይማኖት በግዕዝ ቋንቋ ሚዲያ አማካይነት ከአዲሱ የክብረ ነገሥት መጽሐፍና እምስጣጤዎ ሳውያን ከተባሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መምህራንና ገዳማት እንደተቀበለ ከዘመኑ የታሪክ መረጃና ትምህርት ለማንም አስተዋይ ግለሰብ ግልፅ ነገር ነው።

አራተኛ፣ በ1616-1632 የጦርነት ዘመን የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብን ከኦሪት ሃይማኖት ጋር ከአጼ ሱስንዮስና ከኢየሱሳውያን የመጨረሻ ጥፋት ያዳነው ከላይ የተገለፀው የዳሞት፣ የአገው፣ የትግሬና የአማራ ክርስቲያን ሕዝቦች የአመፅ ትግልና ድል ነው። ይህም በዘመኑ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል በጎሳ፣ በአካባቢ፣ በፖለቲካና በሃይማ ኖት ልዩነት ምክንያቶች ጠላትነትና ጦርነት ላለመኖሩ አንድ ታሪካዊ ማስረጃና ምሳሌ ነው።

አምስተኛ፣ በ1616-1632 የጦርነት ዘመን አጼ ሱስንዮስ የሰሜን/ፈላሻን መንግሥት አሸንፎ ሕዝቡን የንጉሡ ባሪያና ገባር ካደረገ በኋላ በተከዜና በዓባይ ወንዞች ክልል የሚገኘው የሕዝቡ ጥንታዊና እስትራቴጂያዊ ምድር ለአዲሱ የጎንደር መንግሥት የኢኮኖሚ መቲረትና የፖለቲካ ማዕከል ሆነ። በመሆኑም በኢትዮራያ ዛርው የአማራ ማዋበረሰብ ዕድገት የጥንቱ የሰሜን/ፈላሻ ምድርና ሕዝብ አንድ ታላቅ ምንጭና መሠረት ሆነ።

ስድስተኛ፣ በ1616 አጼ ሱስንዮስ ለሰሜን/ፈላሻ ኦሪታዊ ሕዝብ በሞትና በክርስትና ሃይማኖት መካከል ያንዱን ምርጫ በሰጠ ጊዜ ብዙዎቹ «በፍጥነት በክርስትና እየተጠመቁ»[131] ሕዝበ- ክርስቲያን እንደሆኑ በንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሐፊ በተክለ ሥላሴ ተጽፏል። በዚህ በታወቀ የሰለሞናውያኑ የአገዛዝ ሥርዓት ብዙ ኦሪታዊ ሰሜን/ፈላሾች ስማቸውን ሃይማኖታቸውንና ቋንቋቸውን በመለወጥ ከጊዜ በኋላ ክርስቲያን የጎንደር ሕዝብ ሆኑ። ሌሎች ደግሞ በመሬት በባህልና በሃይማኖት ከአገው፣ ከትግሬና ከአማራ አጎራባችና ተዛማጅ የቋንቋ ማህበረሰቦች ጋር ተቀላቀሉ።

ሰባተኛ፣ የአጼ ሱስንዮስን የ1616 የኃይል ጥምቀት በመቃወም በኦሪት ሃይማኖታቸው ጸንተው የቆሙ ሰሜን/ፈላሾች ከመሬታቸው ተነቀሉ። ተጋዙ። እነዚህ አሁን ራሳቸውን «ቤተ እሥራኤል» ብለው የሚጠሩ ንቅል፣ ተፈናቃይ ሰሜን/ፈላሾች በግምት ከ1616 እስከ 1990 ድረስ ለአራት ምዕተ ዓመታት በተወሰኑ መንደሮችና አካባቢዎች በእርሻ፣ በሸክላ፣ በእንጨት፣ በብረት፣ በቆዳና በልብስ ያራዎች

[131] ተክለ ሥላሴ፣ ሱስንዮስ ታሪክ ም. 44 ቁ. 209።

ተሰማርተው ኖሩ። በመሆኑም በኅብረተሰቡ ዘንድ ጠይብ፣ ቡዳና አስማተኛ ተብለው በስድብ ስም የሚጠሩ የኢትዮጵያ አንድ ልዩ የሃይማኖትና የዕደጥበብ ካስት ማኅበረሰብ ሆኑ።

በመጨረሻ በ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ የኢትዮጵያ ቤተ እሥራኤል/ፈላሾች በሥርዓትና በሃይማኖት ግፊት የጥንቱ አገራችን ወደ ሚሉት ወደ እሥራኤል ፈለሱ።

ይህ ከዚህ በላይ ባጭርና በጥቅል የቀረበው የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ረጅም የቁጡዙዙ ዓመታት የመከራና የጦርነት ታሪክ በኢትዮጵያ ዘውዳዊ የሥርዓት ፣ የሕዝቦች መከራ አንድ ምሳልና መግለጫ ብቻ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር የቅርቡ በ60000 የሚቆጠሩ ቤተ እሥራኤሎች የአገረ እሥራኤል ፍለሳ የኢትዮጵያ የሰሜን/ፈላሻ ረጅም ታሪክ ፍጻሜ አይደለም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ልዩ የሕዝቦች፣ የቋንቋዎች፣ የባህሎችና የሃይማኖቶች መስተጋብርና መወራረስ ልምድና ታሪክ መሠረት በተጠቀሰው ረጅም ዘመን ሰሜን/ፈላሾች በመሬት፣ በጊዜ፣ በቋንቋ፣ በደም፣ በባህልና በእምነት በአካባቢው የአገው፣ የአማራና የትግሬ ነባርና ተዛማጅ ሕዝቦች አካል ሆኗልና። እቴጌ ምንትዋብ፣ ዳጃች ውቤ፣ አጼ ቴዎድሮስና እቴጌ ጣይቱ የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ታላላቅ የአገርና የመንግሥት መሪዎች የወለደ አንድ የአገሪቱ ነባር ዘርና ሕዝብ ነውና።





# 4. የእስልምና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

## ከእስልምና በፊት የኢትዮጵያና የአረቦች ታሪካዊ ግንኙነት

### *የኢትዮጵያና የሮማውያን የፖሊሲ ስምምነት በአረቢያ*

በ610-632 በአረቢያ በነቢዩ ሙሐመድ አብደላ የተመራው ታላቁ የአረቦች እስላማዊ አብዮት ታሪካዊ መነሻዎችና ዓለማቀፋዊ ውጤቶች በአካባቢው በሦስቱ የሮማውያን፣ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል ለረጅም ዘመን ከተካሄዱ ጂኦ-ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዙ ናቸው።

ከታሪክ እንደሚታወቀው፣ ሮማውያን በ30 ዓመተ ዓለም ግብፅን ለሦስት ምዕተ ዓመታት (332-30) ከገዙት ግሪኮች ያዙ። በዚህ የግሪኮ-ሮማውያን ዓለማቀፋዊ የሽግግር ዘመን በላይኛው ዓባይ ሸለቆ ጥንታዊ የኑቢያ-ሚሮዌ መንግሥት እንዲሁም በአኅራባቹ አረቢያ ሚናና፣ ሳባ፣ ቀጣባን፣ ሃድራማዊ፣ ሂሚያሪትና ሃምዳና የተሰኙ አናሳ የአረብ መንግሥታት በየበኩላቸው በራሳቸው ውስጣዊና አካባቢያዊ ምክንያቶችና ግፊቶች ሁሉም በፈጣን የውድቀት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ነበሩ።[1]

እነዚህ የዘመኑ ታላላቅ አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ክስተቶች፣ ሁኔታዎችና ሂደቶች የዓባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕር፣ የአረቢያና የመካከለኛው ምስራቅ እስትራቴጂያዊ አገሮችን ለሦስቱ የሮም፣ የፋርስና የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥታት ክፍት የግዛትና የተፅዕኖ አካባቢዎች አደረጉ።[2]

ይሁን እንጂ በአካባቢው ከሦስቱ ተጠቃሽ መንግሥታት፣ በእስትራቴጂያዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በደጋማው ክልል የሚገኘው የኢትዮጵያውያኑ መንግሥት በተጠቀሱት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ለዓባይ ሸለቆ፣ ለቀይ ባሕርና ለኤደን ባሕረሰላጤ ጠረፍ ንግድ፣ ሰላምና ፀጥታ ዋስትና ለመስጠት ብቃት ያለው ኃይል

[1] Kobishchanov, Axum, p. 36.

[2] Ibid., p.37.